አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# ሀገረሰብአዊ የአስተዳደር ስርዓትና የግጭት አፈታት ዘዴዎች በአኝዋ ብሔረሰብ

በ

አበበ ኃይሉ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# ሀገረሰብአዊ የአስተዳደር ስርአትና የግጭት አፈታት ዘዴዎች በአኝዋ ብሔረሰብ

በ

አበበ ኃይሉ

ሐምሌ 1999

አዲስ አበባ

# ህገረሰባዊ የአስተዳደር ስርአትና የግጭት አፈታት ዘዴዎች በአኝዋ ብሔረሰብ

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በኢትዮጵያ ስነጹሑፍና ፎክሎር መርሐግብር ለኤም.ኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

አበበ ኃይሉ

አማካሪ፣ ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሐምሌ 1999

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል
የኢትዮጵያ ስነጹሑፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ ፕሮግራም

# ህገረሰባዊ የአስተዳደር ስርአትና የግጭት አፈታት ዘዴዎች በእኙዋ ብሔረሰብ

ከአበበ ኃይሉ

ሐምሌ 1999

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ፈቃዱ አዘዘ
አማካሪ
ፊርማ

ታደለ በሬሶ
የውጭ ፈታኝ
ፊርማ

ዮናስ አድማሱ
የውስጥ ፈታኝ
ፊርማ

# ምስጋና

እስፈላጊውን የምክር አገልግሎት ለሰጡኝ ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ ከፍ ያለ ምሥጋና አቀርባለሁ:: የገንዘብ ድጋፍ ላደረጉልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና CRDA እንዲሁም በመስክ ስራ ላይ ከጐኔ ላልተለዩኝ አቶ ኡጉታ ኢዲውና ሀኪም ኡፓራ ምስጋናዬ የላቀ ነው::

# ማውጫ



አጠቃሶ ገጽ

1. መግቢያ ........ 1
   - 1.1 ጥናቱን ለማካሄድ ያነሳሳኝ ምክንያት ........ 1
   - 1.2. የጥናቱ አላማ ........ 2
   - 1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 2
   - 1.4. የመረጃ ምንጮች ........ 2
   - 1.5. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች ........ 3
   - 1.6. ከመስክ መረጃ የተሰባሰበባቸው ቦታዎችና ቀናት ........ 3
   - 1.7. የጥናቱ ገደብ ........ 4
   - 1.8. ያጋጠሙ ችግሮች ........ 5
   - 1.9. አካባቢውያዊ ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ዳራ ........ 5
2. ከለሳ ድርሳናት ፣ ስለፖለቲካ ተቋም ፣ ግጭትና የግጭት አፈታት ዘዴዎች የሚያወሱ ትውሮች ፣ ሀሳቦች ፣ ድፍየናዎችና አንዳንድ የአፍሪካ ጎሳዎች ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ........ 8
   - 2.1. ከለሳ ድርሳናት ........ 8
   - 2.2. የፖለቲካ ተቋም ........ 13
   - 2.3. ስለግጭት የሚያወሱ ትውሮችና ድፍየናዎች ........ 15
   - 2.4. ስለ የግጭት መንስኤዎች የሚያወሱ ሀሳቦችና ትውሮች ........ 17
   - 2.5. ስለ ግጭት መፍቻ ዘዴዎች የሚያወሱ ሃሳቦችና ትውሮች ........ 19
   - 2.6. አንዳንድ የአፍሪካ ጎሳዎች ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ........ 20
3. የመንግስታትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ግጭቶችን መፍቻት የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎችና ልማዳዊ ሕጎች በኢትዮጵያ ሕጎች ስለመካተታቸው የተደረገ ቅኝት ........ 26
   - 3.1. የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ........ 26
   - 3.2. የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ........ 28
   - 3.3. የአፍሪካ ሕብረት ........ 28
   - 3.4. የአፍሪካ ቀጠናዊ መንግስታትና መንግስታዊ ያልሆኑ ርጅቶች ........ 29
   - 3.5. የኢትዮጵያ ሕጎች ........ 30
     - 3.5.1. የፍትሐብሄር ሕግ ........ 31
     - 3.5.2. የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ........ 33
   - 3.6. የአኘዋ ልማዳዊ ሕጎች ........ 34

4. የአኝዋ ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርአት ........................................ 37
4.1. የአስተዳደሩ አደረጃጀትና ባለስልጣናት ........................................ 37
4.2. ጆ ሉዋክ ........................................ 39
4.3. የኚያ አስተዳደርና የንግስና ስነስርአት ክንዋኔዎች ........................................ 41
4.4. የኳሮ አስተዳደርና የሹመት በአል ስነስርአት ክንዋኔዎች ........................................ 46
4.5. የቤተመንግስቱ ምድረ ግቢ ገጽታ ........................................ 48
4.6. የመሪዎችና የህዝቡ ግንኙነት ........................................ 49
5. ዋና ዋና የግጭት መንስኤዎችና ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች በአኝዋ ብሔረሰብ ........................................ 51
5.1. ዋና ዋና የግጭት መንስኤዎች ........................................ 51
5.2. ካርሱክ — የአኝዋ ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋም ........................................ 55
5.2.1. የችዎትና ቡሬ ካርሱክ ........................................ 56
5.2.1.1. የችዎትና ቡሬ ስነስርዓት ሂደትና ክንዋኔዎች ........................................ 58
5.2.1.2. የጉርቶንግ ስነስርዓት ክንዋኔዎች ........................................ 64
5.2.2. አቻንግ ደዎቶ ........................................ 67
5.2.3. ካርጎአል ሉፕ ........................................ 71
5.2.4. ጆዉ ዊማች ........................................ 75
5.2.5. ግርፋትና እርግማን የሚያስከትሉ ድርጊቶች ........................................ 76
6. የግጭት አፈታት በአኝዋ ተረቶች ........................................ 79
በተረቶቹ የግጭት አፈታት ላይ የተደረገ ትንተና ........................................ 79
ማጠቃለያ ........................................ 83
ደሁንታ ........................................ 86
ዋቢ መጽሐፍት ........................................ 87
የመረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር ........................................ 91
አባሪ አንድ ሚቶች
አባሪ ሁለት ትንተና የተደረገባቸዉ ተረቶች

# 1 መግቢያ

ይህ ጥናት በስድስት ክፍሎች የተከፋፈለ ሲሆን ክፍል አንድ የጥናቱ መግቢያ ነው። በክፍል ሁለት ክለሳ ድርሳናት፣ ስለፖለቲካ ተቋማት፣ ስለግጭትና የግጭት አፈታት ዘዴዎች በአንዳንድ ምሁራን የተሰጡ ድፍየናዎችና (definitions) ሀሳቦች ታይተዋል።




የጋምቤላ ክልል ካርታ

ILS LIBRARY
ABA UNIVERSITY

# 1 መግቢያ

ይህ ጥናት በስድስት ክፍሎች የተከፋፈለ ሲሆን ክፍል አንድ የጥናቱ መግቢያ ነው። በክፍል ሁለት ክለሳ ድርሳናት፣ ስለፖለቲካ ተቋማት፣ ስለግጭትና የግጭት አፈታት ዘዴዎች በአንዳንድ ምሁራን የተሰጡ ድፍየናዎችና (definitions) ሀሳቦች ታይተዋል። በክፍል ሦስት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት፣ የአፍሪካ ሕብረት (የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን ጨምሮ)፣ አንዳንድ የአፍሪካ ቀጠናዊ መንግስታትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ግጭቶችን ለመፍታት ስለሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች፣ የኢትዮጵያ ሕገመንግስት፣ የፍትሐብሄርና የወንጀለኛ መቅጫ ሕጎች ልማዳዊ ሕጎችን ስለተመለከቱበት ሁኔታና አንዳንድ የተጠኑ የአፍሪካ ጎሳዎች ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች በምሳሌነት ቀርበዋል። በዚህ ክፍል የአኝዋ ልማዳዊ ሕጎችም ተካተው ቀርበዋል። በክፍል አራት ስለአኝዋ ቤተሰብ ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርዓት አደረጃጀት፣ የሹመት በአል ስነስርዓቶች፣ ክንዋኔዎች፣ እንዲሁም በሕዝቡና የመሪዎች ግንኙነት ላይ ገለጻዎችና ማብራሪያዎች ተሰጥተዋል። ክፍል አምስት ያተኮረው ስለአኝዋ የግጭት አፈታት ዘዴዎች፣ ደንቦች፣ ስነስርዓቶችና ክንዋኔዎች ላይ ነው። ክፍል ስድስት በአንዳንድ የአኝዋ ተረቶች ውስጥ ግጭቶች ሲከሰቱ የሚፈቱበትን አግባብ በተመለከተ ትንታኔ ተሰጥቶአል። በመጨረሻም ማጠቃለያና ከርዕስ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሚቶችና ተረቶች አባሪ ተደርገው ቀርበዋል።

## 1.1 ጥናቱን ለማካሄድ ያነሳሱኝ ምክንያቶች

በጋምቤላ ሕዝቦች ብሄራዊ ክልል ባህልና ስፖርት ቢሮ ስሰራ በነበርኩባቸው አመታት አኝዋዎች ሀገረሰባዊ ዘዴዎችን በመጠቀም ግጭቶችን ሲፈቱ አልፎ አልፎ ለመመልከት በመቻሌ ይህ አገር በቀል ሥርዐት (tradition) ሊጠናና ሌሎችም ሊያውቁት ይገባል የሚል ሀሳብ አድሮብኝ ነበር። በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ድኅረ ምረቃ ፕሮግራም የተማርኩት ትምህርትም ከርዕስ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያለው ሆኖ ስላገኘሁት የነበረኝን ፍላጎት እውን ለማድረግ ነው ይህን ጥናት በዋናነት ለማካሄድ የወሰንኩት። ሌላው እንደምክንያት የሆነኝ ኩሪሞቶ (Kurimoto) የሚባል ጃፓናዊ አጥኚ "Natives and Otsiders: The Historical Experience of the Anyaa of Western Ethiopia" በሚል ርዕስ የጻፈውን መጣጥፍ ጋምቤላ በነበርኩበት ወቅት ሳነብ የኢትዮጵያ አካዳሚያዊ ጥናቶች የጠረፍ አካባቢዎችን



ADDIS ABABA UNIV... ILS LIBRARY

የሆነ ናቸው "*Also academic studies of Ethiopia have neglected peoples of periphery*" (2001:1). ማለቱ በወቅቱ ትኩረቴን ስቦት ነበር:: ይብዛም ይነስም የተደረጉ ጥናቶችን ጭራሽ ከግምት ሳያስገባ እዚህ ድምዳሜ ላይ መድረሱ ይህን ጥናት ለማካሄድ በተወሰነ ደረጃ ተጨማሪ መነሳሳትን ፈጥሮልኛል ማለት እችላለሁ::

## 1.2 የጥናቱ ዓላማ

ስለ እኝዋ ብሔረሰብ ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርዓት ተቋማዊ አደረጃጀት፣ ስለ መሪዎች የመመረጫ መስፈርት፣ የበዓለ ሹመት ስነስርዓቶችና ክንዋኔዎች፣ ስለሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች፣ ስነስርአቶች፣ ክንዋኔዎችና ፎክሎራዊ ገጽታዎችን መግለጽና ማብራራት የዚህ ጥናት አላማ ነው::

## 1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት

እኝዋዎች እራሳቸው ባዳበሩዋቸው ሀገረሰባዊ ተቋማት እየተመሩ በአካባቢያቸው ሰላምና መረጋጋትን ለማስፈን ያስቻሉዋቸውን የፎክሎር ቅርሶች ለመመርመርና በአግባቡ እንዲታወቁ ለማስቻል፣ ለሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ህዝቡ የበለጠ ተረቢታ ሰላለውና አሁንም እየተገለገለባቸው ስለሚገኝ ግጭቶችን በአካባቢው ወግና ልማድ መሰረት እንዲፈቱ የሚያደርግ ጠቀሜታን ለመጠቆም ነው:: በተጨማሪም ይህ ጥናት ወደፊት በርዕስ ጉዳዩ ዙሪያ ጥናት ለሚያካሂዱ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፣ ለእኝዋ ባህል ጥናት መጎልበትም የበኩሉን ድርሻ ያበረክታል::

## 1.4 የመረጃ ምንጮች

ስለእኝዋ ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርዓትና የግጭት አፈታት ዘዴዎች የዳበረ ልምድና ዕውቀት ያላቸው የብሔረሰቡ አንጋፋ የአገር ሽማግሌዎች፣ ጎልማሶች፣ ምሁራንና የስራ ኃላፊዎች የዚህ ጥናት አውራ የመረጃ ምንጮች ናቸው:: በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት የተሳተፉ ከ40-80 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው:: እነዚህም ሁለት በቀድሞው የባህላዊ አስተዳደር ስርዓት የቀበሌ ኳሮ (የቀበሌ ሹም ወይም አስተዳዳሪ) የነበሩ፣ አንድ የኚያ (ንጉስ) ሚስት የነበረች፣ አምስት የመሪዎች ሹመት በአል ሲከናወን ተሳታፊ የነበሩ፣ ዘጠኝ ረዘም ላለ ጊዜ በሽምግልና

ስራ ተሳታፊ የነበሩና የጻበረ ልምድ አላቸው የሚባሉ፣ አምስት የህብረተሰቡን ቃላዊ ባህልና ታሪክ በመተረክ የሚታወቁ ሽማግሌዎች፣ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከተቋቋመው የአገር ሽማግሌዎች አማካሪ ምክር ቤት አባላት መካከል ሶስት ሰዎች፣ የአስተዳደር፣ ፍትህና ጸጥታ ዘርፍ ቢሮ ኃላፊ፣ የፍትህ ቢሮ ኃላፊ፣ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ፣ የሴቶች ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ እንዲሁም ሁለት የባህልና ቱሪዝም መምሪያ ኃላፊዎች ናቸው። ከ1983-1995 ዓ.ም እ.ኢ.አ በክልሉ ባህል ቢሮ ስሰራ በነበርኩባቸው አመታት ያሰባሰብኳቸውን አንዳንድ መረጃዎችም ለዚህ ጥናት በግብዓትነት (input) ተጠቅሜአለሁ።

## 1.5 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

መረጃዎች የተሰባሰቡት በቃለ መጠይቅ፣ በቡድን ውይይት፣ በምልከታና ከአንዳንድ የታተሙ ጽሑፎች ነው። የጽሑፉን የመጀመሪያ ረቂቅም ከመረጃ አቀባዮች ለአንዳንዶቹ ልኬ አንዳንድ እርማቶች ተደርገዋል። እንደአስፈላጊነቱም case studies ተጠቅሜአለሁ።

## 1.6 መረጃዎች ከመስክ የተሰባሰቡባቸው ቦታዎችና ቀናት

ጥናቱ የተካሄደው በጋምቤላ ከተማ ዙሪያ ወረዳ በሚገኙ ኡሚኒጋ፣ ዶዘር ኡላሚ፣ ኡዊሊንጋ፣ ጀጀቢ ሠፈር፣ ኢሌይ፣ ቱር ኪርና ጎግ በጀሚ ቀበሌዎች ነው። ህዳር 25ና 26/1999 ከክልሉ መስተዳድር ጽ/ቤትና የባህልና ቱሪዝም ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ጋር ስለጥናቱ አላማ ውይይት በማካሄድ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ቅድመ ሁኔታዎችን የማመቻቸትና እውራ መረጃ አቀባዮችን የመለየት ስራ ተከናውኖአል። ህዳር 27፣ 28 እና 29/1999 ከባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ተወካይ ጋር በመሆን ለመረጃ አቀባይነት የተመረጡ ሰዎች ወደሚገኙባቸው ቀበሌዎች በመሄድ ቃለ መጠይቅና የቡድን ውይይት ለማካሄድ ስለሚቻልበት ሁኔታ ተወያይተን ዕቅድ አውጥተናል።

ከየቀበሌዎቹ የተመረጡ መረጃ አቀባዮች በሰጡኝ ቀጠሮ መሠረት ከታህሳስ 2-4 ኢሌይ፣ ከታህሳስ 6-9 ኡሚኒጋና ጎግ በጀሚ፣ ከታህሳስ 11-13 ቱር ኪር ቀበሌዎች በመገኘት መረጃዎች በቃል መጠይቅ ተሰባስበዋል። ታህሳስ 16 እና 17

በባህልና ቱሪዝም ቢሮ ከባህል መምሪያ ኃላፊ፣ ከፀጥታ፣ አስተዳደርና ፍትህ ዘርፍ ቢሮ ኃላፊ፣ ከሴቶች ጉዳይ ቢሮ ኃላፊና በፍትህ ቢሮ የጋምቤላ ዙሪያ ወረዳ አቃቤ ህግ ባለሙያ ጋር ውይይትና ቃለ መጠይቅ ተደርጓል::

ከታህሳስ 18-20 ደግሞ ጃጃቤ ሠፈርና ዶዘር ኡላሚ ቀበሌዎች ከሚኖሩ የአገር ሽማግሌዎች ጋር በቡድን ውይይትና በቃለ መጠይቅ መረጃዎች ተሰባስበዋል:: ታህሳስ 21 እና 22 አንዳንድ ግልጽ ያልሆኑና ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው ነጥቦችን በመለየት ጋምቤላ ከተማ ከሚገኙ አውራ መረጃ አቀባዮች ጋር የቡድን ውይይትና ቃለ መጠይቅ ተካሂዶአል:: ከማውቃቸው እኝዋዎች ጋር ስገናኝም ተመሳሳይ ጥያቄዎችን በማንሳት መደበኛ ባልሆነ መልኩ (informal) ውይይቶች በማድረግና ማብራሪያዎችን በመጠየቅ የመረጃዎቼን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ተጠቅሜአለሁ:: በቃለ መጠይቅና የቡድን ውይይት ስድስት ካሴት መረጃዎች ተሰባስበዋል:: የእርቅ ስነስርዓት ክንዋኔዎች ደግሞ አርባ ደቂቃ በሚፈጅ የቪዲዮ ካሴት ተቀርጸዋል::

ታህሳስ 23 በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከተቋቋመው አማካሪ የአገር ሽማግሌዎች ምክር ቤት አባላት ጋር ቃለ መጠይቅና ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በመጠቀም እያከናወኑ ስላሉት ተግባራት ውይይት ተካሂዶአል:: ታህሳስ 24 እና 25 የዕርቅ ስነስርዓት ክንዋኔዎችን በቅንብር ተፈጥሮአዊ መቼት (በተፈጥሮአዊ አውድ የሚከናወነውን በትክክል አስመስሎና አቀነባብሮ ማዘጋጀት) ለማዘጋጀት ቅድመ ዝግጅቶችን ከአገር ሽማግሌዎች ጋር በመሆን ለማከናወን ተችሎአል:: ታህሳስ 26 በቅንብር ተፈጥሮአዊ መቼት የዕርቅ ስነስርዓት ክንዋኔዎችን ቪዲዮ በመቅረጽና ፎቶግራፍ በማንሳት አጠቃላይ የመረጃ ማሰባሰብ ስራ ተጠናቋል::

## 1.7 የጥናቱ ገደብ

የእዚህ ጥናት ገደብ ስለአኝዋ ብሔረሰብ ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርዓትና የግጭት አፈታት ዘዴዎችን ፣ አደረጃጀቶችን ፣ ስነስርዓቶችን ፣ ክንዋኔዎችን ፣ ደንቦችንና ፎክሎራዊ ገጽታዎችን መግለጽና እንደአስፈላጊነቱም ትንታኔ መስጠት ነው::

## 1.8 ያጋጠሙ ችግሮች

የዕርቅ ስነስርዓቱን ከነዋኒ በቅንብር ተፈጥሮ መቼት አዘጋጅቶ ቪዲዮ ለመቅረጽና ፎቶግራፍ ለማንሳት የተያዘው በጀት 1,500 ብር ነበር። ይሁን እንጂ በወቅቱ ተፈጥሮ በነበረው የዋጋ ንረት ምክንያት በዚህ ዋጋ የተፈለገውን በሬ መግዛት አልተቻለም። ችግሩን ለመፍታት በቅድሚያ ጋምቤላ በነበርኩባቸው አመታት (1983-95) ያፈራኋቸውን ወዳጆቼን አማከርኩ። እነሱም ችግሬን ተገንዝበው በከብት ንግድ ስራ የተሰማሩ ነጋዴዎችን በማነጋገር እነሱ ከገበሬ በገዙበት ዋጋ እንዲሸጡልኝ በማድረጋቸው ችግሩ ሊቃለል ችሉአል።

## 1.9 አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ዳራ

የጋምቤላ ክልል ከአዲስ አበባ በ753 ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን በሰሜን ከቤኒሻንጉል ጉሙዝና ከኦሮሚያ፣ በደቡብ ከሱዳንና ከደቡብ ብሄር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በምስራቅ ከኦሮሚያና ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በምዕራብ ደግሞ ከሱዳን ይዋሰናል። ክክልሉ አስር ወረዳዎችና አንድ የከተማ መስተዳድር አኙዋዎች የሚኖሩት በአቦቦ፣ ጎግ፣ ጆር፣ በከፊል ደግሞ በአኮቦ፣ ኢታንግ፣ ዲማና ጋምቤላ ዙሪያ ወረዳዎች ነው። የክልሉ ነባር (indigenous) ብሔረሰቦች አኙዋ፣ ኑዌር፣ መዠንግር፣ ኦፖዎና ኮሞ የሚባሉት ናቸው። ከደጋማው የኢትዮጵያ አካባቢዎች የመጡ የተለያዩ ብሔርና ብሔረሰቦች አባላትም በክልሉ ወረዳዎች በንግድ፣ በግብርናና የመንግስት ስራ ተሰማርተው ይኖራሉ። በ1994 የህዝብና ቤት ቆጠራ መሰረት 182,000 ከሚሆነው የክልሉ ህዝብ ቁጥር የአኙዋ ብሔረሰብ ብዛት 45665 ነው (CSA 1995)። አኙዋዎች በአብዛኛው ሰፍረው የሚኖሩት የአኮቦ (ባሮ)፣ ጊሎ፣ አልዌሮ፣ አኮቦና የአሉዌሮን ወንዞች ተፋሰስ ግራና ቀኝ ተከትለው ነው። በአንድ መንደር ተሰባስበው የሚኖሩ አኙዋዎች በዝምድና የተሳሰሩ፣ የአንድ ጎሳ አባላት የሆኑና የቅርብ ትውውቅ ያላቸው ናቸው። የወንዞቹን ተፋሰስ ተከትለው ለመኖሪያነት የመረጡበት ምክንያት በቢጋው ወራት ከወንዞቹ ግራና ቀኝ የሚገኝ ውሃ ሸሽ መሬት ለእርሻ ስራ ምቹ በመሆኑና አሳ ለማጥመድ ስለሚያመቻቸው እንደሆነ አቶ ኡጉታ አዲውና ሀኪም ኡፓራ ገልጸውልኛል። አኙዋዎች ኑሮአቸው የተመሰረተው በግብርና፣ አሳ በማስገርና



ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

በአደን ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ እንስተኛ ቁጥር ያላቸው በመንግስት ስራና በንግድ ተሰማርተው ይገኛሉ።

በእኝዋ ቤሌረሰብ መካከል መተሳሰብ፣ መረዳዳትና ያገኙትን በጋራ ተካፍሎ መኖር የባህላቸው አይነተኛ መገለጫዎች ናቸው። ይህ ሁኔታ በተለይ የዝምድና ትስስር ባላቸው ዘንድ ጎልቶ ይስተዋላል። ያለውን የማያካፍልና ግለኝነትን የመረጠ ከዘመዶቹና ከህብረተሰቡ እንዲፈነገጠ ተቃጥሮ መገለልና እርግማን ሊደርስበት ይችላል። ኑሮአቸው በጋራ መተሳሰብ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ላለመገለልና እርግማን እንዳይደርስባቸው እንዋሥን ጥንቃቄ ያደርጋሉ። እኝዋ የሚለው የብሔረሰቡ መጠሪያ ስምም ይህንን የሚያንጸባርቅ ነው። «እኝዋ ማለት ህብረት፣ አብሮ መኖር፣ መረዳዳት፣ መደጋገፍ ማለት ነው» (አቶ ኡትታ አዲው፣ ቃህሳስ 10፣ 1999)። የእኝዋ ቋንቋዋ ደግሞ ከናይሎ ሰሐራ የቋንቋዎ ቤተሰብ በቻሪ ናይል (Char-iNile) ስር እንደሚመደብ በግሪንበግ (Greenberg) ተገልጾአል።

የአንድ ሰፈር ጎልማሶች፣ አዛውንቶች፣ ወጣቶችና አንዳንዴም ህፃናት በተለይ ጠዋትና ማታ ማታ ሁሌም ቢሆን መገናኛቸው «ዊማች» በሚባል ከሳር የተሰራ ዳስ ውስጥ ነው። የአገር ሽማግሌዎች በጋራ ጉዳያቸው ላይ የሚወያዩትም በዚሁ ስፍራ ነው። በዊማች ሁሌም ቢሆን እሳት አይጠፋም። «ዊማች» የሁለት ቃላት ጥምር ሲሆን «ዊ» በእድሜ ጠና ያሉና አዛውንቶች ማለት ሲሆን «ማች» ደግሞ እሳት ማለት ነው። በተለይ ማታ ማታ አዛውንቶች ስለህብረተሰቡ ልዩ ልዩ ደንቦች፣ስርዓቶች፣ እምነቶች ወዘተ የሚያወሱ ተረቶችን ለወጣቶችና ለህጻናት የሚተርኩት በዊማች ነው። በአጠቃላይ የእኝዋ ባህልና ታሪክ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተተረከ የሚተላለፍበት ዋናው ቦታ ዊማች እንደሆነ አቶ ኡትታ አዲው ነግረውኛል። በዊማች የማይገኝ ሰው ከህብረተሰቡ ማህበራዊ ህይወት እንዲፈነገጠ ስለሚቆጠር በተቸገረ ጊዜ የሚረዳው ሲያጣ ይችላል።

እኝዋዎች ምድርንና ፍጥረታቱን የፈጠረ አንድ አምላክ «ጆዋክ» (እግዚአብሔር) ነው ብለው ያምናሉ። አቶ ኝንዎ አበላ እንደገለጹልኝ "እኝዋዎች ሰው ከሞተ በኋላ ነፍሱ በምድር ላይ ሆኖው ሆና አብራን ትኖራለች የሚል አመለካከት ስላላቸው በሕያዋቻቸውና ቅድመ አያቶቻቸው መንፈስ ያምናሉ"። በአሁኑ ጊዜ ብዛታቸውን

ተገቢውን መረጃ ለማግኘት ባልቻልም በርካታ አኝዋዎች የፕሮቴስታንት ሀይማኖት ተከታዮች መሆናቸውን አቶ ኡጉታ አዲው ነግረውኛል።

በአኝዋ ብሔረሰብ የተለያዩ የጋብቻ አይነቶች አሉ። በፍቅረኛሞች ፍላጎት ላይ የተመሰረተ "ቸድ"፣ በወላጆች ስምምነት "ሚየክ"፣ ያለተጋቢዎች ፍላጎት በሌላ አስገዳጅ ሁኔታ የሚፈጸም "ቢየል"፣ በኢኮኖሚ ችግር አስገዳጅነት የሚፈጸም "ዶኛ"፣ የውርስ ጋብቻ ደግሞ "ዶንግ ጋች" ይባላል። በሁሉም የጋብቻ አይነቶች ጥሎሽ መክፈል ግዴታ ነው። ጥሎሽ ያልከፈለ ትዳር መመስረት አይችልም። ለጥሎሽ የሚከፈል "ድሙኝ" (ከጨሌ የተሰራ የአንገት ጌጥ) በአኝዋዎች ዘንድ ትልቅ ዋጋ አለው። በአሁኑ ጊዜ ግን ራቅ ካሉ የገጠር አካባቢዎች በስተቀር ጥሎሽ በገንዘብ ተቀይሮአል።

ከገንዘብና ኢኮኖሚ ቢሮ ባገኘሁት መረጃ መሰረት የክልሉ መሬት አቀማመጥ ከምስራቅ ከፍተኛ ቦታዎች ወደ ምዕራብ ተዳፋቱ እየቀነሰ የሚመጣና ከ2000-3000 ሜትር ከባህር ወለል በላይ ከፍታ ልዩነት ውስጥ የሚጠቃለል በረሀማ አካባቢ ነው። አማካይ የሙቀት መጠኑ ከ22-33 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ የሚደርስ ሲሆን ከፍተኛ ወርሃዊ አማካኝ ሙቀት 45 ዲግሪ ሴንቲግሬድ በመጋቢት ወር፣ ዝቅተኛው ደግሞ 10.3 ዲግሪ ሴንቲግሬድ በታህሳስ ወር ተመዝግቦአል። 2,754120 ሄክታር ከሚሆነው የክልሉ መሬት ስፋት 577,392 ሄክታር በከፍተኛ ደን ቀረው ደግሞ በቢሻና ቁጥቋጦዎች የተሸፈነ ነው።

# 2 ክለሳ ድርሳናት ፣ ስለ ፖለቲካ ተቋም ፣ ግጭትና የግጭት አፈታት ዘዴዎች የሚያወሱ ትውሮች ፣ ድፍረያናዎችና አንዳንድ የአፍሪካ ጎሳዎች ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች

## 2.1 ክለሳ ድርሳናት

ከአኝዋ ባህልና ታሪክ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶችን Evans Pritchard (1940), Godfrey Lianhardt (1957), Eise Kurimoto (1992, 1996, 2001,2002), Bayleyegn Tasew (1999,2005), Abraham Sewonet (2005) አካሂደዋል፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቦአል፡፡

ኢቫንስ ፕሪቻርድ(Evans Pritchard) "The Political System of Anuak" በሚል ርዕስ በጻፈው መጽሐፍ ስለአኝዋ ባህላዊ አስተዳደር፣ ስለመንደር አመሰራረት፣ የስምና ቅጽል ስም አወጣጥን በከፊል ተመልክቶአል፡፡ በዋናነት ያተኮረው ግን የኚያን (ንጉስ) ወንበር ለመያዝ ሲባል በአኝዋዎች መካከል ስለተካሄዱ ሽኩቻዎችና ይህን ተከትሎ ስለተፈጠሩ ግጭቶችና የንገሱ ነገስታትን ታሪክ በመግለጽ ላይ ነው፡፡

በጥናቱ እንደተገለጸው አኝዋዎች በ"ኚያ" (ንጉስ) እና በ"ኳር" (የቀበሌ ሹም ወይም አስተዳዳሪ) የሚመሩ ሁለት አይነት ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓቶች አሉዋቸው፡፡ ኳር አንጻር ሲታይ ኚያ የሚያስተዳድረው የግዛት ክልል ሰፊ ቢሆንም በኳር ከሚተዳደሩ ቀበሌዎች ጋር የሚያገናኘው የዕዝ ሰንሰለት የለም፡፡ በአኝዋ ባህላዊ አስተዳደር ቀበሌዎች የየራሳቸው ሉአላዊነት ያላቸው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማዕከላት ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ቀበሌም ከባላባት ዘር የሚመረጥ ኳር አለው፡፡ በሁለቱም የአስተዳደር ስርዓቶች ህዝቡ እስከፈቀደ ድረስ ስልጣንን ከአባት ወደ ልጅ በውርስ ማስተላለፍ ይቻላል፡፡ ባህሉ በሚፈቅደው መርህ መሰረት ተግባርና ኃላፊነቱን መወጣት ያልቻለ መሪ በሰላማዊ መንገድ ወይም በሀይል ከስልጣን እንዲወርድ ተደርጎ በምትኩ የህዝብ ድጋፍ ያለው ስልጣን እንዲይዝ የሚደረግበት ስርዓትም አለ፡፡ በኢቫንስ ፕሪቻርድ እንደተገለጸው የአኝዋ ባህላዊ የአስተዳደር ስርአት ዲሞክራሲያዊ ነው " *The system is democratic, inhibiting despotic rule, while, at the same time, it*

*preserves the traditional prestige of the headman's office." (Evans Pritchard, 1940:50)*::

ጎድፍሬይ ሊንሀርደት(Godfery Lienhardt) በአፍሪካ ኢንስቲትዩት ጆርናል ላይ "Anuak Village Headmen" በሚል ርዕስ ባቀረበው መጣጥፍ ስለ አኝዋዎች መንደር አመሰራረትና የቤት አሰራር ጽፎአል። ጎድፍሬይ እንዳለው የአኝዋዎች ግቢ በሳር የታጠረና በውስጡም ሁለት ወይም ሦስት የተለያዩ ተግባራት ያላቸው የሳር ቤቶች አሉ። ከግቢው መግቢያ በር አካባቢ ማታ ማታ ወንዶች ስለባህላቸው፣ ስለቀን ውሎአቸውና የጋራ ጉዳዮቻቸው የሚያወሩበትና የሚመገቡበት ዊማች የሚባል ከሳር የተሰራ ዳስ አለ። የመንደሩ ሹም (ኳሮ) መኖሪያ ግቢ ያሉ የሳር ቤቶች ደግሞ በመጠንም ሆነ በተግባራቸው ይለያያሉ። የኳሮ መኝታ ቤት "ኡዊኖ"፣ ምግብ ቤቱ "አሙኢ"፣ የሚስቶቹ መኝታ ቤት "ጋን ዶንግ" ይባላል። መሪው ባለጉዳዮችን የሚያነጋግርበትና ምክክር የሚደረግበት "ቡራ" የሚባል ከሳር የተሰራ ዳስና ለጭፈራ ተብሎ የተዘጋጀ ልዩ ስፍራም በግቢው ውስጥ አለ።

የአኝዋ መሪዎችን በተመለከተ ጎድፍሬይ እንዳለው ለመመረጥም ሆነ በስልጣን መቆየት እንዲቻላቸው የህዝቡን ፍላጎት ማሟላት ይጠበቅባቸዋል። የህዝቡን ፍላጎት ማሟላት ካልቻሉና ድክመት ባሳዩ ጊዜ ተቀናቃኞቻቸውና ህዝቡ ተባብሮ ከስልጣን ሊያወርዳቸው ይችላል። ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓቱ በፈቀደው መርህ መሰረት ተግባሩን በትጋት የሚያከናውን መሪ ደግሞ ከተከታዮቹ ክብርና ድጋፍ ያገኛል።

"Natives and Outsiders" በሚል ርዕስ ኩሪሞቶ (kurimoto) በ2001 እ.አ.አ በጻፈው መጣጥፍ አኝዋዎች ለመሀል አገር ኢትዮጵያውያን፣ አጎራባች ቤተሰቦችና የውጭ አገር ዜጎች ያላቸውን አተያይ በተመለከተ የቃል መረጃዎችን አያጣቀሰ ጽፎአል። በጥናቱ እንደተገለጸው አኝዋዎች አኝዋ ያልሆኑ ሌሎች ሰዎችን ሁሉ "ጁሬ" ፣ የእነሱን ያህል ያልጠቆሩ ሌሎች ኢትዮጵያውያንን በተለይ ደግሞ "ጁር ሙታር" ወይም "ጋላ" እያሉ ይጠሩዋቸዋል ሲል ኩሪሞቶ የሚከተለዉን ጽፎአል *"They call all peoples other than Anyuaa jur (pl. jure). A white man is called jure mutar. (white outsider, Gaala (pl. gaale) is another word to mean outsiders. This word gala derived from Galla. This word is however,*

*applied to all highlanders who are considered red in skin and even to the whites as well(2001:6).*

"Capturing Modernity Among the Anyuaa of Western Ethiopia" (2001 እ.አ.አ) በሚለው መጣጥፍ ደግሞ ስለግሎባላይዜሽን ሂደትና ውጤቱ አኙዋዎች ያላቸውን አመለካከት ተመልክቶአል። ይህንን ጥናት ሲያካሂድ አኙዋዎች ስለሥልጣኔ ያላቸውን አተያይ ለመገንዘብ ሁለት ተረቶችን ወስዶ ትንታኔ ሰጥቶባቸዋል። ጊሎና ኡቲዮና በሚለው ሚት (myth) ላይ ባካሄደው ትንታኔ ደግሞ ስልጣኔና ቴክኖሎጂን አኙዋዎች እንደ አዲስ ነገር ሳይሆን ቀደም ሲል ያጡትን መልሰው እንዳገኙት አርገው የማየት አመለካከት አላቸው በማለት የሚከተለውን በትንታኔው አስፍሮአል።

> *Significantly, in ancient times when white men and black men lived together, knowledge and technology symbolized by "iron" (nyuwei) and "paper" (warakata) already existed. When the white men left, they took the knowledge and technology, leaving the black men without them. When white men appeared in Anyuaa land around the turn of the century, they "returned" with the lost iron and paper. In other words during the primordial period, the Anyuaa once had access to modernity, and then lost it. Therefore, modernity, is not something to be gained, but to be regained (Kurimoto, 2001:271).*

ከእነዚህ ሁለት መጣጥፎች በተጨማሪ "Fear and Anger: Female Versus Male Narratives Among the Anyuaa" (2002), " Inter-Ethnic Relation of the Anyuaa in Western Ethiopia" (1992), "People of the River: Subsistence Economy of the Anyuaa of Western Ethiopia" (1996) በሚሉ ርዕሶች ስለአኙዋ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ገጽታዎች የሚያወሱ መጣጥፎችን ኩሪሞቶ ለህትመት አብቅቷል።

ባይለየኝ ጣሰው (1999 እ.አ.አ) " Anyuaa Oral Prose Narratives: Ethnic Genres and Social Functions" በሚል ርዕስ ለድኅረ ምረቃ ማሟያ ባዘጋጀው

ጥናታዊ ጽሑፍ የአኝዋ ቃል ተረኮችን ከይዘታቸው አንጻር "ሊሬ" (Leere)፣ "ዋአ" (Wae) እና "አንጋዴ" (Angade) በሚል አካባቢያዊ ዘውግ መድቦ ማህበራዊ ፋይዳቸውን ተመልክቶአል። የሊሬ ትክክለኛ ትርጉም "a true story", History "wisdom", true old talks of the dead ancestors, *and "Genealogical recitations"* የሚሉትን ይወክላል(ገጽ 64)። ስለነገረ ፍጥረት (Creation and Origin)፣ ታሪካዊ ክስተቶችና የጀግኔ ገድሎችን የሚተርኩ ተረኮች በሊሬ ስር ይመደባሉ። የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ የህይወት ገጽታዎችና ልማዶችን የሚያንጸባርቁ አዝናኝና ልቦለዳዊ ተረኮች ደግሞ ዋአ ይባላሉ። አንጋዴ የሚባሉት ከይዘታቸው አንጻር በምሳሌያዊ ንግግር ርዕስ የተሰጣቸው ተረኮችና ምሳሌያዊ ንግግሮች ናቸው ሲል ባይለየኝ ጽፎአል።

An Anyuaa Myth and its Implication "kwor" በሚል ርዕስ በ2005 እ.አ.አ በጻፈው መጣጥፍ ደግሞ "kwor" የአኝዋ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴ እንደሆነ ገልጾአል *"As practiced in the society,* kwor *is a mechanism employed to handle conflicts such as family feuds, heist, injuries, and disputes over property rights, etc. among the common people (Bayleyegn,* 2005 144)። ከመስክ ባገኘሁት መረጃ መሰረት ግን "**Kwor**" የግጭት መፍቻ ዘዴ ሳይሆን ካሳ ያልከፈለ ወንጀለኛ ወይም የደም ካሳ ያለበት ሰው ማለት ነው። ይህን አስመልክቶ አቶ ኡትታ አዲዉ እንደነገሩኝ "ኩዎር የደም ካሳ ያልከፈለ ባለዕዳ እንደማለት ነዉ። ተገቢውን ካሳ ከፍሎ እርቅ ካልተደረገ ደግሞ ወንጀለኛው ኩዎር አለበት (ካሳ አልከፈለም) በሚል እንደ ባለዕዳ ይቆጠራል። የግጭት መፍቻ ተቋም ወይም ዘዴ ደግሞ ካርሉክ ተብሎ ይጠራል"(ታህሳስ ፥16፥1999)። በባይለየኝ መጣጥፍ እንደተገለጸው ሰው የገደለ ፈጥኖ እጁን ለኚያ (ንጉስ) ወይም ኳር (የቀበሌ ሹም ወይም አስተዳዳሪ) መስጠት አለበት።

የዕርቅ ስነስርዓቱ በሁለት ምዕራፍ የተከፈለ ሲሆን የመጀሪያው ምዕራፍ "**Otocing**" (ኦቶኦቺንግ) እንደሚባል በባይለየኝ ተገልጾአል። በመስክ ተገኝቼ እንዳረጋገጥኩት ግን ይህ ስነስርዓት "**Tocing**" (ቶቺንግ) ተብሎ ነው የሚጠራው። ቶቺንግ ማለት ባለጉዳዮች ፊት ለፊት ለመጀመሪያ ጊዜ ተገናኝተው ችግሩን በሰላማዊ መንገድ (በአገር ሽማግሌዎች) ለመፍታት መስማማታቸውን የሚገልጹበት ስነስርዓት



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ነው። በቶቺንግ ስነስርዓት ላይ ገዳይ በፈጸመው ወንጀል መጸጸቱንና ካሳ ከፍሎ እርቅ እንዲደረግ መፈለጉን ለመግለጽ ሁለት እጁን በልጥ ወይም ገመድ ሽብ ተደርጎ የቶቺንግ ስነስርዓት ከሚደረግበት ቦታ (ቡራ) ይቀርባል። ለሟች ወገኖችም ዋናው ካሳ እስከሚከፈል የደም ማበሻ በሚል መጠነኛ የወግ ዕቃዎችን በካሳ መልክ ይሰጣል። ስለቀ ሟዉ የእርቅ ስነስርዓት ግን የተባለ ነገር የለም።

" Breaking the Cycle of Conflict in Gambella Region" በሚል ርዕስ አብርሃም ሰውነት ከ2003-4 እ.አ.እ በፊት በጋምቤላ ክልል ብሔረሰቦች መካከል ተከስቶ ስለነበረው ግጭትና ግጭቱን ተከትሎ ስለተፈጠረው ማህበራዊ ቀውስ በተመለከተ አንድ መጣጥፍ ጽፎአል። በአብርሃም እንደተገለጸው በክልሉ ነዋሪዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ እያደረሱ ያሉት በአኝዋና ኑዌር ብሔረሰቦች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች ናቸው። በአሁኑ ጊዜ (ጥናቱ በሚጠራው ዘመን) በሁለቱ ብሔረሰቦች መካከል ለግጭቶች መባባስ አንዱ ምክንያት የፖለቲካ ሽኩቻዎችና የስልጣን ቀንቅር ነው። በሁለቱም ወገን የክልሉን ከፍተኛ የስልጣን እርከን ለመቆጣጠር ፍላጎት አለ። ይህ በአኝዋና ኑዌር መካከል በየጊዜው የሚከሰት ግጭት በክልሉ ሰፍረው ባሉ የሱዳን ስደተኞ ላይም ስጋት ፈጥሮአል። ለግጭቶች መከሰት የቀረበ ምክንያቶች ለእርሻና ግጦሽ የሚሆን መሬት ለመቆጣጠር የሚደረግ እሽቅድምድም፣ በ1994 ህዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት ላይ በአኝዋዎችና ኑዌሮች መካከል የተፈጠረ ውዝግብ (በቆጠራው ውጤት መሰረት ከክልሉ ህዝብ ቁጥር ኑዌሮች 40 % ሲሆን አኝዋዎች 27% ናቸው)፣ የሁለቱ ብሔረሰቦች አፍ መፍቻ ቋንቋ በመማር ማስተማር ስራ ላይ ሲውል ኑዌሮች በአኝዋዎች ተጽዕኖ ተደርጎብናል በሚል ቅሬታ መፈጠሩና በደቡብ ሱዳን እየተካሄደ በነበረው የእርስ በእርስ ጦርነት በክልሉ ህገ ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውር መበራከት ናቸው። በመጨረሻም የክልሉ ተወላጆች ግጭቶችን ለመቀነስ ያስችላሉ ብለው ያቀረቡዋቸው የመፍትሄ ሐሳቦች ተካተው ቀርበዋል።ስለባህላዊ አስተዳደር ስርዓትና ተቋማዊ አደረጃጀት፣ የመሪዎች አመራረጥ የበአለ ሹመት ስነስርዓትና ክንዋኔዎች፣ የህዝብና የመሪዎች ግንኙነት፣ ስለግጭት አፈታት ዘዴዎች (ባይለየኝ ስለ ካሳ ከጻፈው ውጭ) እና ተቋማት፣ ባህላዊ አስተዳደሩ በግጭት አፈታት ሂደት ያለውን ሚና፣ ስለተቋማቱ ያለ የህዝብ

መሰባሰትና ከርዕስ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ፍክሎሮች በተመለከተ በቀዳማይ አጥኚዎች ስላልተገለጸ በዚህ ጥናት ምላሽ ይሰጥበታል፡፡

## 2.2 የፖለቲካ ተቋም

ማንኛውም ማህበረሰብ የውስጥ ደህንነቱን የሚቆጣጠርበትና ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር የሚኖረውን ግንኙነት የሚመራበት ወይም ማህበራዊ ደንቦችን (Social orders) የሚጠብቅበትና ማህበራዊ ቀውሶችን (Social disorders) እንዲቀንሱ የሚያደርግበት የፖለቲካ ተቋም እንዳለው ይታወቃል፡፡ ይህን በተመለከተ በ Ember R. Carol, Ember Melvin and Peregrine N. Peter እንደተገለጸው *"political organization is the means through which a society maintains social orders and reduce social disorders" (2003:312).* ማለት ነው፡፡ የፖለቲካ ተቋም ስንል በአጭሩ የአስተዳደር ስርዓቶችን የሚመለከት ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡

ሰዎች በጋራ ተሰባስበው መኖር ከጀመሩ ጊዜ አንስቶ በአንተሮፖሎጂስቶች ተለይተው የሚታወቁ የፖለቲካ ተቋማት Village or band with headman፣ የነገድ (tribe) ፖለቲካ ተቋም፣ ችፍደም(Chiefdom) ፣ ንጉሳዊ አገዛዝና የተለያዩ ቅርጽ ያላቸው መንግስታት (states) የሚባሉት ናቸው፡፡ ቀደምትና ጥንታዊ በሚባለው Village or band with headman የፖለቲካ ተቋም መደበኛ (formal) ስልጣንና እውቅና የተሰጠው መሪም ሆነ ማዕከላዊ መስተዳድር የለም፡፡ ይህን በተመለከተ William Havilland እንዳለው *"since bands are small in size, numbering at most a few hundred people, there is no real need for formal, centralized political system (1995:313)*፡፡ በዚህ የፖለቲካ ተቋም ማዕከላዊ መንግስት ባይኖርም የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን ውክልና የተሰጣቸው የቀበሌ ካውንስሎችና ሌሎች ጥቅም የተደራጁ ማህበራት (Village counciles and associations) አሉ፡፡ በአንዳንድ ማህበረሰቦች ደግሞ አንድን ቀበሌ ወይም ቀበሌዎችን እንዲመራና እንዲያስተባብር ውክልና የሚሰጠው መሪ አለ፡፡ መሪው ስልጣን ላይ የሚቆየው ህዝቡን በአግባቡ ማስተባበርና መምራት እስከቻለ ድረስ ብቻ ነው፡፡



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በነገድ የተደራጀ የፖለቲካ ተቋም ያላቸው ማህበረሰቦች ሁሉም ቢሆን የነገድ መሪ አላቸው:: የነገድ መሪ የሚሆን ሰው በአንዳንድ ማህበረሰቦች በውርስ የሚገኝ፣ በአንዳንዶች ደግሞ ባህሉ ባስቀመጣቸው መስፈርቶች ይመረጣል:: የአንድ ነገድ አባል ተበሊዎች የጋራ ጉዳይ ሲገጥማቸው ተሰባስበው የሚመክሩበት ስርዓትና የቀበሌ ተወካዮች ወይም የአገር ሽማግሌዎች የሚሳተፉበት ካውንስሎችም አላቸው:: ማዕከላዊ (centralized) የሆነ የአስተዳደር ስርዓት ግን የላቸውም:: በየራሳቸው የተደራጁ ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ቡድኖች በጋራ ውህደት ፈጥረው በአንድ የፖለካቲ ተቋም ስር በመደራጀት አንድ የበላይ መሪ (chief) እና በተዋረድ ደግሞ የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ስልጣን የሚሰጣቸው ሹማምንቶች ያሉበት የፖለቲካ ተቋም ከሆነ ደግሞ ችፍደም ይባላል::ይህንን በተመለከተ *William Haviland* እንዳለው *"Chiefdom is a regional polity in which two or more local groups are oreganized under a single ruling individual- the chief- who is at the head of a ranked hierarchy of people "(1997:318).* ከእነዚህ የፖለቲካ ቋሚ ተቋማት መካከል በተወሰነ ደረጃ village or band with headman ባህሪያት በኣር (የቀበሌ ሹም) አስተዳደር ስርዓት የሚንጸባረቅ ቢሆንም የንጉሳዊ ፖለቲካ ተቋም ባህሪያት ግን በኚያ አስተዳደር ስርዓት አይታቹም::

በንጉሳዊ አገዛዝ የፖለቲካ ተቋም ንግስና የአንድን ቤተሰብ የዘር ግንድ ተከትሎ በውርስ የሚገኝ ነው:: በአንዳንድ ማህበረሰቦች ንጉሱ የፈላጭ ቆራጭነት ስልጣን ያለው ሲሆን በአንዳንዶች ደግሞ መንግስታዊና ፖለቲካዊ ተግባራት የሚከናወኑት በሌላ አካል በመሆኑ የንጉሱ ስልጣን የይስሙላ ያህል ነው:: በንጉሳዊ የአገዛዝ ስርዓትና ዛሬ መንግስት በምንለው የፖለቲካ ተቋም ማዕከላዊ መንግስት አለ:: የመንግስት አይነት የተለያየ ቅርጽ ያለው ቢሆንም በዋናነት የራሱ የሆነ ህግ አውጪ፣ ህግ አስፈጻሚ፣ ፍርድ ቤቶች፣ የመከላከያና የፖሊስ ሀይል ያለው፣ የሀገሪቱን ሀብት የሚቆጣጠር፣ ግብር የመሰብሰብ ስልጣን ያለውና ሌሎች ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ተግባራትን በበላይነት የሚመራ አካል ነው::

ባሕሩ ዘውዴ እንዳለው በዘመናዊ የመንግስት ስርዓት በተለይ በአፍሪካ ከመስፋፋቱ የቅኝ ግዛት ዘመን በፊት የተለያዩ ጎሳዎች ይተዳደሩ የነበረው በሀገረሰባዊ

የአስተዳደር ስርዓት ነበር። ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርዓቶች ደግሞ በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ስላላቸው ሰላምና ጸጥታን ለማስፈን የጎላ ድርሻ አላቸው። በቅኝ ግዛት ዘመን ግን በርካታ ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርዓቶች እንዲቀሩ ተደርጓል። ከቅኝ ግዛት በኋላም ቢሆን አፍሪካውያን የራሳቸውን ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርዓት ችላ ብለው በአውሮፓውያን አምሳያ በተቀረጸ የይስሙላ ፓርላሜንታዊ የመንግስት ስርዓትን መከተል መርጠዋል። ይህ ፓርላሜንታዊ የዲሞክራሲ ስርዓት ግን በአፍሪካ ዲሞክራሲንና የኢኮኖሚ ብልጽግናን ሊያመጣ ባለመቻሉ አፍሪካ ዛሬን ድረስ የድህነት፣ የግጭትና አምባገነናዊ መንግስታት ምሳሌ ሆና ትገኛለች በማለት ባህሩ የሚከተለውን በጥናቱ አስፍሯል " *It is argued that for the continent to emerge out of the vicious cycle of military dictatorship and corrupt civilian regime, it has to be re-examine its traditional systems, revitalize them and make them pertinent for contemporary application."(2002:17)*:: በአውሮፓውያኑ አምሳያ የተቀረጸዉ  የይስሙላ ፓርላሜንታዊ ስርአት በአፍሪካ ዲሞክራሲን ማስፈን ካልቻለ  አፍሪካ ከገባችበት አምባገነናዊ ስርዓትና የሙስና አዙሪት ለመውጣት እንዲቻላት በእርግጥም ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርአቶቿን እሴቶች መለስ ብላ መመልከትና ጠቃሚዎቹን ስራ ላይ ማዋል አለባት የሚለዉ ሀሳብ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል

## 2.3 ስለ ግጭት የሚያወሱ ትውሮችና ድፍየናዎች

ማንኛውም ማህበረሰብ በጋራ አብሮ ለመኖር እንዲቻለው የደነገጋቸው ልማዳዊ ሕጎች አሉት። ሕግ በጋራ ተስማምቶ የሚኖር ማህበረሰብ እንደየባህሉ የተስማማባቸውን ማህበራዊ ልማዶች (social norms) እና ደንቦች ጠብቆና አክብሮ ለመኖር ይቻለው ዘንድ ያበጀው ገደብ ነው። እንደዛሬው የተጻፈ ህግና ዘመናዊ ፍርድ ቤቶች ባልነበሩበት ዘመን የተለያዩ ማህበረሰቦች እራሳቸው በተስማሙበትና ባዳበሩት ልማዳዊ ህግ (Customary Law) በመመራት ሰላምና መረጋጋትን በየአካባቢያቸው ለማስከበት ሲጠቀሙበት ኖረዋል። ልማዳዊ ሕጎች በማህበረሰብ ይሁንታን ያገኙ ስለመሆናቸው ሙራዱ አብዶ (Muradu Abedo) ባዘጋጀው የክፍል ውስጥ ጻረኀት (hand out) እንደተገለጸው *"customary Law is secreted by society itself. Every individual is immerged in it. Individuals in a traditional society can*

*not envisage living without observing it. Society as a whole accept it and consider it a necessity"* (2003:33). ዛሬም ቢሆን በተለያዩ ማህበረሰቦች ዘንድ ልማዳዊ ሕጎች እየተሰራባቸው ይገኛሉ። የተጻፈ ህግ ባላቸውም ሆነ በሌላቸው ማህበረተሰቦች ህግ ግጭቶችን የመፍቻ፣ ደንብና ስርዓትን የማስጠበቂያ መሳሪያ ነው። ህግን ለመተርጎምና ግጭቶችን ለመፍታት ማህበረሰቡ ፈቅዶ ያቋቋማቸው ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት በየትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ አሉ። ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚያስችል ህግና ስርዓት ሁሌም ያለ ቢሆንም ይህ ሳይሆን ተርታ ግጭቶች ከቀጠሉ ሀይልን እንደአማራጭ በመጠቀም መፍታት ጥንትም ሆነ ዛሬ ያለ ነው። የግጭት ድፍየናን በተመለከተ ደግሞ በአንዳንድ ምሁራን የተሰጡ ድፍየናዎች እንደሚከተለዉ ቀርቦአል።

ሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መካከል የሚከሰት ቅራኔንና ይህን ተከትሉ የሚፈጠረውን አሉታዊ ግንኙነትን መሰረት በማድረግ ፊሸር ኢታል (Fisher Etal) ስለግጭት የሰጠው ድፍየና *"conflict is a relationship between two or more parties (individual or group) who have or think they have incompatible goals"* (2000:4) የሚል ነው። በዚህ ድፍየና መሰረት ግጭት የሚከሰተው በአንድ ጉዳይ ላይ ሁለት የተለያየ አቋም ወይም ሀሳብ የያዙ ወገኖች ልዩነታቸውን ወደ አንድ የጋራ ግብ ማምጣት ካልቻሉ ነው። በፊሸር ኢታል የተሰጠውን ድፍየና በማይጻረር መልኩ ዱግላስ ፍሬይ (Duglas Fry) የሰጠው ድፍየና ደግሞ ሁለትና ከሀለት በላይ ባሉ ኀራዎች መካከል በሚፈጠር የጥቅም ልዩነት ላይ ያተኩራል። ሁለት የተለያየ ጥቅምና ፍላጎት ያላቸው ወገኖች የየራሳቸውን ጥቅምና ፍላጎት ለማስጠበቅ በሚያደርጉት ትግል ግጭት ሊከሰት ይችላል። በዚህ አንጻር ተመልከቶ ዱግላስ ፍሬይ የሰጠው ድፍየና *"conflict refers to perceived divergent interests between two or more parties"* (1996:237) የሚል ነው። በሁለቱም ምሁራን የተሰጡ ድፍየናዎች የሚያሳዩት ግጭት በሁለትና ከሁለት በላይ በሆኑ ተቃራኒ ሀሳብና ፍላጎት ባላቸው ወገኖች መካከል (ምክንያቱ ቢለያይም) የሚፈጠር ማህበራዊ ክስተት መሆኑን ነው።

ሄንሪክ ዎልፍጋንግ (Heinrich Wolfgang) እንዳለው ደግሞ ግጭት አሉታዊ አንድምታን እንደሚጭር በሁሉም ዘንድ የጋራ ግንዛቤ አለ። ግጭት የተለመደውና



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

እንዲኖር የሚፈለገው ማህበራዊ መስተጋብር የተናጋበት ግንኙነት ቢሆንም የግድ መፈታትና መወገድ አለበት በማለት የሚከተለውን በጽሁፉ አስፍሮዋል "...*conflict must be resolved, and made to disappear. The absence of conflict is perceived as a positive state. According to this perception, 'conflict' is a disruption of normal, desirable social interaction, a 'dysfunctional' state of social relations."* (1997:3)::

እላይ ከተሰጡት ድፍየናዎች በተጨማሪ ከተለያዩ የሙያ መስኮች አንጻር የተሰጡ ድፍየናዎችም አሉ። ለምሳሌ ለህግ ባለሙያ ግጭት በአንድ ጉዳይ ላይ በሚፈጠር አለመግባባት ወይም መብትን (right) ለማስከበር ሲባል በሁለት ወገኖች መካከል የሚደረግ ክርክር ወይም ሙግት ተደርጎ እንደሚታይ በአሰፋ አበበ መጣጥፍ ዉስጥ ተገልጾአል ። በፖለቲካ ሳይንስ ምሁራን ዘንድ ስለግጭት የተሰጠ ድፍየናን በተመለከተ ደግሞ ፕላኖን *(Plano)* አሰፋ እንደሚከተለው ተጠቅሶአል:: "*For political scientist, the term conflict is defined as antagonistic encounters or collisions of interest, principles, ideas, policies or programs that characterize many of the interactions carried on within or between political systems*" ( 2005:52):: በዚህ ድፍየና መሰረት ግጭት በመርሆዎች፣ ሀሳቦች፣ ፖሊሲዎች፣ ወይም ፕሮግራሞች ዙሪያ የተለያየ አቋም ያላቸው ወገኖች የሚያደርጉትን ክርክርና የሀሳብ ፍጭት ብቻ የሚመለከት ነው::

ከላይ የተመለከትኳቸው ድፍየናዎች እንደተጠበቁ ሆነው በእኔ ጥናታዊ ጽሁፍ ለግጭት የሰጠሁት ተግባራዊ ድፍየና (operational definition) ማህበረሰቡ ፈቅዶ ከሚተዳደርበት ደንብና ስርዓት በማፈንገጥ፣ በጥቅምና በሀሳብ ልዩነቶች ምክንያት በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መካከል የሚፈጠር ቅራኔና ይህን ተከትሎ የሚከሰት አሉታዊ ግንኙነት ነው::

## 2.4 ስለ የግጭት መንስኤዎች የሚያወሱ ሐሳቦችና ትውሮች

ግጭት ከሰው ልጅ ታሪክ ጋር ለዘመናት አብሮ የኖረ፣ መንስኤዎቹም የተለያዩ ናቸው። የሀሳብና የጥቅም ልዩነቶችና ውስን የሆነን የተፈጥሮ ሀብት ለመቆጣጠር

የሚያረጉ ትግሎች ለበርካታ ግጭቶች መከሰት ምክንያት ሆነው ይስተዋላሉ። አንዳንድ ምሁራን እንደሚሉት የድህነት መባባስና የህዝብ ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ በመሄዱ የሚፈጠር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና ለግጭቶች መከሰት ምክንያት ናቸው።ይህንን ሀሳብ በሚከተለዉ ጥቅስ ማጠናከር ይቻላል *"From the dawn of human history communities have been competing for the control of resources and dominance. These competitions lead indivduals as well as social, political, economic, and religiuos groups to conflict"* (Assefa, 2005: 50) ። በአንድ አገር ውስጥ የህዝብ ብዛትና የኢኮኖሚ እድገት ካልተጣጣመ ድህነት እየተንሰራፋ መሄዱ አይቀርም። ድህነትና ስራ አጥነት እየጨመረ በሄደ መጠን ደግሞ ሰዎች መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ከህግና የማህበረሰቡን ወግና ልማድ የሚጻረሩ ተግባራትን በመፈጸም ግጭቶች ሊከሰቱ ይችላሉ። በመሬት ይገባኛል፣ በወሰን፣ ስርቆት፣ ዝርፊያ፣ ወዘተ ምክንያት የሚከሰቱ ግጭቶች ዛሬን ድረስ በተለያዩ አካባቢዎች የሚከሰቱ ናቸው። በብሔረሰቦች መካከል ለሚከሰቱ ግጭቶችም ምክንያት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና የድንበር ጥያቄዎች በመዋናንነት ተጠቃሽ ናቸው። የሰው ልጅ የራሱን ጥቅምና ፍላጎት ለማሟላት በሚያደርገው መፍጨርጨር ሁሉም ቢሆን ግጭቶች መከሰታቸው አይቀሬ ነው። ከዚህ በመቀጠል ስለግጭት መንስኤ በአንዳንድ ምሁራን የተሰጡ ሀሳቦችን እንመለከታለን።

ፐርሲ ኮኸን (Percy Cohen) ማህበራዊ ግጭቶችን (social conflicts) አስመልክቶ ባቀረበው ጽሑፍ እንደተገለጸው በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ለማህበሩ የጋራ የሆኑ እሴቶች፣ ልማዶችና ፍላጎቶች አሉ። ሁሉም የማህበሩ አባላት የአጠቃላዩን ማህበረሰብ እሴቶች፣ ልማዶችና ፍላጎቶች መጠበቅና ማክበር ይጠበቅባቸዋል። ይህ ሳይሆን ቀርቶ አንደኛው ወገን ካፈነገጠ ወይም ደንቦቹን ተቀብሎ ከራሱ ጋር ማዋሀድ (internalize) ካልቻለ ግጭቶች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ኮኸን እንዲህ ሲል ጽፏል፣ *"the existence of commonly shared value, norms and interests which they believe held sub-parts. Any deviance behavior or conflict is a result of weakness in the process of socialization"* (1968: 166)

የግጭት መንስኤ የሚመነጨው ሀብትና ስልጣን በጥቂቶች ቁጥጥር ስር ከሆነበት ስርዓት ማህበር ነዉ የሚለዉን የማርክስ ትውር (Theory) በተመለከተ ደግሞ Lewis Coser እንደሚከተለዉ ገልጾታል ::

> *Karl Marx was a leading figure in the debate on conflict theory. His analysis on conflict is rooted in the social system in which both scarce resources and power found under the command of a few. He further remarked that every system was liable to transformation as a result of class conflict rising from within a system. (1967)::*

በማርክስ ትዉር መሰረት ማንኛውም ስርዓተ ማህበር ከራሱ ከስርዓቱ በሚመነጭ የመደብ ግጭት ለለውጥ የተጋለጠ ነው።

## 2.5 ስለግጭት መፍቻ ዘዴዎች የሚያወሱ ሐሳቦችና ትውሮች

የሰው ልጅ የእርስ በእርስ መስተጋብርና ማህበራዊ ግንኙነት ሁለንተናዊ ነው:: ሁለንተዊ ነው መባሉ በማንኛዉም ቦታ፣ ጊዜና ማህበረሰብ ዉስጥ የሚከሰት መሆኑን ለመግለጽ ነው:: ይህ ሁለንተናዊነት ደግሞ ግጭትን ከህብረተሰቡ ውስጥ ጭራሹን ማስወገድ እንደማይቻል ያሳያል። ከዚህ እንፃር ተመልክቶ ሁሴን ጀማ እንዳለው "*it is hardly possible to avoid conflict as long as there is human interaction*" (2005፡ 9):: ይሁን እንጂ ግጭቶችን ጭራሹን ማስወገድ ባይቻልም ማንኛውም ማህበረሰብ በጋራ አብሮ ሲኖር ግጭቶችን ለመፍታት የሚያስችሉትን ዘዴዎች አዳብሯል:: ድርድር፣ ሽምግልናና እርቅ ግጭቶችን ለመፍታት የተለመዱ ዘዴዎች ናቸዉ በፍቃዱ ዘለቀና ዲሬብሳ አባተ "*the usual techniques for confict resolution are usually negotiation, mediation and arbiteration.*"(2005:91) በማለት ገልጸዋል:: ሀገረሰባዊ ችሎቶችና የሀይማኖት አባቶች ምክርም በተለያዩ ማህበረሰቦች የሚዘወተሩ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ናቸው:: በፍርድ ቤት እግባብና የፖሊቲካ ውሳኔዎችም ግጭቶችን መፍታት ጥንትም ሆነ ዛሬ የሚሰራበት ነው:: መፍትሄዎች ሁሉም የተጋጩ ወገኖችን እኩል ያረካሉ ማለት ግን አይቻልም:: አንዳንዴ አንደኛው ወገን ተጎጂ የሚሆንበት ጊዜ አለ:: ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ

ለመፍታት ከተፈለገ የግድ መቻቻል መኖር አለበት፡፡ የፖለቲካ ምክንያት ላላቸው ግጭቶች በተለይ ደግሞ የፖለቲካ ቁርጠኝነትና በስጥቶ መቀበል መርህ ላይ የተመሰረተ ፍላጎት መኖር አለበት ሲል ሁሴን ቀጥሎ የተጠቀሰውን ጽፎአል፤ *"Again, conflict resolution requires political will, tolerance, compromise, and accommodation. It should be based on the will to give and take and not on "Zero-sum game", where the gain of some becomes (or, felt to be) the loss of others."* (Hussein, 2005:24)::

## 2.6 አንዳንድ የአፍሪካ ጎሳዎች ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች

ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች በልዩነት ውስጥ አንድነትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ግጭቶች በባህላዊ እርቅ ስለሚፈቱ የተጋጩ ወገኖች ቅሬታዎቻቸውን ከልብ ፈትተው በሰላም አብሮ የመኖር ባህላቸውንና አንድነታቸዉን ያጠናክራል በማለት ጸጋ እንዳለው (Tsega Endalew) የሚከተለውን ጽፎአል *"The traditional principles pay attention to group unity, reconciling the conflicted individuals or groups and their peaceful re-incorporation into the community"*(2005:146). የአፍሪካ ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች የህዝቡን ባህል መሰረት ያደረጉና ተቀባይነትም ያላቸው ናቸው፡፡ ይህን በተመለከተ ለምሳሌ ያህል በኬንያ፣ ኡጋንዳ፣ ሩዋንዳ፣ ሱዳንና ኢትዮጵያ የተጠኑ የአንዳንድ ጎሳዎች ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች እንደሚከተለው በአጭሩ ቀርበዋል፡፡

በኬንያ የሚኖሩ የማሳይ ጎሳዎች ግጭቶችን በድርድር የሚፈቱበት ዘዴ "Olip" ይባላል፡፡ የአገር ሽማግሌዎች በዛፍ ስር ተቀምጠው በጎሳው የሚከሰቱ ግጭቶችን በolip ስነስርዓት መሰረት የሚፈቱ ሲሆን በግጭቱ ሰው ከሞተ የደረሰው አደጋ ከፍ ያለ መሆኑን ለመግለጽ ስነስርዓቱ የሚከናወነው በደረቀ ዛፍ ስር ነው፡፡ በድብድብ ወይም በጦርነት ጊዜ ደግሞ ማሳይዎች እርጥብ ሳር ቀጥፈው ወደ ላይ በመያዝ ምልክት ካሳዩ ወዲያው ግጭቱ ይቆማል፡፡ ምክንያቱም ማሳይዎች ሁላችንም ከአንድ ማህጸን የወጣን ነን ብለው ስለሚያምኑ እንደሆነ somjc እንዲህ ሲል ገልጾታል *"Whenever there is a fight and a maasai picks up grass the fight*

*stop because they believe they all come from one womb" (Fekade Azeze. Compiler, 2004:5).*

በኡጋንዳ የአቾሊ ጎሳ **"mata-oput"** የሚባል ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴ አላቸው። በMata-oput ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የአገር ሽማግሌዎች የተለመደ ነው። እርቅ ሲደረግ በስነስርዓቱ ላይ በሬ ታርዶ ደሙን የእውነት አምላክ ወደሚለምኑት አምላካቸውና የአገር ሽማግሌዎች እንደሚረጩ ፈቃደ አዘዘ ባዘጋጀው ፕሬስ ውስጥ እንደሚከተለው ተገልጾአል *"An animal is sacrificed and the blood sprinkled on the shrine of the God of truth and the reconcile" (Fekade Azeze, 2004:6).* ታራቂዎቹም በአንድ እቃ እንዲበሉና እንዲጠጡ ይደረጋል። በአንድ ዕቃ መብላትና መጠጣት ከልብ መታረቃቸውን መግለጫ ትዕምርት እንደሆነም ተገልጾአል።

በሩዋንዳ የባኒያሩዋንዳ ጎሳዎች ዘንድ **"Agacaca"** የሚባለው ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴ ዛሬን ድረስ በስራ ላይ እየዋለ ይገኛል። በግለሰቦችም ሆነ በቡድን መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት በመጀመሪያ ጉዳዩ ለአገር ሽማግሌዎች ቀርቦ ይታያል። በመቀጠልም የተጋጩ ወገኖች የአገር ሽማግሌዎች ፊት ቀርበው ክርክርና ድርድር ያካሂዳሉ ወይም የእምነት ክህደት ቃላቸውን እንዲሰጡ ይደረጋል። ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘም የበደለውን ይቅርታ ጠይቆ እርቅ ይደረጋል።የሩዋንዳ መንግስትም በ1994 እ.ኤ.አ የዘር ማጥፋት ወንጀል የተከሰሱ አንዳንድ ሰዎችን ጉዳይ በAgacaca እንዲታይ ፈቅዷል።

በደቡብ ሱዳን የሚገኙት የኑዌርና ዲንካ ብሔረሰቦች ግጭቶችን የሚፈቱት በውይይት ነው። በውይይቱ ላይ የአገር ሽማግሌዎች፣ የሀገረሰባዊ ሀይማኖት ተሳውስትና ተረት ተራኪዎች ይሳተፋሉ። ተረት ተራኪዎች የሚሳተፉበት ምክንያት ከተከሰተው ግጭት ጋር የተያያዙ ተረቶችን በመተረክ የሞራል ትምህርት ለማስተላለፍና ውይይቱና የዕርቅ ስርዓቱ ከመጀመሩ በፊት ተረቱን እንደ መግቢያ አርጎ ለመጠቀም ነው። ይህን በተመለከተ በፀጋ መጣጥፍ ውስጥ እንደሚከተለው ተገልጾአል። *" The main aim of the story told by the elders is to highlight the moral teaching of the stories, in relation to the conflict and as an*

introduction to the discussions." *Ayub (as quoted by Tesega, 2005: 147).*
በስንሰርጎት መጀመሪያና መጨረሻ ቀን ላይ ደግሞ ነጭ ኮርማ በሬ ይታረዳል፡፡ ነጭ ቀለም በሁሉም ብሔረሰቦች እንደ የሰላም ትዕምርት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

በኢትዮጵያ የኦሮሞ ብሔር ከሚዘወተሩ ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች "ኢላፊ ኢላሜ"፣ "ጃርሱማ"፣ "ዋቃፌና" እና የገዳ ስርዓት ግጭት መፍቻ ተጠቃሾች እንደሆኑ ከሚከተለዉ ጥቅስ መረዳት ይቻላል፡፡

> *The Oromo people use different indigenous mechanisms to prevent, manage, and resolve conflicts. These mechanisms include, but are not limited: 1. Ilafi Ilamee — negotiation of parties in the conflict without the involvement of a third party. 2. Jarsuma system— traditional reconciliation system adminstered by community elders. 3. Gada system— a traditional Oromo political system and 4. Waqefenna system— traditional Oromo religious system (Assefa, 2005:54).*

በኢላፊ ኢላሜ የተጋጩ ወገኖች በአገር ሽማግሌዎች አማካኝነት ፊት ለፊት ተገናኝተው በመደራደርና በመቻቻል ከተስማሙ በኋላ አጥፊው የበደለውን ይቅርታ ይጠይቃል፡፡ ከኦሮሞ ግጭት መከላከያና መፍቻ ዘዴዎች ሁሉ በስፋት የሚሰራበትና የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው የሚታመንበት ጃርሱማ እንደሆነ በአሰፋ ተገልጾአል::

በአሰፋ መጣጥፍ የቀረበው ሦስተኛው አይነት የግጭት መፍቻ ተቋም ዋቃፌና ይባላል፡፡ ዋቃፌና መሰረት ያደረገው የኦሮሞ ሀገረሰባዊ ሀይማኖትን ነው፡፡ የዚህ ተቋም መሪዎች በጥቅሉ «ቃሉ» በመባል ይታወቃሉ፡፡ በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ ኦሮሞዎች የየራሳቸው ቃሉ ያላቸው ሲሆን መቀመጫውን ባሌ ያደረገው ዋና ቃሉ «አባ ሙዳ» ይባላል፡፡ በአባ ሙዳ የሚሾም የአካባቢ ቃሉ ደግሞ «ጨባ» እየተባለ እንደሚጠራ በአሰፋ ተገልጾአል፡፡ "*In the earlier time, all Oromo have one chief qallu called Abba* muda and a depuaty qallu called chaba ('representative'). The Abba muda gives power to chabas through delegation. All chabas from all

parts of Oromo land make pilgrimage to the site of Abba muda in Bale…" (Assefa,2005:64). አባ ሙዳ በኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው በመሆኑ በአመት አንዴ ለአባ ሙዳ ክብር ሲባል ክብረበአል ይዘጋጃል። በዚህ ክብረበአል ላይ የኦሮሞ አባ ገዳዎችና የቤተዘመድ መሪዎች (Kinship leaders) ተሰባስበው በጋራ ጉዳያቸው ላይ ይመክራሉ። በዋቃፈና የሚወሰኑ ውሳኔዎችን ያላከበረ እርግማን ይደርስበታል። የዋቃፈና መሪዎችም መለኮታዊ ሀይል አላቸው የሚል እምነት ስላለ በእነሱ የተረገመ አደጋ ይደርስበታል ተብሎ ይታመናል።

ዘመናትን ባስቆጠረው የገዳ ስርዓት ውስጥም እራሱን የቻለ የግጭት መከላከያና መፍቻ ዘዴ አለ። በገዳ ስርዓት ደንብ መሰረት በእያንዳንዱ የገዳ ዘመን (8 አመት) አዳዲስ ዳኞች ይመረጣሉ። የዳኞች ቁጥር እንደ ግጭቱ አፈጻጸምና የወንጀል መጠን ይለያያል። ለከፍተኛ ግጭት ወይም ወንጀል ከሚሰየሙ 12 ዳኞች አምስቱ በከሳሽ አራቱ ደግሞ በተከሳሽ ይመረጣሉ። ወንጀሉ አነስተኛ ከሆነ ደግሞ ከገዳው ዳኞች ጋር እንዲሰሩ ከሳሽና ተከሳሽ ከአንድ በላይ ሰው መወከል አይችሉም። ከከሳሽና ተከሳሽ ጋር ዝምድና ወይም ጠብ ያለውን ሰው መወከልም አይቻልም። የዳኞች ቁጥር 12 ከሆነ «[illegible]» አምስት ከሆነ ደግሞ «ሸንቻ» ይባላል ሲል አሰፋ ተጥሉ [illegible] ይገልጻል።

*The procedure of the proceeding of the Gada court involves that the plaintiff has the right to select five elders who will investgate the case along with the three juges of the Gada system. The defendant also has the right to select four elders on his part. …The nine elders, called salge ('the nine') and the three juges together (twelve persons) constiute the full bench of court. This bebch is called Dhaddacha or Sanacha (2005:57).*

ሰው ገድሎ ጳደቻ የቀረበ በቦሬና ኦሮሞ 30 ከብቶች በከረዩ ኦሮሞ ደግሞ 35 ከብቶች ወይም 15,000 ብር ካሳ ይከፍላል። በገዳ የዳኝነት ስርዓት የሚሳተፉት ወንዶች ብቻ ቢሆኑም ባል በሚስት ላይ በሚያደርሰው በደል የሚከሰት ግጭት የሚዳኘው በሴቶች እንደሆነ አሰፋ ገልጾአል።

በአብአላ ወረዳ አፋሮች ደግሞ ግጭቶች የሚፈቱት «መዳ» በሚባል ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴና ልማዳዊ ሕግ መሰረት መሆኑን ቀለመወርቅ ተፈራና ምትኩ ሀይሌ "Indigenous institutions of conflict resolution among the Ab ala Afar of north-eastern Ethiopia" በሚል ርዕስ በ2005 ባዘጋጁት መጣጥፍ (ገጽ 175) ገልጸዋል። በግጭቱ የደረሰው ጉዳት በሽማግሌዎች ታይቶ ለተጎጂው ካሳ መክፈል በመዳ ደንብ መሰረት ግዴታ ነው። ለምሳሌ የአጥንት ስብራት ከደረሰ በመጀመሪያ ለአጥንት መጠገኛ ተብሎ ሁለት ፍየሎች ይሰጣሉ። በመቀጠልም ጉዳዩ በአገር ሽማግሌዎች ተጣርቶ «ሞሩስ» የሚባል እስከ አንድ ግመል የሚደርስ ካሳ ይከፈላል። በጥናት አቅራቢዎች (ገጽ 176-77) እንደተገለጸዉ ሞት ያስከተለ ግጭት ከተፈጠረ ደግሞ በመጀመሪያ «ሚካበን» የሚባሉ የእጥቢያ ዳኞች ከጎሳ መሪዎች ጋር በመሆን ላም ወይም ግመል ታርዶ ስብሰባ ይቀመጣሉ። እርድ የሚደረገው ግጭቱ በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ሂደት መጀመሩን ለማብሰር ነው። ከዚህ ስነስርዓት በኋላ እስከ አርባ ቀን በሚፈጅ ጊዜ ውስጥ ስለ ግጭቱ ሁኔታ በዳኞች ይጣራል። የማጣራቱ ስራ እንደተጠናቀቀ ህዝባዊ ስብሰባ ተደርጎ የዳኞች ሪፖርት ይቀርብና ገዳይ እስከ አርባ የሚደርስ ግመሎችን ካሳ እንዲከፍል ይወሰንበታል። የሟች ወገኖችም ከገዳይ ወገን ጋር እርቅ መፈለጋቸውን በመሀላ ያረጋግጣሉ። ካሳው በሚከፈልበት ቀን የሀይማኖት አባቶችና የአካባቢው ሰዎች በተገኙበት የርክክብ ስነስርዓት ይዘጋጃል።።። ስነስርዓቱ የሚያበቃው የሀይማኖት አባቶች ከቁርአን እያጣቀሱ በሚያደርጉት ንግግርና ምርቃት እንደሆነ በአሰፋ ተገልጸዋል።

ግጭቱ የተፈጠረው በጎሳዎች መካከል ከሆነ ደግሞ ችግሩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት በአስቸኳይ «መባሉ» የሚባል ህዝባዊ ስብሰባ ተጠርቶ በጉዳዩ ዙሪያ ውይይት ይደረጋል። በዚህ ስብሰባ ላይ የሁለቱም ወገን የጎሳ መሪዎችና ነዋሪዎች ይሳተፋሉ። ስለሁኔታው ማጣራት የሚደረገው ከሁለቱም ወገን በተውጣጡ የአገር ሽማግሌዎች ነው። በመባሉ ስብሰባ ላይ ውይይት ተደርጎ የህዝብ አስተያየትና ምስክርነት ከተሰማ በኋላ በአገር ሽማግሌዎች የጋራ ስምምነት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ካሳ ይከፍላል። ይህ ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴ «ሞት» እየተባለ ይጠራል።



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

አፋሮችና አጎራባቾቻቸው የዋጀራት ትግሬዎች ግጭቶችን በጋራ የሚፈቱበት «ገርብ» (Gereb) የሚባል ሀገረሰባዊ ተቋም እንዳላቸውም በቀለመወርቅና ምትኩ መጣጥፍ ዉስጥ (ገጽ185) ተገልጿል። የገርብ ሰብሳቢ ዳኛ (አቦ ገርብ) የሚመረጠው በህዝብ ነው። በገርብ ደንብ መሰረት ሰው የተገደለበት ወገን ስለሁኔታው በመጀመሪያ ለአቦ ገርብ ማሳወቅ አለበት። አቦ ገርብም የሁለቱንም ወገን ስብሰባ ጠርቶ ችግሩ በሰላማዊ መንገድ የሚፈታበትን ሁኔታ ያመቻቻል። ገዳይ በድርጊቱ መጸጸቱንና በህግ ቁጥጥር ስር መሆኑን ለመግለጽ ደግሞ ጥቁር ጨርቅ አገልድሞና በአንገቱ ማጭድ ይዞ ከተሰበሰበው ህዝብ ፊት ይቀርብና በደረቱ እንዲተኛ ይደረጋል። በመቀጠልም ዳኛው ሰውየው እሁኑኑ እንዲገደል ይፈልጉ እንደሆን የሟችን ወገን ይጠይቃሉ። የሟች ወገን ግን ነገ በልጆቻችን ይደርሳል በሚል ፍራቻ ሰውየው ይገደል አይሉም። በዚህ ስነስርዓት ላይ በሬ ታርዶ ግብዣ ይደረጋል። ለሟች ወገንም ገዳይ ካሳ እንዲከፍል የጊዜ ገደብ ይሰጠዋል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

## 3. የመንግስታትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎችና ልማዳዊ ህጎች በኢትዮጵያ ህጎች ስለመካተታቸው የተደረገ ቅኝት

በእዚህ ክፍል ስር የቀረቡ ዋና ዋና ርዕስ ገዳዮች የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ፣ የአፍሪካ ሕብረት (የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን ጨምሮ) ፣ አንዳንድ የአፍሪካ ቀጠናዊ መንግስታትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ግጭቶችን ለመፍታት የሚከተለዋቸውን ዘዴዎች ፣ የኢትዮጵያ ሕገመንግስት ፣ የፍትሐብሄርና የወንጀለኛ መቅጫ ሕጎች ልማዳዊ ሕጎችን ስለተመለከቱበት ሁኔታ ላይ የተደረገ ቅኝት እንዲሁም የአኝዋ ልማዳዊ ሕጎች ናቸው።

### 3.1 የተባበሩት መንግስታት ድርጅት

በ1945 (እ.አ.አ) የተመሰረተው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከዋና ዋና አላማዎቹ አንዱ በአባል አገራት መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ማድረግ ነው። አባል አገራቱም ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት፣ ሰብአዊ መብቶችን ለማክበር ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍትህን ለማስፈን ፣ በመቻቻልና በሰላም ለመኖር መስማማታቸዉን በድርጅቱ ቻርተር አንቀጽ አንድ ላይ ተገልጾአል። በአገሮች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችንና አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት እንዲቻለውም በስሩ የፀጥታው ምክር ቤትንና አለም አቀፍ የፍርድ ቤት ተቋምን አቋቁሞአል። በድርጅቱ ቻርተር አንቀጽ 39፣ 40 እና 41 መሠረት የጸጥታው ምክር ቤት በአገሮች መካከል የሚነሱ ግጭቶችን ፣ የግዛት ሉአላዊነትን በመጣስ የሚደረጉ ወረራዎችን ፣ የአለምን ሰላምና ደህንነት የሚያደፈርሱ ማናቸውንም ተግባራት እየተከታተለ የመፍትሄ ሀሳቦችን ማቅረብ ወይም ሊወሰዱ የሚገባቸውን የመፍትሄ እርምጃዎች የመወሰን ስልጣን አለው። በድርጅቱ ቻርተር አንቀጽ 33 ላይ እንደተገለጸው በአገሮች መካከል የሚከሰቱ ማናቸውም ግጭቶች በመጀመሪያ መፍትሄ

ሊፈለጉላቸው የሚገባው በድርድር፣ በሽምግልናና በፍርድ ቤት አግባብ መሆን አለበት።

ከ1945-1989 እ.ኤ.አ የተባበሩት መንግስታት በርካታ ሰላም የማስጠበቅ ተግባራትን አከናውኗል። በአገሮች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶች እየቀነሱ ቢመጡም በርካታ የእርስ በእርስ ጦርነቶች ግን እየተካሄዱ ይገኛሉ። የተባበሩት መንግስታት ከተቋቋመ ጀምሮ በበርካታ የሰላም ማስጠበቅ ተግባራት መሳተፉን በተመለከተ ሄንሪክ ዎልፍጋንግ ጁንን (Jun) ጠቅሶ እንደሚከተለው ገልጾታል።

> *Between 1945 and 1989, the UN was involved in 15 peace making operations, while the number of armed conflicts between states has decreased, more and more states are torn by intra-societal conflicts. According to some studies, 83 percent of all war or armed conflicts since 1945 were inter-state conflicts( Jun as quoted in Heinrich Wolfgang, 1997:1).*

የተባበሩት መንግስታት በአገራት መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታትና ሰላምን ለማስፈን የተለያዩ ጥረቶችን ቢያደርግም በተፈለገው መጠንና ፍጥነት ችግሮችን መፍታት አልቻለም እየተባለ ይወቀሳል። ድርጅቱ ከሚወቀስባቸው ድክመቶች አንዱ ግጭቶች ተባብሰው ወደ ጦርነትና ብጥብጥ ከመሸጋገራቸው በፊት ፈጥኖ የመፍትሄ እርምጃዎችን ሲወስድ አለመታየቱ ተጠቃሽ ነው። ይህን የተባበሩት መንግስታት ድክመት በሚከተለው ጥቅስ ማረጋገጥ ይቻላል። *"Organizations such as the UN often lack efficiency because of bureaucracy or political imposed limitations" (Monique Mekenkamp, Paul van Tongeren and Hansvan de Veen (eds.), 1999:51).* ግጭቶች ከተከሰቱ በኋላ መፍትሄ ለመስጠት የሚያደርገው ጥረትም ዘገምተኛ ነው እየተባለ ይታማል። በሶማሊያ የተከሰተውን የእርስ በእርስ ጦርነት ማስቆም አለመቻሉን ለዚህ አባባል በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። ይህን የሶማሊ ጉዳይ በተመለከተ የተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሐፊ ልዩ መልዕክተኛ የነበሩት (1992 እ.ኤ.አ) አምባሳደር መሐመድ ሳህኑን የተባበሩት መንግስታት ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎች



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

የሶማሊያን ግጭት ሊያስቆሙ አልቻሉም ሲሉ የሰጡት አስተያየት በሄንሪክ ቮልፍ ጋንግ እንደሚከተለዉ ተጠቅሶአል። *"...He was convinced that the traditional strategies and policies of the UN could not work in the Somali conte" (Hienrich Wolfgang, 1997:XV).*

## 3.2 የአፍሪካ አንድነት ድርጅት

በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተር አንቀጽ ሁለት ተራ ቁጥር አንድ እንደተገለጸው የተቋቋመበት ዋና አላማ በአፍሪካ አገሮች መካከል አንድነትን፣ ወዳጅነትንና ትብብርን ማጠናከር፣ የህዝቡን ኑሮ ማሻሻል፣ የአባል አገራቱን ሉአላዊ የግዛት አንድነትና ነጻነታቸውን ማስከበር፣ የአፍሪካ አገሮችን ከቅኝ ግዛት ማላቀቅ፣ አለም አቀፍ ትብብሮችን ማጠናከር፣ የተባበሩት መንግስታትን ቻርተርና አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን ማክበር የሚሉ ናቸው። በቻርተሩ አንቀጽ ሶስት ተራ ቁጥር አራት መሰረት በአገራት መካከል የሚከሰቱ ማናቸውም ግጭቶች መፈታት ያለባቸው በሰላማዊ መንገድ መሆን እንዳለበት ተደንግጎአል። ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀምባቸው ዘዴዎችም ግልግል (Mediation)፣ እርቅ (conciliation) እና ሽምግልና (arbitration) መሆናቸውን በቻርተሩ አንቀጽ ሰባት ተራ ቁጥር 4 ላይ ተደንግጓል።

## 3.3 የአፍሪካ ሕብረት

በ2000 ዓ.ም እ.ኤ.አ የተቋቋመው የአፍሪካ ሕብረት ከዋና ዋና ተግባራቱ መካከል በአፍሪካ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሱ የመጡ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ነው። በህብረቱ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ ሶስት እንደተገለጸው ዋና ዋና አላማዎቹ 1. የአባል አገራቱን የድንበር ወሰን ማክበር 2. በአገሮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት 3. በአገሮች መካከል የዘር ማጥፋትና የሰብአዊ መብት ረገጣዎች ሲከሰቱ ጣልቃ መግባት 4. በሰላም አብሮ የመኖር መርህን ማዳበር 5. የአባል አገሮችን ሰላምና ደህንነት ማክበር 6. ዲሞክራሲያዊ መርሆዎችን፣ ሰብአዊ መብቶችን፣ የህግ የበላይነትንና መልካም አስተዳደርን ማጠናከር የሚሉ ናቸው። በአፍሪካ ህብረት መርህ መሰረት ማናቸውም ግጭቶች መፈታት ያለባቸው ሰላማዊ



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

በሆነ የጋራ ስምምነት፣ በእርቅና የፍርድ ቤት አግባብ ብቻ ነው። በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ሀይል መጠቀምን ይቃወማል።

## 3.4 የአፍሪካ ቀጠናዊ መንግስታትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

በኢኮኖሚያዊና የንግድ ጉዳይ ዙሪያ በጋራ ተባብረው ለመስራት ከተቋቋሙ የአፍሪካ ቀጠናዊ መንግስታት ድርጅቶች (African Regional States) መካከል የምዕራብ አፍሪካ መንግስታት የኢኮኖሚ ማህበረሰብ (ECOWAS)፣ የምስራቅ አፍሪካ በይነ መንግስታት(IGAD) እና የደቡባዊ አፍሪካ ልማት ማህበረሰብ(SADC) በየቀጠናዎቻቸው ግጭቶች እንዳይከሰቱ ቀድሞ ለመከላከል፣ ከተከሰቱም በሰላማዊ መንገድ ለመፍታትና ግጭቶች በተከሰቱባቸው አገሮችም የሰላም አስጠባቂ ሀይል ለማሰማራት የሚያስችላቸውን ስምምነት አድርገዋል። ይሁን እንጂ እነዚህ ድርጅቶችም ቢሆኑ የረባ ውጤት ሲያስመዘግቡ አይታዩም በሚል ይወቀሳሉ "*Sub-regional organizations did not necessarily respond to brewing disputes in their area that could escalate in to violence, any earlier than other types of third parties" (Monique Mekenkamp, Paul van Tongeren and Hans van de Veen,1999:59).*

በርካታ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም ሰላማዊ የግጭት መፍትሔዎችን በማበረታታትና በአፍሪካ ሰላምና ዲሞክራሲ እንዲሰፍን በማስተማርና ህዝቡን በማንቃት ስራ ላይ ትኩረት አድርገው ይንቀሳቀሳሉ። ይህንን በተመለከተ "Searching for Peace in Africa: An Overview of Conflict Prevention and Management Activities" በሚል ርዕስ Monique Mekenkap, Paul van Tongeren, and Hans van de Veen ባደቱት (edit) መጽሐፍ ዉስጥ ከተመለከትኳቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መካከል የሚከተሉት ለምሳሌ ያህል ቀርበዋል።

West Africa Network for Peac Building (WANEP) በምዕራብ አፍሪካ አካባቢ ሰላም፣ ፀጥታና የፖለቲካ መረጋጋት እንዲሰፍን ከሚሰሩ ድርጅቶች አንዱ ነው። ከዚህ ጎን ለጎን ግጭትን ለማስወገድና ሰላምን ለመገንባት የሚሰሩ ድርጅቶችን



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

እያሰባሰበ የልምድ ልውውጥና የጋራ ግንባር እንዲፈጥሩ እየሰራ ይገኛል። African Center for the Constructive Resolution of Disputes (ACCORD) የተባለው መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅትም በአፍሪካ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ የመፍታትና ሰላምን የመገንባት ባህል እንዲዳብር ህብረተሰቡን በማስተማር ላይ አትኩሮ ይንቀሳቀሳል። ከድርጅቱ ፖሊሲ አንዱ በአፍሪካ የሚከሰቱ ግጭቶችን በአፍሪካውያን እንዲፈቱ ማበረታታት እንደሆነ ከሚከተለው ጥቅስ መረዳት ይቻላል "ACCORD based in south Africa, seek to encourage and further constructive resolution of conflicts by African's people" [Monique Mekenkanp, Paul van Tongeren and Hans van de Veen(eds)., 1999 :47)። በተመሳሳይ ሁኔታ Nairobi Peac Group እና Inter African Group ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ፣ ዲሞክራሲ እንዲስፍንና የሰላም ባህል ግንባታ እንዲጠናከር ህብረተሰቡን በማስተማር፣ በመቀስቀስና ጥናትና ምርምሮችን በማድረግ ስራ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ።

ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱና በአፍሪካ ሰላምና የዲሞክራሲ ባሕል እንዲጠናከር ትኩረት አድርገው ከሚንቀሳቀሱ አንዳንድ የተመለከትኳቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መካከል Search for Common Ground የተባለ ድርጅት ግጭቶችን ለመፍታት ህገሰባዊ ዘዴዎችን ይጠቀማል። Life and Peace የተባለው ድርጅትም በአፍሪካ ቀንድ ፕሮግራሙ ተራ ቁጥር አንድና ሁለት ላይ እንደተገለጸው በምስራቅ አፍሪካ ቀጣይነት ያለው ሰላምን ማግኘት የሚቻለው በማህበራዊና ባህላዊ አውድ ውስጥ ነው ሲል የሚከተለውን በደንቡ አስፍሯል። "That sustaninable peace can only be found within the local social and cultural context...." (Hienrih Wolfgang, 1997:xi). ይህ ድርጅት ሰላምን የማስፈን ስራ መጀመር ያለበት ከታችኛው ማህበረሰብ ጀምሮ በአጠቃላይ ህብረተሰቡን በማሳተፍ የሰላም ባህልን በመገንባት ነው ብሎ ያምናል።

## 3.5 የኢትዮጵያ ሕጎች

በእዚህ ንኡስ ርዕስ ስር የቀረቡት ስለኢትዮጵያ የፍትሐብሔርና ወንጀለኛ መቅጫ ሕጎችና በእነዚህ ሕጎች ውስጥ ልማዳዊ ሕጎች ስለመካተታቸው የተደረገ አጭር ቅኝት እንዲሁም ስለእነኛ ልማዳዊ ሕጎች ነው።



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

### 3.5.1 የፍትሐብሔር ሕግ

በ1960 እ.ኤ.አ በወጣው የኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሕግ ውስጥ ልማዳዊ ሕጎችን ለማካተት የተደረገውን ሙከራ በተመለከተ George krezeczunowicz እንዳለው "*A large core of Ethiopian customary law is preserved through its incorporation into the civil code. In this way formulated custom became general state law(1965:429).* ይሁን እንጂ እነዚህ የተካተቱ ልማዳዊ ሕጎች በተለያዩ ቤሔር ቤሔረሰቦች ዘንድ የሚሰራባቸውን ልማዳዊ ሕጎች የሚወክሉ መሆናቸው አይታዩም። ምክንያቱም ልማዳዊ ሕጎቹን ለማካተት እንዱ መመዘኛ በደጋው በሚገኘን ኢትዮጵያ በአብዛኛው የሚሰራባቸው ከሆኑ ብቻ መሆኑ ነው። በአጠቃላይ ልማዳዊ ሕጎችን ለማካተት የቀረቡ መስፈርቶች ጠቃሚ ከሆኑ ግብረገቦችና ሀይማኖታዊ አድገቶችና ከፍትሐነገስት ጋር የማይጻረሩ የሚሉት ነጥቦች እንደ መመዘኛ መታየታቸውን ሙራዱ አብዶ (Muradu Abedo) ባዘጋጀው የኮርስ ውስጥ ጹሑፍ (Hand-out) እንደሚከተለው ተገልጾአል።

> *Incorporate customary rules if those rules met the following criteria. Incorporation of custom took place when the custom was sufficiently general as to be practiced by at least a majority of the highland population, when the custom was not repugnant to the natural justice which permeated the altimate old authority the Fetha Negast, when custom was not contrary to imperatives of social and economic progress and when the custom was sufficiently clear and articulate as to be capable of definite in civil law term ( 2003:18).*

ከላይ በተጠቀሰው መመዘኛ መሰረት ቢሆንም እንደተፈለገው ልማዳዊ ሕጎችን ለማካተት የሚያስችል ሁኔታ አልነበረም። ለዚህ እንዱ ምክንያት የኢትዮጵያ ልማዳዊ ሀጎች በአግባቡ ተሰባስበው አለመጠናታቸው እንደሆነ ሙራዱ እንዲህ በማለት ገልጾታል። "*Generally, explicit incorporation of Ethiopian customary practices in the codes was not possible because no systematic survey of*



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

customary law had *even been attempted in Ethiopia (Muradu, 2003,19).* በተቀመጠው መመዘኛ መሰረት የተወሰኑ ልማዳዊ ሕጎች እንዲካተቱ ከተደረገ በኋላ በፍትሐብሔር ሕጉ ከተደነገገው ውጭ ከዚህ በፊት ይሰራባቸው የነበሩ ልማዳዊ ህጎች በዚህ ህግ ስለተተኩ የተሻሩ ስለመሆናቸው በአንቀጽ 21 ቁጥር 3347 ላይ ተገልጾአል። በአገሪቱ ካሉ ብሔር ብሔረሰቦች ብዛት አንጻር ስናየው እነዚህ ተካተዋል የተባሉ ልማዳዊ ህጎች የሁሉንም ፍላጎትና ጥቅም ባገናዘበ መልኩ ተካተዋል ማለት አይቻልም።

የፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ ስምንት በአገሬው ልማድ መሰረት ግጭቶች በግልግል፣ በእርቅ እንዲፈቱ ማድረግን ይፈቅዳል። አንፃራዊ በሆነ መልኩ ሲታይ በሕጉ የተካተቱ ልማዳዊ ሕጎች የቤተሰብ፣ የውርስ፣ የጋብቻና የጋራ መጠቀሚያ መሬቶችን የሚመለከቱ ሆነው እንደሚስተዋሉ George Krzeczunowicz እንዲህ ሲል ገልጾታል "*On the contrary, in the traditionally cultivated branches of law concerning family, land and succession, many fitting general customs have been preserved through their inclusion in the code"(P.430).* በፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 577 (2)፣ 580፣606፣632፣(1)፣ 633 መሰረት የልማድ ጋብቻዎች ዕውቅና ተሰጥቷቸዋል። በባልና ሚስት መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን በሽምግልና መፍታት እንደሚቻል በቁጥር624፣ 630፣641(2)፣ 676፣678 ላይ ተደንግጓል። ለመጋባት ተስማምተው ውሉን ባፈረሰ ወገን ላይ ደግሞ በቁጥር 573 በተገለጸው መሰረት በአገሬው ልማድ ካሳ እንዲከፍል ሕጉ ያስገድዳል። ከጋብቻ በፊት ክብረ ንጽህናዋን የተደፈረች ሴት ጉዳይ በአገር ሽማግሌዎች ወይም በቤተዘመድ ዳኞች ታይቶ ካሳ እንዲከፈላት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2116፣2117 እና 2119 ግዴታን ይጥላል። በጋራ መጠቀሚያ መሬቶችና በተጠቃሚዎች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን በተመለከተ ደግሞ በቁጥር 1489፣ 1490፣1491፣ 1997፣2983 (2)፣ 2990 (1ና2)፣ 2997፣ (2)፣ 3006፣ 3113 (3) ላይ እንደተገለጸው በአገሬው ልማድ መሰረት መፍታት ይቻላል።

በ1987 (እ.ኢ.አ) በወጣው የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት አንቀጽ 34 ተራ ቁጥር 4 ላይ እንደተገለጸው በሀይማኖትና በባህል የህግ ስርዓቶች ላይ ተመስርተው ለሚፈጸሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ሕግ ሊወጣ እንደሚችል ይፈቅዳል። በዚህ አንቀጽ ተራ ቁጥር 5 መሰረት የግልና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ ተከራካሪዎች ከፈለጉ በሀይማኖት ወይም በባህል ህጎች መዳኘትን አይከለክልም። የባህል ፍርድ ቤቶችም ሊቋቋሙ ወይም



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ስልጣን ሊሰጣቸው እንደሚችል በተራ ቁጥር 5 ላይ ተገልጿል። በአንቀጽ 62 ተራ ቁጥር 6 መሰረት ደግሞ በክልሎች መካከል ለሚነሱ አለመግባባቶች መፍትሄ የሚሰጠው በፌደሬሽን ምክር ቤት ነው።

በክልሎች ውስጥ የሚከሰቱ የብሔረሰብ ግጭቶችን ለመፍታት መንግስት ጣልቃ ሲገባ የሚታየዉ ግን በፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በኩል ነው። መስሪያ ቤቱ ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን እየተጠቀመባቸው እንዳለም የዲሞክራታይዜሽን መምሪያ ተጠሪነቱ መምሪያ ኃላፊ የሆኑት አቶ ተስፋስላሴ መዝገብ ነግረውኛል። በተለይ በአፋር፣ በሶማሌ፣ ጋምቤላና አንዳንድ የኦሮሚያ ክልሎች የተከሰቱ ግጭቶችን ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን በመጠቀም ማኔጅ ማድረግ መቻሉን አቶ ተስፋስላሴ በምሳሌነት አቅርበውልናል። በእነዚህ ክልሎች ሀገረሰባዊ ዘዴዎችን በመጠቀም ግጭቶችን እንዲፈቱ በማድረግ የሀገር ሽማግሌዎች አማካሪ ምክር ቤቶችም ተቋቁመዋል። በጋምቤላ የአገር ሽማግሌዎች አማካሪ ምክር ቤት አባል የሆኑት አቶ ሀኪም ኡጋራም በክልሉ የተከሰቱ ግጭቶችን በአገሬው ልማድ መሰረት ለመፍታት ከ1996 ወዲህ ውጤታማ ተግባራትን በማከናወን ላይ እንዳሉ ነግረውኛል።

## 3.5.2 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ

በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ከመውጣቱ 1930 እ.ኤ.አ በፊት የወንጀል ጉዳዮች ይታዩ የነበረው ፍትሀነገስት ውስጥ በተደነገውና ልማዳዊ ህጎች መሰረት ነበር። ከዚህ ጎን ለጎን የእስልምና ሐይማኖት ተከታዮች በፍትሐነገስቱ ለመዳኘት ስለማይገደዱ ጉዳያቸው በሸሪያ ፍርድ ቤት እንዲታይ ከልከላ እንደሚሰጣቸው George Krzeczunowicz እንዲህ ሲል ጽፎአል፤ *"In favour of muslems by the continuing factual recognition by state courts of the juridiction of kadis councils applying muslem personal law."* (P.430):: በአጠቃላይ ከ1930 በፊት በኢትዮጵያ ለወንጀለኛ መቅጫ የህግ መሰረቶች ፍትሐነገስት፣ ልማዳዊና የሸሪያ ሕጎች ነበሩ። በህብረተሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶች እንዲፈቱ ይደረግ የነበረውም እንደ ህዝቡ ባህልና ሀይማኖት በእነዚህ የህግ መሰረቶች ነበር።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በ1930 እ.ኤ.አ የወጣው የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ልማዳዊ ህጎችን ከዘመናዊ የህግ ጽንሰሀሳቦች ጋር ለማገናዘብ የሞከረ ነው። ሙራዱ ባዘጋጀው የክፍል ውስጥ ፈረንት እንደተገለጸው በ1930 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሲወጣ በምንጭነት የተጠቀመው ፍትሀነገስትንና የአውሮፓን ዘመናዊ ህጎች ነው። ወንጀለኞች በሰሩት ወንጀል ሲቀጡ የጎሳ ታሪካቸውን፣ የትምህርት ደረጃቸውንና ወንጀሉን ለመፈጸም የገፋፋቸውን ምክንያት ከግንዛቤ ያስገባል። በነፍስ ግድያ ወንጀል የተከሰሰ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ እስከ ሞት የሚያደርስ ቅጣት እንደሚጣልበት በወንጀለኛ መቅጫ ህጉ ከቁጥር 522 እስከ 524 ባለው ተደንግጓል። የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት በማወክ ተግባር የተከሰሰ ደግሞ በቁጥር 323 ላይ በተገለጸው መሰረት ፍርድ ቤት ቀርቦ ቅጣት ይበየንበታል።

## 3.6 የአኝዋ ልማዳዊ ሕጎች

አኝዋዎች ህገሰባዊ የግጭት መፍቻ ደንቦችና ህጎችን ማን እንዳወጣቸው ሲጠየቁ ወደ ኋላ ሄደው የሚጠቅሱት "ኡቹዶን" ነው። ስለኡቹዶ በሚነገሩ ሚቶችም ይኼው ይንጸባረቃል (በአባሪ ተራ ቁጥረ ከ1-3 ያለውን ይመልከቱ)። አኝዋዎች እንደሚሉት ከኡቹዶ በፊት ፍትሀዊ ዳኝነትና ህገሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴ አልነበረም። *«ለሰላማዊ የግጭት መፍቻ ዘዴ የህግ መሰረት የጣለው ኡቹዶ ነው»* (ኦ/ሮ ... አኳይ፣ *ታህሳስ 8፣1999)*። አኝዋዎች ኡቹዶ "አጀዎ ናም ጁዋክ" (የወንዝ አማልክት) ነው ብለዉ ያምናሉ። ለአጀዎ ናም ጁዋክ ኡቹዶ ብለው ስም ያወጡለት አኝዋዎች ናቸው (አባሪ ተራ ቁጥር 2ና4 ይመልከቱ)።

በቡድን ውይይት ተሳታፊ የነበሩት (አቶ ሀኪም ኡጋራ፣ ኡጉታ ኦዲው፣ አመድ ኡዲሉ፣ አኳይ ኡመድ) እንደነገሩኝ *"በአኝዋዎች መካከል የተፈጠረን አለመግባባት ለመደምደም ዘዴ የሸመገለው ኡቹዶ ነው"*። በዚህ ተግባሩ የተደሰቱ የአካባቢው ነዋሪዎችም ግጭቶች ሲከሰቱ ትዳኝናለህ በሚል አብሮአቸው እንዲኖር ጠይቀውት ነበር። ኡቹዶ ግን ከቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረው በወንዝ ውስጥ እንደሆነ ነግሮቸአው ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚያስችሉ የህግ መርሆዎችን አወጣ። በመጨረሻም ባልታወቀ ሁኔታ ከአካባቢው ተሰወረ። ኡቹዶ ህግ ከማውጣቱ በፊት ግን በወቅቱ የነበረው ችዋይ የሚባል የአኝዋ መሪ እንደፈለገ በፈላጭ ቆራጭነት ይዳኝ እንደነበር አቶ ኡጉታ ኦዲው እንዲህ ሲሉ ነግረውኛል፣

በችዋይ ዘመን ፍትህ አልነበረም። ችዋይም ለዘመዶቹ የሚያደላ ነበር። በአጠቃላይ ዘመኑ ሀይለኛ ደካማውን፣ ሀብታም ደሀውን የሚያጠቃበት ነበር። ዛሬን ድረስ ፍትሀዊ ያልሆነ ዳኝነትን እኝዋዎች የችዋይ ፍርድ እያሉ ይጠሩታል። ፍትሀዊ ዳኝነትን ማግኘት የተቻለውና በሽምግልና ግጭቶችን መፍታት የተጀመረው ኡቼዶ ሕግ ካወጣ በኋላ ነው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እኝዋዎች ግጭቶቻቸውን በሰላማዊ መንገድ እየፈቱ ለዘመናት አብረው ለመኖር ችለዋል (ታህሳስ 10፣1999)።

በእኝዋ ሀገረሰባዊ ህጎች መሰረት ማንኛውም አይነት ግጭት መፈታት ያለበት በሰላማዊ መንገድ ብቻ ነው። የግጭቱ አይነትና መጠን ምንም ይሁን ምን ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ እንዲከፈል ሕጉ ያስገድዳል። ካሳ ካልተከፈለ ለግጭቶች ዘላቂ መፍትሄ መስጠት አይቻልም። በእኝዋዎች ዘንድ ሰው መግደል ከፍተኛ ወንጀል ነው። በልማዳዊ ሕጎቻቸዉም ሰው የገደለ ይገደል የሚል የለም። በማንኛውም ሁኔታ ሰው የገደለ ደግሞ ፈጥኖ እጁን ለኚያ (ንጉስ) ወይም ኳር (የቀበሌ ሹም ወይም አስተዳደሪ) መስጠት እንዳለበት የእኝዋ ልማዳዊ ህግ ያዛል። እጁን የሰጠ ደግሞ ብቀላ እንዳይፈጸምበት ከለላ ያገኛል። ገዳይ በተከለለበት ማንም ሰው ገብቶ የሀይል እርምጃ መውሰድ አይችልም። ገዳይ እጁን ከሰጠበት ኚያ ወይም ኳር ግቢ ገብቶ ብቀላ የፈጸመ ሰው እንደ ወንጀለኛና ነውር ይቆጠራል።

በባልና ሚስት መካከል የሚከሰት ግጭት የሚዳኘው "ጆው ዊማች" በሚባል የቤተዘመድ ጉባኤ ነው። በጆው ዊማች ውሳኔ መሰረት ጥፋተኛ ሆና የተገኘች ሚስት ከሆነች ተመክራ እንድትመለስ ወደ ቤተሰቦቿ ትላክና ላጠፋችው ጥፋት ባሏን እንድትክስ ይደረጋል። በጆው ዊማች ሊፈታ ያልቻለ የባልና ሚስት ጉዳይ በቀጥታ ኝዎር በሚባለው የባህላዊ አስተዳደር ባለስልጣን ለሚመራው ጆዶንጎ (የአገር ሽማግሌዎች) ይተላለፋል። በዚህ ጆዶንጎ ሊፈታ ካልቻለ የባልና ሚስት እጣ ፈንታ መፋታት ብቻ ነው።

በመሬት ይገባኛልና በድንበር ምክንያት የሚፈጠር አለመግባባት፣ የህብረተሰቡን ወግና ልማድ የጣሰ፣ የጎረቤት ግጭት፣ ስርቆት ዘረፋ፣ ድብድብ፣ እምነት ማጉደል፣ ሁከት መፍጠር፣ ጠለፋና የመሳሰሉ ድርጊቶችም በሚመለከታቸው ጆዶንጎዎች

እንዲታዩ ያደረጋል። በእነዚህ ምክንያቶች በደል ደርሶብኛል የሚል አቤቱታውን በቀጥታ የሚያቀርበው "ሰዘርንኦል ሉጎ" (የሰፈር ጆዶንጎዎች) ወይም ኘቡር ነው። እላይ ከተጠቀሱት ድርጊቶች መካከል የህብረተሰቡን ወግና ልማድ ጥሶ ነውር የሰራ፣ የራሱ ያልሆነን ንብረት ይዞ የተገኘና ሁከት በመፍጠር የተወነጀለ ሰው ደግሞ በኛቱዌል (ከአስተዳደሩ ከፍተኛ ባለስልጣን አንዱ) አመካኝነት ጉዳዩ ተጣርቶ ለጆዶንጎዎች ይቀርባል።

በዘመዶቹ ላይ ተገቢ ያልሆነ በደል የሚያደርስ፣ ክፉ ነገር ከመስራት ተመክሮ ያልተመለሰ፣ ራስ ወዳድ፣ ስግብግብና የመሳሰሉ ባህሪያት የተጠናወተው ሰው በመጀመሪያ ከመጥፎ ድርጊቱና ባህሪው እንዲመለስ በዘመዶቹ ይመከራል። ተመክሮም ቢሆን አሻፈረኝ ካለ የሚደርስበት የመጨረሻ ቅጣት እርግማንና መገለል ነው። እርግማን የደረሰበት እስከ ሞት የሚያደርስ አደጋ ይገጥመዋል የሚል እምነት አለ።

## 4. የአኝዋ ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርዓት

አኝዋዎች በኚያና (ንጉስ) እና ኳሮ (የቀበሌ ሹም ወይም አስተዳዳሪ) የሚመሩ ሁለት አይነት ግን ተመሳሳይ የሆነ አደረጃጀትና አወቃቀር ያላቸው ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርአት እንዳላቸው ቀደም ሲል ተገልጹዋል:: ከእዚህ በመቀጠል ደግሞ ስለአስተዳደር ስርአቶች አደረጃጀት ፤ አሰራር ፤ የንግስና ስነስርአትና ክንዋኔዎች እንዲሁም በህዝብና በመሪዎች መካከል ያለ ግንኙነትን የተመለከቱ ዝርዝር ገለጻዎችና ማብራሪያዎች ቀርበዋል።

### 4.1 የአስተዳደሩ አደረጃጀትና ባለስልጣናት

ከጋምቤላ ከተማ በስተደቡብና ደቡብ ምስራቅ አካባቢዎች (የአቦና ጆር ወረዳዎች በከፊል) የሚኖሩ አኝዋዎች የሚተዳደሩት በኚያ ሲሆን የተቀሩት አካባቢዎች ግን የየራሳቸው ሉአላዊ ነፃነት ያላቸውን ቀበሌዎች በሚያስተዳድሩ ኳሮዎች ነው:: እያንዳንዱ ቀበሌም የራሱ ኳሮ አለው። «በአንድ ቀበሌ የሚኖሩ አኝዋዎች በአብዛኛው የአንድ ጎሳ አባላትና በዝምድና የተሳሰሩ ናቸው። ኳሮ የሚመረጠውም የባላባት ዝርያ ካለው ቤተሰብ ነው» (አቶ ኙጎም አበላና ኡመድ ኡኩኝ፤ ታስሳስ 8፤1999):: የአንድ ቀበሌ ነዋሪዎች ቀበሌያችን የጋራ ግዛታችን ነው የሚል አመለካከት እንዳላቸውም አቶ ኙጎም አበላ ነግረውኛል።

በሁለቱም የአስተዳደር ስርዓት ከፍተኛ የሆኑ አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ መክሮ ውሳኔ የሚሰጥ የመማክርት ሸንጎ አለ። ይህ የመማክርት ሸንጎ በኚያ አስተዳደር "ቸምቅ"፤ በኳሮ ደግሞ "ጀቡሬ" እየተባለ ይጠራል:: የመማክርት ሸንጎው አባላት ደግሞ "ካርዋንግ"፤ "ኝኩጉ"፤ "ኚያቱዋል"፤ "ኝቡር"፤ "ኝባድቦጎ" የሚባሉ ከፍተኛ ባለስልጣናት፤ "ጃይ" (ከፍተኛ አማካሪ የአገር ሽማግሌዎች) እና "ሚኚዬዎች" (የመሪው እናት ወንድሞች ወይም የቅርብ ዘመዶች) ናቸው:: ሚኚዮዎች በሸንጎው የሚሳተፉበትን ምክንያት ጠይቄ አቶ ኡጉታ አዲው እንደሚከተለው ነግረውኛል::

ኚያና ኳሮ ከአንድ በላይ ሚስቶች ስለአሉዋቸው (ከአንድ በላይ ማግባት በአኝዋ ቤተሰብ የተለመደ ነው) በአባት አንድ ሆነው በእናት የሚለያዩ



ERSITY LIBRARY ...LS

ወንድማማቾች (አንዳንዴም በአንድ እናት ልጆች) መካከል በስልጣን መቀናቀን አለ፡፡ በዚህ ምክንያት የእናት ወንድሞች ስልጣኑ ከእነሱ ወገን እንዳይወጣ ግንባር ፈጥረው ተቀናቃኞቻቸውን ለመቋቋም ከኒያው ጋር በቅርብ ሆነው ይሰራሉ (ታህሳስ 10፤1999)፡፡

የአስተዳደሩ ባለስልጣናት የሚሾሙት ለመሪያቸው ባላቸው ቅርበትና ችሎታቸው ሲሆን የባለስልጣናቱ መጠሪያ ስምና ተግባራት በኒያም ሆነ በኳር አስተዳደር ተመሳሳይ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ከኒያ ወይም ኳር ቀጥሎ ከፍተኛ ባለስልጣን ካርዋንግ ይባላል፡፡ ካርዋንግ የኒያ ወይም ኳር የቅርብ ረዳትና እነሱ በሌሉበት ተወክሎ ማንኛውንም አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ተግባራትን የሚያከናውን ነው፡፡ ከዋናው ቀበሌ ተነጥለው ያሉ ንኡሳን ቀበሌዎችንም በውክልና የማስተዳደር ስልጣን አለው፡፡

ከካርዋንግ ቀጥሎ የኒያ ወይም የኳር አማካሪና የቅርብ ረዳት፣ ከአጎራባችና ሌሎች አካባቢ መስተዳድሮች ጋር የሚኖረውን ግንኙነት የሚያስተባብር ከፍተኛ ባለስልጣን ኘኩት ይባላል፡፡ ኘኩት የአካባቢውን ሰላምና ጸጥታ የሚያውኩ ሰዎችን የመቆጣጠር ኃላፊነትም አለበት፡፡

የኒያ ወይም የኳር ልዩ መልእክተኛ፣ መረጃዎችን ወደ ተለያዩ አካባቢዎች የሚያደርስና እንደ ሕዝብ ግንኙነት ያሉ ተግባራትን የሚያከናውነውና ህዝባዊ ስብሰባዎች ሲካሄዱ የሚያስተባብር ኚያቱዌል ይባላል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የታዋቂ ግለሰቦችን ቀብር ስነስርዓት የማስተባበርና የመምራት ኃላፊነት አለበት፡፡ ታዋቂ ሰዎች ከመሞታቸው በፊት በቅርብ ተገኝቶ የሚያስተላልፉትን የኑዛዜ ቃል ያዳምጣል፡፡ ኑዛዜያቸውንም በቀብር ሥነስርዓታቸው ላይ ለህዝብ ያሳውቃል፡፡ ለጋራ መጠቀሚያነት የተከለሉ ቦታዎችንም ይቆጣጠራል፡፡ ለጋራ መጠቀሚያነት የተከለሉ ቦታዎች ላይ በራሱ ፍቃድ ለግል ጥቅሙ ሲል የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን የተገኘን ተከታትሎ የስነስርዓት እርምጃ እንዲወሰድበት የማድረግ ኃላፊነትም አለበት፡፡

በአስተዳደሩ የግዛት ክልል ውስጥ ድንገተኛ የተፈጥሮ አደጋ (ለምሳሌ ጎርፍ፣ ወረርሽኝ፣ ረሀብ) ሲከሰት ጉዳዩን እየተከታተለ የአገር ሽማግሌዎችና የዕምነት መሪዎች ተሰባስበው ፈጣሪያቸው ከተከሰተው አደጋ እንዲታደጋቸው ይማጸኑ ዘንድ የማስተባበር

ኃላፊነት የተሰጠው ባለስልጣን ኜቡር ይባላል። ኜቡር የተፈጠረውን ችግር በጋራ ለመቋቋም እንዲቻል ህዝቡ ተባብሮ እንዲሰራ ያደርጋል። አኝዋዎች የተቸገሩና አቅመ ደካሞች በህብረተሰቡ ታቅፈው እንዲረዱ የማድረግ ባህል ስላላቸው ኜቡር ይህንን ጉዳይ ከበላይ ሆኖ ይከታተላል። የታመሙትን ይጠይቃል፣ አዛውንቶች ከመሞታቸው በፊት አገራቸውንና ህዝባቸውን ፈጣሪ ከክፉ ነገር ይጠብቅላቸው ዘንድ እንዲጸልዩና እንዲመርቁ ያስተባብራል። ከኚያቁዌል ጋር በመሆንም በቀብር ሥነስርዓት ላይ ህዝብ እንዲገኝና ንግዜዎችን እንዲያዳምጥ ያስተባብራል። በአኝዋዎች ዘንድ አንድ ሰው ታሞ ከመሞቱ በፊት ስለሚቀበርበት ቦታ፣ በቤተሰቦቹ ሊደረግለት ስለሚፈልገው የሀዘን ስነስርዓት፣ ህዝቡ ሊደግፈውና ተቀብሎ ሊተገብረው ስለሚገባው ጉዳይ ወዘተ በንግዜ መልክ የማስተላለፍ ልማድ አለ። ንግዜን ማክበር አኝዋዎች እንደ ማህበራዊና ሀይማኖታዊ ግዴታ ስለሚያዩት ማናቸውንም ዓይነት ንግዜዎች ተግባራዊ ያደርጋሉ። ንግዜን ያላከበረ ከህብረተሰቡ ወቀሳና ሀሜት ይደርስበታል። ንግዜ ተግባራዊ ካልሆነ የሟች መንፈስ ይቆጣናል፣ ይቀየመናል፣ መጥፎ ነገር ሊገጥመንም ይችላል የሚል እምነት አለ። ኚያቁዌልና ኜቡርም ንግዜዎችን እየተከታተሉ ለህዝብ ያሳውቃሉ።።

የኚያን ወይም የኳሮን መኝታ ስፍራ፣ መቀመጫ፣ አልባሳት ወዘተ በቅርብ ሆኖ እንዲከታተልና እንዲያዘጋጅ ኃላፊነት የተሰጠው ሰው ኜባድቦጎ ይባላል። ኜባድቦጎዎች ሁለት ሲሆኑ እነዚህ ሰዎች ሁሌም ቢሆን መሪዎች በሚሄዱበት ቦታ ሁሉ አይለዩም። ኃላፊነታቸው ካሬ የፕሮቶኮል ሹም ከሚባለው ጋር ተመሳሳይነት አለው።

የቤተመንግስቱን ምድረ ግቢ የሚያስተዳድር፣ ባለጉዳዮችንና እንግዶችን ተቀብሎ ከኚያ ወይም ከኳር እንዲገናኙ የሚያደርግ ባለስልጣን ኜፓር ይባላል። አንዳንዴ ኜኬና ከሚባል የምግብ ጉዳይ ኃላፊ ጋር በመሆን ይሰራል። የመሪዎች ምግብ የሚዘጋጀው ኜኬና በሚባል የቤተመንግስት አገልጋይ ሲሆን ኚያና ኳሮዎች ሴት ያዘጋጀችውን ምግብ አይመገቡም። መሪዎች ለጭፈራ ፕሮግራም ሲወጡ የባህል ጌጣጌጦችንና አልባሳትን አድራጊና አጃቢ ደግሞ ኳች ኮዴ ይባላል።

## 4.2 ጆ ሉዋክ

በአኝዋ ብሔረሰብ በተቀራራቢ የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ወጣቶች በጋራ ተሰባስበው በአንድ ቡድን ይደራጃሉ። ይህ የእኩያሞች ስብስብ ያለበት ቡድን "ጆ



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ሱዋክ እየተባለ ይጠራል። የጆ ሱዋክ ቡድን መሪ የሚመረጠው ከቡድኑ አባላት መካከል ሲሆን መጠሪያ ስሙም "ኳይ ሱዋክ" ይባላል። የጆ ሱዋክ አባላት በጦርነት ጊዜ በግንባር ይሳተፋሉ። ኚያዎችንና ኳሮዎችንም በጉልበት ስራ ይረዳሉ። በተለያዩ የማህበረሰባዊ አገልግሎት ተግባራትም እንደ ሁኔታው ተሳትፎ ያደርጋሉ። ኚያና ኳሮዎች በበኩላቸው በተለያዩ ጊዜያት ለጆ ሱዋክ አባላት ግብዣና የጭፈራ ፕሮግራም ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል። በአስርና አስራ አምስት አመት አንዴ ደግሞ ኚያዎች የቀድሞዎቹንና አዲሶቹን ጆ ሱዋኮች በጋራ የሚጋብዙበት ከፍተኛ ድግስና የጭፈራ ፕሮግራም ያዘጋጃሉ። በዚህ ግብዣ ላይ በጀግንነታቸውና መልካም ተግባራቸው የተመረጡ የቀድሞ ጆ ሱዋክ አባላትን ገላ ቅቤ የመርጨት ስነስርአት ይካሄዳል። ገላቸውን ቅቤ የተረጨ የጆ ሱዋክ አባላት "ሱፒ" በመባል ይጠራሉ(በመልካም ተግባራቸው የተመረጡ እንደማለት ነው)። እንዲህ አይነቱ ሥነስርዓት የሚካሄድበትን ምክንያት አቶ ሀኪም ኡፓራና ኡጉታ አዲው እንደሚከተለው ገልጸውልኛል። "ኚያዎች ከቀድሞ የጆ ሱዋክ አባላት በጀግንነታቸውና መልካም ተግባራቸው የተመረጡትን ገላ ቅቤ በመርጨት ሱፒ የሚሉዋቸው ወጣት የጆ ሱዋክ አባላት ተግተው እንዲሰሩና ለሱፒ ደረጃ እንዲበቁ ለማበረታታት፣ መልካም ተግባር ለፈጸሙ ሰዎች ደግሞ ክብር ለመስጠትና በመሪዎችና በጆ ሱዋክ ቡድኖች መካከል ያለውን መልካም ግንኙነት ለማጠናከር ነው።"(ታህሳስ 16፣1999)።

ኢቫንስ ፕሪቻርድ በኚያና ኳሮ አስተዳደር የተደራጀ የጋራ ጦር ሰራዊትና የግጭት መፍቻ ተቋም እንደሌለ ሲገልጽ የሚከተለውን ብሎአል "*...yet there is no organization or joint military enterprises nor any well defined judical institutions for the settlement of disputes, (P.138)::* በመስክ ተገኝቼ እንዳረጋገጥኩት ግን ይህ የኢቫንስ ፕሪቻርድ አባባል በተጨባጭ ካለው ሁኔታ ጋር የሚጋጭ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። የቡድን ውይይት ተሳታፊ የነበሩት አቶ ሀኪም ኡፓራ፣ ኡጉታ አዲውና ኚንም አበላ እንደሚከተለው ገልጸውልኛል።

> አንዋዎች የውጭ ሀይል ሲያጠቃቸው ሲመጣ ወይም በሌላው ላይ ለብቀላ ሲነሱ የተለያዩ ቀበሌዎች ግንባር በመፍጠር ጊዜያዊ የጦር ሰራዊት ያደራጃሉ። ጦሩን በበላይነት የሚመራውን ደግሞ ኚያ ወይም ኳሮ ነው። በቀበሌዎች መካከልና ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታትም ካርዋንግ፣

ኒያቁዋል፣ ኝቡር፣ ኝኩጉ የሚባሉ ባለስልጣናትና የአገር ሽማግሌዎችን ያቀፈ የአስታራቂ ቡድን ይቋቋማል (ታህሳስ 16፣1999)።

ይህ ቡድን የተፈጠረውንግጭት በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ኃላፊነት አለበት።

## 4.3 የኒያ አስተዳደርና የንግስና ስነስርዓት ክንዋኔዎች

ኒያዎች የየራሳቸው የግዛት ክልል ያላቸው ሲሆን የዘር ግንዳቸውም "ቱንግ ኡዶላ" እና "ቱንግ ጎች" ይባላል። ቱንግ ኡዶላ በሱዳን፣ ቱንግ ጎች ደግሞ በኢትዮጵ ይገኛሉ። ኳሮዎችም የኒያን ስልጣን መያዝ ያልቻሉና ከነተከታዮቻቸው ተገንጥለው በመውጣት የመሰረቱዋቸዉን ቀበሌዎች የሚመሩ የኒያ ዝርያ ያላቸው ናቸው። የመጀመሪያው የአኝዋ ኒያ እንደሆን የሚነገርለት ጊሉ የሚባል የኡቺዶ ልጅ ነው (አባሪ 4እና5 ይመልቱ)። አቶ ሀኪም ኡፓራ እንደነገሩኝ "ኡቺዶ የቱንግ ኡዶላና ቱንግ ጎች አባት ተደርጎ ይታያል። ኒያ የሚመረጠውም ከሁለቱ የዘር ግንዶች ለስልጣኑ ቅርበት ያለው ብቻ ነው። ኳሮዎችም ከሁለቱ የዘር ግንዶች ተገንጥለው የወጡ የቀበሌ መሪዎች ናቸው" (ታህሳስ10፣1999)። ኒያ በኳሮ የግዛት ክልል ውስጥ ጣልቃ ገብቶ ለማዘዝና ተጽእኖ ለማሳረፍ የሚያስችል ምንም አይነት ስልጣን የለውም። ስለሆነም አኝዋዎች የሚኖሩበትን የግዛት ክልል አንድ አርጎ የሚያስተዳድር ማዕከላዊ መንግስት የለም። ብዙ ጊዜ ኳሮዎች የኒያዎች ባላንጣ ሆነው እንደሚታዩም አቶ ሀኪም ነግረውኛል። ኢቫንስ ፕሪቻርድም በንጉስ የሚተዳደሩ በርካታ የአፍሪካ አገሮች ማዕከላዊ መንግስት አላቸው ፣ በተቃራኒዉ ደግሞ በአኝዋ ብሄረሰብ ንጉስ አለ ማዕከላዊ መንግስት ግን የለም በማለት የሚከተለውን ጽፎአል።

> *In most African monarchies the local divisions of the kingdom are held together by a central authority, and the local rulers are delegates of, and subject to this authority. Among the Anuak, on the contrary, there is a kingship but no central government. The king is not the ruler of the country. The nobles who have authority over the villages are not delegates of the king, or subject to him. They are his rivals (p.136)*

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

የተለያዩ አካባቢዎችን የሚያስተዳድሩ ኚያዎች ቢኖሩም የንጉሶች ሁሉ ንጉስ ተደርጎ የሚታየው ግን አዶንግ በሚባል የሱዳን ግዛት የሚገኘው የቱንግ ኡዶላ ኚያ ነው። የአዶንግ ኚያ እንደ ንጉሰነገስት ተደርጎ ቢታይም እውቅና ከመስጠት ባለፈ በሌሎች ኚያዎች ላይ የበላይነቱን የሚያረጋግጥበት ስልጣን የለውም። የሌሎች ኚያዎች ሹመት የሚጸድቀውና የንግስና ስነስርዓት የሚከናወነው ግን የአዶንግ ኚያ ሲፈቅድ ብቻ ነው። የበአለ ንግስ የወግ ዕቃዎችና ጌጣ ጌጦች በሙሉ የሚቀመጡትም ከአዶንግ ኚያ ዘንድ ነው።

በአኝዋ ባህል አንድ ኚያ ከመሞቱ በፊት ከልጆቹ መካከል ዙፋኑን የሚወርሰው ማን እንደሆን ለታማኝ ወዳጆቹ አስቀድሞ በሚስጥር ይናዘዛል። እስከሚሞት ድረስ ኑዛዜው በሚስጥር እንደተጠበቀ ይቆያል። ለዚህ ምክንያቱ በስልጣን ሽኩቻ ምክንያት በወንድማማች መካከል ጠብ እንዳይነሳ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ነው። ኑዛዜው ለወራሹና ለህዝቡ ይፋ የሚሆነው ኚያው ከሞተ በኋላ በቀብር ስነስርዓቱ ላይ ነው። ለኚያነት የታጨው ልጅ ለአቅመ አዳም ያልደረሰ ከሆነ ለቦታው ብቁ እስከሚሆንና የንግስና ስነስርዓቱን እስከሚያከናውን ድረስ ኚያቱዌል፣ ኝቡር፣ ኝባድቦጎ የሚባሉት ባለስልጣናትና የአገር ሽማግሌዎች ከእናቱ ወንድሞች ጋር በመሆን ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮችን እያከናወኑ ይቆያሉ። ሴቶች ለኚያነት አይታጩም። በአስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ በመስጠትም ተሳትፎ አያደርጉም።

ኚያዎች ሲነግሱ የንግስና ስነስርዓቱ የሚከናወነው አዶንግ ድረስ በመሄድ እዚያ በሚገኘው ኚያ ቤተመንግስት ግቢ ውስጥ ነው። ለስነስርአቱ ድግስ በሬ ይታረዳል፣ ባህላዊ መጠጦችም ይዘጋጃሉ። ምግቡ የሚዘጋጀው ኝኬና (የኚያ ምግብ አዘጋጅ) በሚመራው የወንዶች ቡድን ሲሆን ሴቶች ባህላዊ መጠጦችንና ለገንፎ የሚሆን ዱቄት አዘጋጅተው ከማቅረብ ውጭ በምግብ ዝግጅት አይሳተፉም።

ለንግስና የሚያበቁ ቅድመ ዝግጅቶችን ለማከናወን እስከ አመት የሚፈጅ ጊዜ ሊወስድ ይችላል። ከቅድመ ዝግጅት እስከ በአለ ንግሱ ድረስ ያለው ሂደትና ክንዋኔ "ሮኝ" እየተባለ ይጠራል። ሮኝ የሚከናወነው በኚያው እናት ወንድሞች አማካኝነት ነው። የሚነግሰው ኚያ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የቱንግ ጎች ወገን ከሆነ የእናቱ ወንድሞች ቀደም ብለው ወደ አዶንግ በመሄድ እጩው ኚያ እውቅና እንዲሰጠውና የንግስና

ስነስርዓቱ እንዲፈጸም ይጠይቃሉ፡፡ የአደንግ ኚያ በእጨው ኚያ ላይ ቅሬታና ቂም ካለው አውቅና ሊነፍግ ይችላል፡፡ ዕውቅና ከተነፈገ የንግስ በአሉን አካሂዶ ኚያ ሊባል አይችልም፡፡ አደንግ ከሚገኘው የቱንግ አደላ ወገን ከሆነ እጨው ኚያ በእናቱ ወንድሞች አማካኝነት ስነስርዓቱ ተዘጋጅቶ አባቱ በሞተ ጥቂት ቀናት ውስጥ ኚያ ተብሎ ይሾማል፡፡ የቱንግ ጎች ኚያ ሲነግስ ወንድሞቹ ከበአለ ንግሱ ቀን በፊት የአደንግ ኚያ ገቢ ተገኝተው ባህሉ በሚፈቅደው ደንብ መሰረት ድግስ ያዘጋጃሉ፡፡ ስነስርዓቱ የሚፈፀመው "ዲቶሩ" በሚባል ልዩ ስፍራ ላይ ነው፡፡ ዲቶሩ በከፊል በሳር የታጠረ ሲሆን የአደንግ ኚያና ባለሥልጣናት የሚቀመጡት ለክብራቸው በተዘጋጀ የተለየ ቦታ ነው፡፡ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች፣ የአገር ሽማግሌዎች ፣ የእጨው ኚያ ወገኖችና ሌሎች የስነሥርአቱ ታዳሚዎችም በተዘጋጀላቸው ስፍራ ሆነው ስነስርዓቱን ይከታተላሉ፡፡ ከዲቶሩ መሀል ላይ ደግሞ "ዎሉ" (የንጉስ ልጅ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ እጨው ኚያ የሚቀመጥበት ባለ አንድ እግር በርጩማ) ይቀመጣል፡፡ *"አቹዶ ለመጀመሪያ ጊዜ ወንዝ ዳር ተቀምጦ የተገኘው ዱል ጃክ በሚባል የግንድ ጉማጅ ላይ ነው፡፡ ዎሉም ይህንኑ እንዲመስል ተደርጎ የተዘጋጀ ሲሆን እውነተኛ የኚያ ልጅ ለመባል ማረጋገጫው ባህሉ በሚፈቅደው ደንብ መሰረት ዎሉ ላይ መቀመጥ የቻለ ብቻ ነው" (አቶ ኡጉታ አዲው፣ ታህሳስ 9፣1999)፡፡*

የንግስ ስነስርአቱ ሲከናወን እጨው ኚያ ፀጉሩን ተላጭቶ "አዱዳ" የሚባል እንደ ዘውድ ተደርጎ የሚታይ ባለማንገቻ ጥምዝ የጨሌ ጥምጣም ያደርጋል፡፡ ኚያ
ሲሞት ተመልሶ በውሃ ውስጥ ህያው ሆኖ ይኖራል የሚል እምነት በአኙዋዎች ዘንድ አለ፡፡ ፀጉሩ አብሮት የሚቀበረውም ውሃ ውስጥ ሲኖር መልሶ ይበቅልለታል የሚል እምነት ስላለ ነው፡፡ ከወገቡ በላይ የሚለብሰው የነብር ቆዳ ደግሞ "ፔንችቦክ" ይባላል፡፡ "ጋኛ" ፣ "ኚያሉ" ፣ "ዋንጋሊክ" ፣ "ኡቾክ" እና "ጉራማቱ" የሚባሉ የአንገት ጨሌዎችንም በቅደም ተከተላቸው መሰረት ያጠልቃል፡፡ የጨሌዎቹ ርዝመት የተለያየ ሲሆን ቀለማቸውም ጋኛ ደብዘዝ ያለ ነጭ፣ ኚያሉ ደማቅ ሰማያዊ፣ ዋንጋሊክ ደብዘዝ ያለ ሰማያዊ፣ ኡቾክ (ጥቁር)፣ ጉራማቱ ደግሞ ወደ ጥቁር ያደላ ሰማያዊ ነው፡፡ ከእነዚህ ጨሌዎች ዋናው የኚያነት መገለጫ ትዕምርት (Symbol) ኡቾክ ሲሆን የተቀሩት ጥንት የነበሩ ኚያዎች ለንግስና በአላቸው ክብር ያዘጋጁዋቸው ናቸው፡፡ አቶ ኙጎዎ እንደነገሩኝ "አንዳንዶች ጊሉ የተወለደው በአንገቱ ኡቾክ አጥልቆ ነው ሲሉ አንዳንዶች ደግሞ ኡቹዶ



*በ1995 ዓ.ም. የገበሰው ለዳንግ ለገዳ ቃም ኚያ ተብሉ ሲሾም የተነሳ ፎቶግራፍ*

እጬው ኚያ አልባሳትና ጌጣጌጦቹን አሟልቶ ማድረጉን የእናቱ ወንድሞች ካረጋገጡ በኋላ አጅበውት ወደ ዲቶሩ ይመጣሉ። በዚህ ጊዜ የእጩው ኚያ ሚስቶች፣ እንጀራ እናቶችና የቅርብ ዘመድ የሆኑ ሴቶች ተንበርክከው "አግዋጋ" የሚባል ስሜት ቀስቃሽ የጀግና ዘፈን ይዘፍናሉ። ዘፈኑ እንደተጀመረ እጩው ኚያ በእናቱ ወንድሞች ታጅቦ "ዶም" እና "ጆም" የሚባሉ ሁለት ጦሮች በግራና ቀኝ ይዞ እየሰበቀና እየፎከረ ወደ ዲቶሩ ይመጣል። በዚህ ጊዜ አንድ ሰው ትንሽ ከበሮ ከብብቱ ስር ታቅፎ ድም … ድም…ድም… በሚል ረጋ ያለ ምት እየመታ የኚያውን እንቅስቃሴ አብሮ ያጅባል። ከጥቂት ቆይታ በኋላ ዘፈኑ ይቆምና ምሉ ላይ የመቀመጥ ሥነስርዓት ይከናወናል። ምሉ ላይ የመቀመጥ ስነስርዓት ሲከናወን ከአጃቢዎች በስተቀር ስነስርዓቱን በጥሞና ከመከታተል ባለፈ ለማንም ሰው መቆምና መንቀሳቀስ አይፈቀድም። እጩው ኚያ በምሉ ላይ ምንም ሳይፈራ፣ ሳይርበተበትና ሳይንገዳገድ የመቀመጥ ግዴታ አለበት። ከተንገዳገደ፣ ከፈራና ከወደቀ የኚያ ልጅ አይደለም ስለሚባል ወዲያው በአጃቢዎቹ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ይገኛሉ። በእኝዋዎች የህይወት ፍልስፍና ኚያዎች ደፋሮች፣ ጠንካሮች፣ ህዝቡን ከማገናኛውም አደጋና ችግር የሚጠብቁና አስተዋዮች ናቸው። ይህን የታደሉና በእግዚአብሄር የተመረጡ ደግሞ የቁንግ ኡዶላና ቱንግ ጎች ዘሮች ናቸው። ቱንግ ኡዶላና ቱንግ ጎች ወደ ኋላ ሄደው የዘር ግንዳቸውን ሲቆጥሩ መቆሚያቸው ኡቹዶ ነው። ስለዚህ በባህሉ መሰረት ፊራ ተባ ሳይል በእግባቡ ምሉ ላይ መቀመጥ ያልቻለ የኚያ ልጅ ህዝቡን በአግባቡ ለመምራትና ለማስተዳደር ብቃት የለውም የሚል አመለካከት አለ። በኡቹዶ ሚት እንደተገለጸው (አባሪ ይመልከቱ) ኡቹዶ በእኝዋዎች ዘንድ ፍትህን ለማስፈን የተላከ ልዩ ፍጡር ተደርጎ ይታያል። ስለዚህ እኝዋዎች ከኡቹዶ ዝርያ ውጭ ኚያ ከተሾመ መጥፎ ነገር ሊገጥመን ይችላል የሚል እምነት አላቸው።

ደንቡ በሚፈቅደው መርህ መሰረት ሳይደናገጥ ሚዛኑን ጠብቆ ምሉ ላይ መቀመጥ የቻለ እጩ ኚያ ወዲያው "እሮኝ" ይባላል። ነገሰ ማለት ነው። ከእሮኝ በኋላ ኚያው ከህዝቡ ፊት ቆሞ የግዛት ክልሉን ሰላምና ጸጥታ እንደሚያስከብር፣ ህዝቡን ያለ አድሉዎ እንደሚያገለግል፣ ፍትህን እንደሚያሰፍን፣ የተቸገሩን እንደሚረዳ፣ የአባቱንና የህዝቡን ጠላቶች እንደሚፋለም ወዘተ የሚገልጽ ንግግር በማድረግ ቃል ኪዳን ከገባ በኋላ እየፎከረና እየሸለለ ወደ ዲቶሩ እጥር መግቢያ በር በመሄድ የበሩን ቋሚ ግራና ቀኝ ይዞ ይቆማል። እሱን ተከትለው ጃይ የሚባሉት እማካሪ የአገርሽማግሌዎች ከኚያው እግር ስር ግራና ቀኝ በመሆን ቁጢጥ ብለው ይቀመጣሉ። በመቀጠል ኚያው በጀግንነታቸውና በመልካም ተግባራቸው የተመረጡ ሰዎችን እየጠራ ሽልማት ይሰጣል። ተሸላሚዎችም ስማቸው ሲጠራ ኚያቸውን እያሞገሱና ለሽልማት ያበቃቸውን ተግባር በዜማ እየተረኩ ይፎክራሉ። የሽልማቶቹ መጠንና አይነት ተሸላሚው እንዳከናወናቸው ተግባራት የሚለያዩ ሲሆን ከብቶች፣ ጦር ድሙኙና ልዩ ልዩ የወግ እቃዎች ከሽልማቶቹ መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው። የሽልማት ስነስርዓቱ እንዳበቃ ወንዶችና ሴቶች ለየብቻቸው በመሆን ከተዘጋጀው ድግስ ይቋደሳሉ። በባህሉ መሰረት ኚያ ሰው ፊት ቀርቦ ወይም ሰው እያየው መብላትና መጠጣት አይችልም። ከነገሰ በኋላ ኚያው የሚጠራው በቀድሞ ስሙ ሳይሆን በእናቱ ስም የእገሌ ልጅ እየተባ ወይም በሌላ ቅጽል ስም ነው። ለምሳሌ በ1995 እ.ኢ.አ የተሾመው የእዶንግ ኚያ የቀድሞ ስሙ እዶንግ አገዳ ቻም ሲሆን ከነገሰ በኋላ ወሪ አቻንግ (የአቻንግ ልጅ) እየተባለ ይጠራል። የእገሌ ልጅ እየተባለ

የሚጠራበትን ምክንያት አቶ ሀኪም አፓሬ እንዲህ በማለት ገልጸውልኛል *"ኚዮዎች ከተለያዩ ሚስቶቻቸው የወለዱዋቸው በርካታ ልጆች ስላላቸው የአባቱን ዙፋን የወረሰው የትኛዋ ሚስቱ ልጅ እንደሆነ ለመለየት ነው"*:: ከነገሰ ማግስት ጀምሮ አዲሱ ኚያ በአባቱ ግቢ በይፋ ስራውን መጀመር ይችላል::

በእኛዋ ባህል መሰረት በዋና ዋና ጦርነቶች ላይ ጦሩን የሚመራው ኚያ ነው:: በእድሜ መግፋትና በሌሎች ምክንያቶች ጦሩን መምራት ካልቻለ ግን በጀግንነቱ ታዋቂ የሆነ ሰው ተመርጦ "ኢጋሜ ኚያ" ወይም "ኚኚያ ጋሜ" የሚባል ሹመት ይሰጠውና ጦሩን እንዲመራ ይደረጋል:: እንደ ዋናው ኚያ የሹመት አሰጣጥ ስነስርዓት ግን አይካሄድም:: ኢጋሜ ማለት የተሰበሰበ ረጃጅም የሳሽና ሳር የበዛበት ጫካ ማለት ሲሆን ኢጋሜ ኚያ ደግሞ የጫካ ንጉስ እንደማለት ነው:: ሹመቱ የሚሰጠው ጃይ በሚባሉ አማካሪዎችና ካይ ሉዋኮች (የጆ ሉዋክ ቡድን መሪዎች) ቢሆንም የተሿሚው ጀግንነት በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል:: የኢጋሜ ኚያ ሹመት በዋናው ኚያ ወይም በሌላ ሁኔታ በህይወት እያለም ሆነ ሲሞት ሊሻር አይችልም::

## 4.4 የኳር አስተዳደርና የበአለ ሹመት ስነስርዓት ክንዋኔዎች

ከኚያዎች የግዛት ክልል ውጭ ያሉ ቀበሌዎች የሚተዳደሩት በኳሮዎች ሲሆን እያንዳንዱ ቀበሌም የራሱ ኳሮው አለዉ:: የኳር ስልጣን ከአባት ወደ ልጅ በውርስ ይተላለፋል ወይም "አጓም" እየተባለ በሚጠራ ህዝባዊ አመጽ የቀድሞውን ኳር ከስልጣን በማስወገድ በምትኩ ህዝባዊ ድጋፍ ያለው የባላባት ወገን ለኳርነት ይመረጣል:: ኳር ከመሞቱ በፊት ስልጣኑን ማን እንደሚወርስ በመጀመሪያ ለሚቀርበው ወዳጁ በሚስጢር ይናዘዛል:: በሚስጥር የተያዘ ኑዛዜ እስከ ኳር እስተሞት ደረስ ለማንም አይነገርም:: አቶ ሀኪም እንዳሉት *"ኑዛዜው በሚስጢር የሚያዘው በአንድ በኩል በወንድማማቾች መካከል አምባጓሮ እንዳይፈጠር ታስቦ ሲሆን በሌላ በኩል የአንድን ሰው ኑዛዜ ሰውየው ከመሞቱ በፊት ይፋ ማድረግ በእኛዋ ባህል ስለማይፈቀድ ነው"(ታሀሳስ፡8፡1999)*:: ኳሮው እንደሞተ ኑዛዜው ለወራሽ ይነገራል:: በቀብሩ ስነስርዓት ላይም ለህዝቡ ይፋ ይደረጋል:: ኳር ስልጣኑን የሚያወርሰው ለወንድ ልጁ ነው:: ወንድ ልጅ ከሌለው ወንድሙ ስልጣኑን መውረስ ይችላል:: የኳር ስልጣን በውርስ ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ ቢሆንም ለኳርነት ሚያበቁትን መስፈርቶች ያላሟላና የህዝብ ድጋፍ



ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

የሌለው ስልጣን ላይ መቆየት ስለማይፈቀድለት በአጌም (በሀይል ወይም በሰላማዊ መንገድ) ከስልጣን ይባረራል።

በእዚህ ጥናት ክፍል ሁለት ላይ village or band with head man የፓለቲካ ተቋም ባላቸው ማህበረሰቦች ዘንድ አንድ ሰው የመሪነት ሚና የሚኖረው ህብረተሰቡን በአግባብ ማስተባበርና መምራት እስከቻለ ድረስ ብቻ እንደሆነ መገለጹ ይታወሳል:: የኳር አስተዳደር ስርአትም ከእዚህ ጋር ተመሳሳይነት አለው ማለት ይቻላል:: አንድን ኳር በአጌም ከስልጣን ለማውረድ የቀበሌው ህዝብ አብላጫ ድጋፍ መኖር አለበት። በስልጣን ላይ ያለ ኳር ጥፋት ከሰራና ህዝብ ከበደለ በመጀመሪያ ከጥፋቱ እንዲመለስና ህዝቡን በአግባቡ እንዲመራ በአገር ሽማግሌዎች ይመከራል። ምክር ተቀብሎ ጥፋቱን ካረመ በኳርነቱ መቀጠል ይችላል። ምክር ሳይቀበል ቀርቶ ተደጋጋሚ ጥፋት ከሰራና ህዝቡ ትረታ ካደረበት የአገር ሽማግሌዎች ከኳሮው ወንድሞችና እኅቶች ጋር በመሆን ውስጥ ውስጡን ህዝባዊ አመጽ እንዲነሳ ቅስቀሳ ያካሂዳሉ። ህዝቡም ኳሮውን በማግለል፣ ዝናውን በማጉደፍ፣ በማጥላላትና ትብብሩን በመንፈግ ተቃውሞውን ይገልጻል። ተቃውሞው ቀስ በቀስ እየተጠናከረ ሄዶ ኳሮው በሰላማዊ መንገድ ስልጣኑን እንዲለቅ በአገር ሽማግሌዎች ይጠየቃል። ጥያቄውን ተቀብሎ ስልጣን የለቀቀ ኳር እንደማንኛውም ሰው ከህብረተሰቡ ተቀላቅሎ በሰላም መኖር ይችላል። ይህ ሳይሆን ቀርቶ የራሱን ደጋፊዎች በማደራጀት ስልጣኔን አልለቅም ካለ ተቃዋሚው ወገን በሀይል ከስልጣን ያስወግደዋል። በአጌም የተማረከ ኳር ይገደላል። ካልተማረከ ደግሞ ከንተከታዮቹ ወደ ሌላ አካባቢ በመሰደድ የራሱን ግዛት መመስረት ይችላል ወይም በሌላ የኳር ግዛት ካሉ ዘመዶቹ ዘንድ በስደት ይኖራል። አጌም ሲካሄድ ዋናው ነገር የኳር ስልጣን መገለጫ ትዕምርት ተደርጎ የሚታየውን ከበሮ መቆጣጠር መቻል ነው። አንዳንዴ ከበሮ በመንጠቅ ወይም በመስረቅ አጌም ይካሄዳል። በዚህ ሁኔታ አጌም ተካሂዶ ለኳርነት የታጨ ሰው ከበሮውን እየመታ የቀድሞው ኳር ከስልጣን መወገዱን ወዲያውኑ ያውጃል። ከበሮውን የተነጠቀ ወይም የተሰረቀ ኳር በህዝቡ ዘንድ እንደ ኳር አይታይም። ከስልጣን በአጌም የተባረረ ኳር ንብረቱ ተወርሶ ለአዲሱ ኳር ይሰጣል። በአኙዋኮች ዘንድ የኳሮና የኚያዎች ንብረት የህዝብ ንብረት ነው የሚል አመለካከት አለ።

አዲስ የተሾመ ኳር ስልጣኑን በይፋ ሲረከብ "ቡራ" በሚባል ከቤተመንግስቱ ግቢ ውስጥ ባለ ስፍራ ግብዣ አዘጋጅቶ ህዝቡን ይጠራል። ስነስርዓቱ ሲከናወን ኳሮ፣

ባለስልጣናቱና አማካሪ ሽመግሌዎች በተዘጋጀላቸው ልዩ ስፍራ ሲቀመጡ ተራው ህዝብ በጾታና በእድሜ ተከፋፍሎ በአንድ ወገን ይቀመጣል፡፡ አዲሱ ካር በበአለ ሹመቱ ስነስርዓት ላይ በይፋ የሚረከበው ለቀበሌው ህዝብ የጋራ ንብረትና የካር ስልጣን መገለጫ ትእምርት ተደርጎ የሚታየዉን "ቡል ሙ ኡላው" የሚባል ትልቅ ከበሮ ነው፡፡ ከርክክቡ በኋላ አዲሱ ካር ከበሮውን እየመታ አግዋጋ (የጀግና ዘፈን) መዝፈንና መጨፈር ይጠበቅበታል፡፡ ይህን በአግባቡ ከተወጣ ሹመቱ የጸና ይሆናል፡፡ ከበሮ መጫወት ልምድ ከሌለው ከበአለ ሹመቱ ቀን በፊት ከአዋቂዎች ጋር በመሆን ወደጫካ እየሄደ መለማመድ አለበት፡፡ የከበሮ መምታት ስነስርዓት ከተጠናቀቀ በኋላ ባህሉ በሚፈቅደው መርህ መሰረት ህዝቡን ያለ አድሎዎ ለመምራትና ለማገልገል ቃል ኪዳን ይገባል፡፡ ወደ ማምሻው ደግሞ ኚያቱዌል፣ ኝቡር፣ ኝኩጉና የአገር ሽማግሌዎች በጋራ ሆነው ለወራሽ ካር አባቱ ያከናወናቸውን መልካም ተግባራት በመግለጽ የእሱን አርአያ እንዲከተል፣ አባቱ ከዳር ያላደረሳቸው ጉዳዮች ካሉ እንዲፈጽም፣ ህዝቡን በአግባቡ እንዲመራና አጊም ከሚያስነሱ ድርጊቶች እንዲቆጠብ ይመክሩታል፡፡ አጊም ተካሂዶ የተሾመ ካር ከሆነ ደግሞ የቀድሞ ካር የፈጸማቸውን ስህተቶች እንዲያስተካክልና ከህዝቡ ጋር የሚያጋጩ ተግባራትን እንዳይፈጽም ይመከራል፡፡ የስልጣን ርክክብ ከንዋኔ ካበቃ በኋላ የስነስርዓቱ ታዳሚዎች ከድግሱ እየተቋደሱ ሲዘፍኑና ሲጨፍሩ ያመሻሉ፡፡

## 4.5 የቤተመንግስቱ ምድረ ግቢ ገጽታ

የቤተ መንግስቱ ምድረ ግቢ ሰፊና ዙሪያውን በረጃጅም እንጨቶችና የሳሻና ሳር የታጠረ ነው፡፡ ይህ ጥንታዊ የቤተመንግስት አጥር "ኪር" ይባላል፡፡ የአጥሩ ቋሚ እንጨቶች ጫፋቸው ተከርክሞ ያጌጡና የሾሉ ሲሆን በየጫፎቻቸው ላይ የተሰካ የልዩ ልዩ አራዊቶች ቀንድ፣ የዝሆን ጥርስና የቀጭኔ ጭራ ምልክት አለ፡፡ የምልክቶቹ ትዕምርት ግቢው ቤተመንግስት፣ መሪውም ጅግናና አዳኝ መሆኑን የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ በግቢው ዉስጥ ለተለያዩ አገልግሎት የተሰሩ የሳር ቤቶች አሉ፡፡ ልዩ ማረፊያ የኚያ ከሆነ "ዲዲክ" የካር ከሆነ "ኡዲያንግ"፣ መኝታ ቤቱ "ሉል" ፣ መእድ ቤት "አሙአ" ፣ ምግብ ቤት "እጆም" ፣ የሚስቶቹ መኖሪያ "ጋን ዶንግ" ይባላል፡፡ የተለያዩ ስነስርአቶችና የጭፈራ ፕሮግራም የሚካሄድበት መሀል ላይ ያለ ገላጣ ቦታ ደግሞ "ዲቶሩ" ይባላል፡፡ የኚያ አልባሳትና ቁሳቁሶችም የተለየ መጠሪያ ስም አላቸው፡፡ ለምሳሌ የመመገቢያ ሳህን

"አተሃ" ፤ ወጥ ማቅረቢያ "ጎና"፣ ውሃ መጠጫ "ጂም" ፤ ጋያ ማጨሻ "ዲቢሮ" ፤ የቆዳ ምንጣፍ "ቦን"፣ ማንኪያ "ቾያ" ይባላሉ።

## 4.6 የመሪዎችና የህዝቡ ግንኙነት

በመሪዎችና በህዝቡ መካከል ያለው ግንኙነት የገገርና የተገገር አይነት ሳይሆን በጋራ ጥቅምና መተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ነው። ኒያና ኳሮዎች ስልጣን ላይ መቆየት እንዲችላቸው የህዝቡን ፍላጎት ማሟላትና ድጋፍ ማግኘት አለባቸው። ቀደም ሲል እንደተገለጸው መሪዎች ተግባራቸውን መወጣት ካልቻሉና በህዝቡ ቅሬታ ከተፈጠረ እንደም በሰላማዊ መንገድ አሊያም በሀይል ከስልጣናቸው እንዲወርዱ ይደረጋል። በስልጣን ላይ ላሉ መሪዎች ደግሞ ተገቢውን ክብር፣ አገልግሎትና ጥቅም መስጠት ደግሞ ከህዝቡ የሚጠበቅ ማህበራዊ ግዴታ ነው። ለመሪው ተገቢውን ክብርና አገልግሎት ያልሰጠ እንደጥፋቱ መጠን ቅጣት ይጣልበታል። ህዝቡ መሪዎቹን በእርሻ፣ የቤት ስራና የመሳሰሉ ተግባራት ያገለግላል። በጋራ ከሚገኝ የተለያዩ ጠቀማጥቅሞችም በግብር ወይም በስጦታ መልክ ለመሪዎቻቸው ያካፍላል። የታደኑ አውሬዎች ቆዳ (ለምሳሌ የነብር፣ የአንበሳ፣ የጎሽ)፣ የቀጭኔ ጭራና የዝሆን ጥርስ ለመሪዎች በስጦታ ይበረከታል። ለመሪዎች የሚሰጡ ስጦታዎች ወይም ጥቅማ ጥቅሞች «ኡሩዋ» በመባል ይጠራሉ።

መሪዎች ደግሞ በግብር ወይም በስጦታ መልክ ከሚያገኙት ሀብትና ንብረት ላይ ህዝቡን በተለያየ መልክ ተጠቃሚ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ይህንን ለማድረግ ደግሰው ህዝቡን ያበላሉ፣ ታዋቂና ጀብዱ የሰሩ ሰዎችን ይሸልማሉ፣ ለተቸገሩ ጥሉሽ ሰጥተው ይድራሉ፣ የታመሙና አቅመ ደካሞችን ይረዳሉ ወዘተ። ኒያና ኳሮ ህዝቡን ግብር የማብላትና የጭፈራ ፕሮግራም የማዘጋጀት ኃላፊነት ስላለባቸው ለዚሁ ተብሎ የተከለለ ቦታ በግቢያቸው አለ። በጭፈራ ጊዜ ኳሮ ከህዝቡ ፊት ቀርቦ ይጨፍራል። ህዝቡም በተራው ኳሮን እያሞገሰ ይጨፍራል። ኳሮ ከህዝቡ ፊት ሆኖ የሚጨፍረው ለህዝቡ ያለውን ታማኝነትና መልካም ግንኙነት ለመግለጽ ነው። እኘዋዎች ለሙዚቃና ለጭፈራ ልዩ ፍቅር እንዳላቸው አቶ ኡፒየው አኩሪ እንዲህ ሲሉ ገልጸውልኛል።

> እኛ እኘዋዎች ሁሌም ቢሆን በሰላም መኖር እንፈልጋለን። በአካባቢያችን ሰላም ካለ፣ እዝመራው ካማረ ሁሌም መደሰትና መጨፈር የቆየ ባህላችን

ነው። የሰው ልጅ ሰላም ካገኘ፣ ከበላና ከጠጣ መጨፈር፣ መደሰት አለበት። በእኛ ባህል አዘውትረን የጭፈራ ፕሮግራም እናዘጋጃለን። ወጣቶችም የራሳቸውን የጭፈራ ፕሮግራም የሚያዘጋጁበት ስርዓት አለ ። ኳሮዎችም በባህላችን መሰረት የጭፈራ ፕሮግራም ያዘጋጃሉ። በድሮ ባህላችን መሰረት የጭፈራ ፕሮግራም ለማዘጋጀትና ክበር ለማግኘት የኳር ፍቃድ መኖር ነበረበት። አሁን ግን ማንም በፈለገ ጊዜ ወዳጅ ጓደኞቹን አሰባስቦ መጨፈር ይችላል። ለሙዚቃና ለጭፈራ ያለን ፍቅር ዛሬም በልጆቻችን ዘንድ ያስተዋላል። (ታህሳስ 16፣1999)

እኝዋዎች ለኚያና ለኳሮዎቻቸው ያላቸውን ክብር በተመለከተ በቡድን ውይይት ወቅት ተሳታፊ የነበሩ አቶ ሀኪም ኡፓራ፣ ኝጎዎ አበላና ኡጉታ አዲው እንደገለጹልኝ ማንኛውም የተበሉ ነዋሪ ባህሉ በሚፈቅደው መሰረት ለኚያውና ለኳር ክብር መስጠት አለበት። ኚያ ወይም ኳር ከግቢው ውጭ ሲዘዋወር ወንዶች አጎንብሰው ሴቶች ደግሞ ተንበርክከው ሰላምታ በመስጠት አክብሮታቸውን የመግለጽ ባህላዊ ግዴታ አለባቸው። በመሪዎቹ መኖሪያ ግቢ ውስጥ ከሆነ ወንዶችም በጉልበታቸው ተንበርክከው ሰላምታ በማቅረብ አክብሮታቸውን ይገልጻሉ። ማንኛውም ኚያ ወይም ኳር ያለጫማ ባዶ እግሩን መታየት የለበትም። ያለጫማ መታየት እንደነውርና ክብርን ዝቅ ማድረግ ተደርጎ ይታያል። በአሁኑ ጊዜ የክልልና የወረዳ አስተዳዳሪዎችን እኝዋዎች ኳር እያሉ ይጠሩዋቸዋል። ስያሜው ከባህላዊ አስተዳዳሪዎች መጠሪያነት ባለፈ በዘመናዊ የአስተዳደር ስርዓት ውስጥ ገብቶ የአስተዳዳሪዎች መጠሪያ ስም ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል።

## 5. ዋና ዋና የግጭት መንስኤዎችና ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች በእኘዋ ብሔረሰብ

ይህ ክፍል ማትኮሩ ያደረገው የእኘዋ ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን ፣ ተቋማትን ፣ የተቋማቱን አሰራርና የቅጣት አይነቶችን ሲሆን በቅድሚያ ግን ዋና ዋና የሚባሉ የግጭት ምክንያቶች ቀርበዋል።

### 5.1 ዋና ዋና የግጭት መንስኤዎች

የግጭት አፈታት ዘዴዎችን ለመመልከት መንስኤዎችን በቅድሚያ ለይቶ ማወቅ ለግንዛቤ ይረዳል። እኘዋዎች በመካከላቸውና ከሌላ አጎራባች ቀበሌዎችና ብሔረሰቦች ጋር የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች የተለያዩ እንደመሆናቸው የግጭት መንስኤዎችንም ከዚሁ አንጻር መመልከት ተገቢ ነው።

ከደጋማው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ተነስተው ወደ ቆላማው የጋምቤላ ክልል የሚፈሱ ወንዞችን ተፋሰስ ተከትለው መንደሮቻቸውን የመሰረቱ እኘዋዎች የእርሻ ስራን የሚያከናውኑት የወንዞቹን ግራና ቀኝ ተከትለው ነው። በአነስተኛ የእርሻ ማሳቸው ኋላ ቀር የአመራረት ዘዴን የሚጠቀሙ ሲሆን የወንዝ ሙላት በሚቀንስበት የበጋ ወራት ደግሞ በውሃ ሸሽ መሬት ላይ የእርሻ ስራን ያከናውናሉ። በበጋው ወራት ውሃ ሸሽ መሬቶች በእኘዋ ገበሬዎች ዘንድ እጅግ ተፈላጊ በመሆናቸው በመሬት ይዞታዎል ምክንያት አልፎ አልፎ ግጭቶች ሲከሰቱ ይስተዋላል።

እኘዋዎች የሰብል አመራረት ዘዴያቸው ባህላዊና ኋላቀር በመሆኑ አንዳንድ ገበሬዎች ቤተሰቦቻቸውን ከአመት እስከ አመት ሊቀልብ የሚችል ሰብል በአንድ የምርት ዘመን ለማምረት አይችሉም። በወንዞች ዳርቻ የሚገኙ ውሃ ሸሽ መሬቶችን በመጠቀም በአመት ሁለቴና ሶስቴ ማምረት ያልቻሉ እኘዋዎች የምግብ እህል ፍለጋ በአጎራባች ቀበሌዎች ላይ ዝርፊያ የሚያካሂዱበት ጊዜ አለ። ኒያና ኳሮዎች በስልጣናቸው ለመቆየት የሚያስችል የህዝብ ድጋፍ የሚያገኙት በዋናነት ለጋስ፣ ህዝቡን ግብር ማብላትና የተቸገሩትን መረዳት ከቻሉ ነው። ይህን ማድረግ ካልቻሉ መገለልና ከስልጣን የመባረር እጣ ስለሚገጥማቸው ለድግስና ለተቸገሩ መርጃ የሚሆን

እህል ፍሊጋ ዝርፊያ የሚያካሂዱበት አጋጣሚዎች አሉ፡፡ ይህ አይነቱ ሁኔታ በተለይ በዱር ጊዜ በቀበሌዎች መካከል ለሚከሰቱ ግጭቶች ዋና ምክንያት እንደነበር አቶ ኘጎም አበላ ገልጸውልኛል (ታህሳስ 18፤1999)፡፡

በአንድ አካባቢ መንደር መስርተው የሚኖሩ አኝዋዎች በጎሳ፣ በዝምድናና በትውውቅ የጠበቀ ትርርብ ያላቸው፣ እርስ በእርስ የሚረዳዱ፣ ጥቃትን በጋራ የሚከላከሉና በሌሎች ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶችም የተሳሰሩ ናቸው፡፡ ይህ የመንደር አመሰራረታቸውና የአኗኗር ባህላቸው በቀበሌዎች መካከል ለሚከሰቱ ግጭቶች እንደ አንድ ምክንያት የሚታይበት ሁኔታ አለ፡፡ ይሄውም የአንድ መንደር ነዋሪ በሌላኛው መንደር ነዋሪ ከፍተኛ የሆነ ጥቃት ደረሰበት ማለት ጉዳዩ መንደርተኛውን ሁሉ የሚያስቆጣበት ጊዜ መኖሩ ነዉ፡፡ እንዲህ ያለ ሁኔታ ሲከሰት ጥቃት ያደረሰውን ግለሰብ ብቻ ሳይሆን በመንደርተኛው ላይ የተጠቂው ወገን ቀበሌ ብቀላ ይፈጽማል፡፡ ይህንን መሰሉ ግጭት እርቅ እስከሚወርድ ድረስ ማብቂያ የለውም፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን እንዲህ ያለው ግጭት ጎልቶ እንደማይስተዋል አቶ ኡጉታ አዲው ገልጸውልኛል (ታህሳስ 8፤1999)፡፡

በአኙዋዎች ዘንድ ድሙኝ (ለጥሎሽ የሚሰጥ የአንገት ጨሌ) ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠው የሀብትና የክብር መገለጫ ነው፡፡ ከ1966 እ.ኢ.አ በኋላ ግን የባህል አብዮት በሚል አንዳንድ ልማዶች (ለምሳሌ የፊት ጥርስ ማውለቅ፣ ጋያ ማጨስ፣ የባዕድ አምልኮ፣ የድሙኝ ጥሎሽ ወዘተ) እንዲቀሩ በተደረገ ሙከራ ጥሎሽ በገንዘብ እየተተካ በመምጣቱ የድሙኝ ዋጋ እየቀነሰ ቢመጣም ዛሬን ድረስ ራቅ ባሉ የገጠር አካባቢዎች ድሙኝ ከፍ ያለ ዋጋ አለው ፡፡ ስለዚህ ወጣቶች ትዳር ለመያዝ የሚያስፈልጋቸውን ድሙኝ ወይም ገንዘብ ሲያጡ ዘረፋ የሚያካሂዱበት ጊዜ አለ፡፡

ከጋብቻ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች የሚፈጠሩ ግጭቶች ዛሬም ቢሆን በስፋት ሲከሰቱ ይስተዋላል፡፡ በአኙዋ የጋብቻ ባህል መሰረት ባል ለሚስት ቤተሰብ ጥሎሽ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡ ከጋብቻ በፊት ወሲባዊ ግንኙነት መፈጸም በአኙዋ ባህል የተከለከለ ባይሆንም ማርገዟ የታወቀባት ሴት ግን ከማን እንዳረገዘች በአባቷና በወንድሞቿ ትጠየቃለች፡፡ ከማን እንዳረገዘች ከታወቀ ሰውየው በባህሉ መሰረት ጥሎሹን እንዲከፍል ይጠየቃል፡፡ ይህ ከሆነና ጥሎሹን መክፈል ካልቻለ ወይም

ጥያቄውን ተቀብሎ ምላሽ ካልሰጠ በልጅቷ ቤተሰብ ወይም ዘመዶች ተይዞ ስውነቱ እስኪቆስል በግርፋት ይቀጣና ጥሎሹን እንዲከፍል እንደገና ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ይለቀቃል።

ከትዳሯ ውጭ ስትማግጥ (ወሲባዊ ግንኙነት ስትፈጽም) የተገኘችን ሚስት ባልየው ከእንግዲህ አልፈልግሽም ብሎ መፍታት ከፈለገ ሲያገባት ለወላጆቿ የከፈለውን ጥሎሽ እንዲመልሱለት የመጠየቅ መብት አለው። መፍታት ካልፈለገ ደግሞ ሚስቱን በአገር ሽማግሌዎች አስመክሮና አስጠንቅቆ ያማገጣት ሰው ካሳ እንዲከፍለው መጠየቅ ይችላል። ያማገጣት ሰው ጥፋቱን አምኖ ካሳውን ለመክፈል አሻፈረኝ ካለ ጉዳዩ በአገር ሽማግሌዎች እንዲታይ ይደረጋል።

በተደጋጋሚ ሲከሰቱ የሚታዩ ችግሮች ከትዳርና ከስካር ጋር የተያያዙ ናቸው። በአኝዋዎች ዘንድ አረቂ ፣ "ቦርዴ" ፣ "አታርቡብ" እና "ኡጎሊ" የሚባሉ ባህላዊ መጠጦች በስፋት ይዘወተራሉ። በመሸታ ቤቶችም ሆነ በጭፈራ ፕሮግራሞች ላይ በስካር መንፈስ የሚነሱ ግጭቶች ከመለስተኛ እስከ ከፍተኛ የሚደርሱ ናቸው። አቶ ኡጉታ እንዳሉት "በስካር መንፈስ በሚነሱ ግጭቶች ወጣቶች በቡድንና በሰፈር ተከፋፍለው ድብድብ የሚገጥሙበትና የአካል ጉዳት የሚደርስበት ጊዜ አለ" (ታህሳስ 16፣1999)።

በአኝዋዎችና አጎራባች ብሔረሰቦች መካከል በተለያዩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ግጭቶች ሲከሰቱ ኖረዋል። በተለይ አኝዋዎችና ኑዌሮች ለረጅም ዘመናት በበላንጣነት የሚታዩ በመሆናቸው በመካከላቸው በሚነሱ ግጭቶች በርካታ የህይወትና የንብረት ጥፋት ደርሶአል። ይህን በተመለከተ አቶ ኝጎዎ አበላ የሚከተለውን በምሳሌነት ጠቅሰውልኛል።

> በ1977 እ.ኢ.አ በአኮቦ ወረዳ የሚኖሩ ኑዌሮች በአጎራባቾቻቸው የጆር ወረዳ ቀበሌዎች የሚኖሩ አኝዋዎችን ወርረው እስከ 25 የሚሆኑ ሰዎች (ቁጥሩን በግምት ነው የነገሩኝ) ገድለዋል። በርካታ ከብቶችንም ዘርፈዋል። በ1985 እ.ኢ.አ ደግሞ በኢታንግ አካባቢ የሚኖሩ ኑዌሮችና አኝዋዎች መካከል በተፈጠረ ግጭት ከሁለቱም ወገን የሰው ህይወት ጠፍቶአል

(የሞቱትን ሰዎች ቁጥር በውል አላስታውስም ብውኛል):: ችግሩ ወደ ከፋ ደረጃ እንደይሸጋገር የአኮቦና ጆር ወረዳ መስተዳድር ከአገር ሽማግሌዎች ጋር በመሆን ግጭቱ በሽምግልና እንዲበርድ ተደርጓል:: (ታህሳስ 22፤1999)::

ባሬም ቢሆን በአኝዋና በኑዌር ብሔረሰቦች መካከል የሰመረ ግንኙነት ባለመኖሩ ለክልሉ ሰላምና ጸጥታ መናጋት እንደ አንድ ምክንያት ይታያል:: በሁለቱ ብሔረሰቦች መካከል ለሚከሰቱ ግጭቶች አንዱና ዋነኛው ምክንያት ኑዌሮች ለግጦሽና ለእርሻ የሚሆን መሬት ፍለጋ ወደ አኝዋዎች የግዛት ክልል ዘልቀው በመግባታቸው እንደሆነ አቶ ኝንም አበላ ነግረውኛል:: ኑዌሮች በከፊል አርብቶ አደር በመሆናቸው በተለይ በበጋው ወራት ለከብቶቻቸው የግጦሽ ሳር ፍለጋ አኝዋዎች በሚኖሩባቸው ስም አካባቢዎች ይሰማራሉ:: ሁለቱ ብሔረሰቦች ቀድሞውንም በባላንጣነት የሚተያዩ በመሆናቸው አኝዋዎች ወደ ክልላቸው ዘልቀው ከገቡ ኑዌሮች ጋር ተዋግተው ወደ መጡበት ይመልሱዋቸዋል:: ይህንን ለማድረግ ሀይል ካጠራቸው ደግሞ አካባቢውን ለቀው ወደ ሌላ በመሄድ መንደር መስርተው ይኖራሉ:: ከቀበሌያቸው ተሰደው ወደ ሌላ ቦታ በመሄድ መንደር መስርተው መኖር የጀመሩ አኝዋዎችም እርቅ እስካልተደረገ ድረስ ኢታንግ ጠብቀው ከመኖሪያቸው ያፈናቀሉዋቸውን ኑዌሮች የሚበቀሉበት ጊዜ አለ:: እንዲህ ያለው ሁኔታ ከጥንት ጀምሮ በተደጋጋሚ ሲከሰት የኖረ ነው በማለት አቶ ኡትታ አንድ የቅርብ ጊዜ ክስተት ነው ያሉትን እንዲህ ሲሉ ተርከዉልኛል::

> በ1994 እ.ኢ.አ በኢታንግ ወረዳ የሚገኙ ፓቴክ፣ ፒኝሞ፣ ብርሃንና ሰላም፣ ቻም፣ ኝኳሊና ኢዲኒ በሚባሉ የአኝዋ ቀበሌዎች ላይ አጎራባች ኑዌሮች ጥቃት አድርሰው አኝዋዎች ወደ ጋምቤላ ወረዳ ኢሊያ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ተሰደው ነበር:: በግጭቱ በርካታ ቤቶችም ተቃጥለዋል:: ወደ ኢሊያ የተሰደዱ አኝዋዎችም ነገሩ እስኪበርድ ለተወሰኑ ወራት በመጠለያ ካምፕ ከኖሩ በኋላ መንግስት በጉዳዩ ጣልቃ ገብቶ ከአገር ሽማግሌዎች ጋር በመሆን ችግሩ በሽምግልና እንዲፈታ ተደርጓል:: ተፈናቃዮችም በክልሉ መንግስት መቋቋሚያ ተሰጥቶአቸው ወደየ ቀበሌዎቻቸው ለመመለስ ችለዋል (ታህሳስ 20፤1999)::

በ1977 እ.ኤ.አ ጀምሮ በርካታ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያዊያን ከአኝዋዎች እውቅና ውጭ በሰፈራ ፕሮገራም አኝዋዎች በሚኖሩበት አካባቢ እንዲሰፍሩ ተደርጎአል። አኝዋዎች በሚኖሩበት አካባቢ ባለ የስደተኞች ካምፕ የሚኖሩ የሱዳን ስደተኛ ኑዌሮች ቁጥርም ከፍ ያለ ነው። ይህን በተመለከተ ኩራሞቶ እንዳለዉ " *Another group of outsiders, that is 65,000 settlers mainly composed of the Tigre, Amhara and Kambata, were settled in Anyuaa land by the socialist Ethiopian government. By the begining of 1991 most of them had either died or fled (1992:7).* ቀደም ሲል እንደተገለጸው እነዚህ ሰፋሪዎች ከአኝዋዎች ፍላጎት ውጭ እነሱ በሚኖሩበት መሀል መስፈራቸው ቅሬታን ፈጥሮአል፣ ጥቃት ያደረሱበትም ጊዜ አለ። በክልሉ ይንቀሳቀስ ከነበረው የደቡብ ሱዳን ነጻ አውጪ ግንባር (SPLA) ጋር በተፈጠረ አለመግባባትም ተደጋጋሚ ግጭቶች ተከስተዋል።

እኛ የአካባቢው ነባር ተወላጆች ነን የሚል ስሜት በአንዳንድ አኝዋዎች ዘንድ ይንጸባረቃል። አንዳንድ ኑዌሮችንም እንደ ሱዳናዊያን የማየት አዝማሚያ ይስተዋላል። ኑዌሮች ደግሞ አኝዋዎች ስለ እነሱ ባላቸው አመለካከት ቅሬታ አላቸው። በተፈጠው ፌደራላዊ የክልል መስተዳድር የስልጣን እርከኖች ላይም ጎልተው መታየትን ይሻሉ።ለዚህ ማስረጃ የሚሆን አብርሃም ሰውነት የሚከተለውን ጽፎአል "*Who should control the regional government lies at the heart of the competition. The political crisis is compounded by competition over natural resources, uneven distribution of social services, and administrative offices" (2003:541).* በእነዚህና እነዚህን መሰል ምክንያቶች በሁለቱ ቤሔረሰቦች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶች ለክልሉ ሰላም መናጋት እንደ ምክንያት የሚጠቀሱ ናቸዉ።

## 5.2 ካርሱክ - የአኝዋ ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋም

ምክንያታቸው ምንም ይሁን ምን አኝዋዎች ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ የሚፈቱበት ሀገረሰባዊ ተቋም "ካርሱክ" ይባላል። ካርሱክ የሁለት ቃላት ጥምር ሲሆን "ካር" የችሎት ቦታ "ሱክ" ደግሞ መካሰስ፣ መደራደር፣ መወያየትና ለግጭቶች መፍትሄ መስጠት ማለት ነው። የካርሱክ ትርጉምም ሀገረሰባዊ የችሎት ቦታዎችና በእነዚህ



ILS LIBRARY

መናኛ ተቋማት መጠሪያ ሲሆን እንደ ግጭቶች አይነትና መጠን በተለያዩ ደረጃዎች የተቋቋሙ የካርሉክ አይነቶችም አሉ። ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቦአል።



የሽምግልናና ዕርቅ ሥነስርአት የሚከናወንበት ካርሉክ ይህንን በመሰለ የዛፍ ጥላ ስር ነው።

## 5.2.1 የችምትና ቡራ ካርሉክ

የችምትና ቡራ ካርሉክ ተመሳሳይ ሲሆን በኚያ የአስተዳደር ስርዓት ያለው "ችምት" በኳር ደግሞ "ቡራ" ይባላል። የችምትና ቡራ ካርሉክ ችሎት በባህላዊ የአስተዳደር ስርአቱ ደንብና ህግ መሰረት የሚከናወነው በመሪዎች ግቢ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ቦታ ሁሉ እየተሰራበት ይገኛል። እነዚህ ተቋማት እንደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለሚቆጠሩ በተቋሙ የሚታዩ ጉዳዮችም የግድያና ከፍተኛ የሚባሉ አንዳንድ ወንጀሎች ብቻ ናቸው። ኚያና ኳሮ የተቋሙን እንቅስቃሴ በቅርብ ሆነው ከመከታተል ውጪ በፍትህ ስርዓቱ ጣልቃ ገብተው ተጽዕኖ ማሳረፍ አይችሉም። በዳኝነትና ሽምግልና ተግባራት የሚሳተፉት ኝቡር (ሰብሳቢ)፣ ኛቱዌል (መረጃ አሰባሳቢ) እና ኝኩን የሚባሉ የአስተዳደሩ ከፍተኛ ባለስልጣናት፣ ካይአቱት (የስፈር ካርሉክ ሰብሳቢ ዳኛ) እና ጃይ የሚባሉ አማካሪ የአገር ሽማግሌዎች ናቸው።

በቅርብ ሆነው ከመከታተል ውጪ በፍትህ ስርዓቱ ጣልቃ ገብተው ተጽዕኖ ማሳረፍ አይችሉም። በዳኝነትና ሽምግልና ተግባራት የሚሳተፉት ኸቡር (ሰብሳቢ)፣ ኛቱዌል (መረጃ አሰባሳቢ) እና ኸኩን የሚባሉ የአስተዳደሩ ከፍተኛ ባለስልጣናት፣ ኪይአቱት (የሰፈር ካርሱክ ሰብሳቢ ዳኛ) እና ጃይ የሚባሉ አማካሪ የአገር ሽማግሌዎች ናቸው። ጎሉቱን ተቀምጠው የሚከታተሉና የሚታዘቡ "ልዋኮችም" (ነጠላ ከሆነ "ልዋክ" ይባላል) በስንስርዓቱ ላይ ተሳታፊ መሆን ይችላሉ። በእነዚህና ወደ ኋላ በምንመለከታቸው የካርሱክ አይነቶች ላይ የሚሳተፉ ጆዶንጎዎች (የአገር ሽማግሌዎች) ላይ አኝዋዎች ከፍተኛ የሆነ እምነት እንዳላቸው አቶ ኛጎዎ አበላ እንዲህ ሲሉ ነግረውኛል።

> የጆዶንጎ አባላት በእድሜ የበለጸጉ፣ በአስታራቂነት ስራ ልምድ ያላቸው፣ ለህብረተሰቡ ሰላምና ጸጥታ ተግተው የሚሰሩ፣ የማያዳሉ፣ ተስሚነት ያላቸው፣ እንደቡተ ርቱእና ህዝባዊ አደራ እንደተጣለባቸው ጠንቅቀው የተገነዘቡ ናቸው። ይህ አደራ እንደተጣለባቸው ስለሚያውቁ የአኝዋ ጆዶንጎዎች ያለምንም አድሉዎ ህብረተሰቡን በመዳኘት ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ሲያደርጉ ኖረዋል (ታህሳስ 9 ፣ 1999 )።

በአስተዳደሩ ከተሰየሙት ጆዶንጎዎች አባላት በስተቀር ሌሎች ጆዶንጎዎች የሚመረጡት በአካባቢው ህዝብ ነው። ምርጫው ሲካሄድ ነዋሪዎቹ ተሰባስበው ስለ እያንዳንዱ እጩ ባህሪያት፣ ተግባርና ስብዕና በሚገባ ከተወያዩ በኋላ መስፈርቱን የሚሉና አብላጫ ድምጽ ያገኙ እንዲመረጡ ይደረጋል። የምርጫ መስፈርቶቹም በአካባቢው ነዋሪ የሆነ ፣ በመልካም ስነምግባሩ የታወቀ፣ በጦርነት ጊዜ ደፋርና ጀግና መሆን የተመሰከረለት፣ ያለምንም ማወላወልና አድሉ ህብረተሰቡን ማገልገል የሚችል፣ የማስታረቅ ጥበብና ክህሎት ያለው፣ ተናግሮ የማሳመን ችሎታ ያለው እንደቡተ ርቱዕ የሚሉት ናቸው። በእነዚህ መስፈርቶች የተመረጡ ጆዶንጎዎች በእድሜ መግፋትና በጤና መታወክ ወይም በስነምግባር ጉድለት ከስራቸው እንዲነሱ ካልተደረገ በስተቀር የዳኝነትና የሽምግልና ስራን እንዲያከናውኑ በቋሚነት የሚመረጡ ናቸው። በካርሱክ ተቋማት ሌቶች የመምረጥም ሆነ የመመረጥ መብት የላቸውም። ማናቸውም ተግባራት የሚከናወኑት በወንዶች ብቻ ነው። የችሎት ስነስርዓቶችን ለመከታተል ከፈለጉ ግን ክልከላ የለባቸውም።



ILS LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY



የሽምግልና ስነስርአት ሲጀመር የጆዶንጎቹ ሰብሳቢ ስለተፈጠረው ሁኔታ ለታዳሚዎች ማብራሪያ ሲሰጡ

### 5.2.1.1 የችምትና ቡራ ስነስርዓት ሂደትና ክንዋኔዎች

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በችምትና ቡራ የሚታዩ ጉዳዮች በአብዛኛው የግድያ ወንጀሎች ናቸው። በእኘዋ ልማዳዊ ህግ መሰረት በማንኛውም ሁኔታ ሰው የገደለ ፈጥኖ እጁን ለአካባቢው ኚያ ወይም ኳር መስጠት አለበት። ዘመዶቹም በሟች ወገኖች አደጋ እንዳይደርስባቸው ወደ ኚያ ወይም ኳር ግቢ መጥተው እንዲጠለሉ በአስቸኳይ መልዕክተኛ ይላካል። ስለወንጀሉ ቀድመው ከሰሙም ፈጥነው ወደ አካቢያቸው መሪ መጥተው በመሰባሰብ ሊደርስባቸው ከሚችል አደጋ እራሳቸውን መጠበቅ አለባቸው። በመሪዎች ግቢ ገብቶ ማንም ሰው የሀይል እርምጃ መውሰድ አይችልም። ይህን የፈጸመ መሪውንና ባህሉን እንደደፈረ ተቆጥሮ ቅጣት ይደርስበታል። እርቅ እስኪደረግ ገዳይና ዘመዶቹ በተጠለሉበት ይቆያሉ። ስለሟች አሟሟት ሁኔታም በአስቸኳይ የማጣራት ስራ ይጀመራል። የማጣራት ስራው የሚከናወነው በጆዶንጎዎች ሲሆን ኚያው ወይም ኳሮዉ ደግሞ ጉዳዩን ከበላይ ሆኖ ይከታተላል። ጆዶንጎዎችም ስላከናወኑት ተግባር ለኚያ ወይም ኳር ሪፖርት ያደርጋሉ።

ስለወንጀሉ አፈጻጸም የሚደረግ ማጣራት የተወሰኑ ቀናት ቢፈጅም ሁኔታውን ለማጋገብና የሟች ወገኖችን ለማረጋጋት ሲባል ገዳይ እጁን በሰጠ ጥቂት ቀናት ውስጥ ከየሰፈሩ ከጆዶንጎዎች ጋር በመሆን የገዳይና የሟች ወገኖችን በችሎት/ቡራ ፊት ለፊት እንዲገናኙ «ቶቺንግ» (የእርቅ ስነስርአቱ የመጀመሪያ ምዕራፍ) ይካሄዳል። በዚህ ስነስርአት ላይ ገዳይ በሰራው ወንጀል መጸጸቱንና ይቅርታ መጠየቁን ለመግለጽ ሁለት እጁን በገመድ ወይም በልጥ ሽብ ተደርጎ ካርሱክ ይቀርባል። ወንጀል የፈጸመበትን ጦርም ለአገር ሽማግሌዎቹ ያስረክባል። ወንጀል የፈጸመበትን ጦር ለአገር ሽማግሌዎች የሚያስረክብበትን ምክንያት አቶ ኡትታ አዲው እንዲህ ሲሉ ነግረውኛል «ገዳይ ወንጀሉን የፈጸመው ጦር ስለያዘ ነው። ጦር ባይኖረው ኖሮ የሰው ሕይወት አያጠፋም ነበር። ስለዚህ የሰው ህይወት የጠፋበትን ጦር ከእንግዲህ በእጁ እንደማይዝና ዳግመኛ ተመሳሳይ ድርጊት እንደማይፈጽም በአገር ሽማግሌዎች ፊት ቃል ስለመግባቱ ገላጭ ትዕምርት ነው» (ታህሳስ 16፤1999)።

ገዳይ በፈጸመው ወንጀል መጸጸቱን ለመግለጽ ሁለት እጁን በልጥ ወይም በገመድ ሽብ ተደርጎ በቶቺንግ ላይ ከቀረበ በኋላ ኚያው ወይም ኳሮው ወይም የጆዶንጎዉ ሰብሳቢ ይህንኑ የገዳይ በድርጊቱ መጸጸትና ይቅርታ መጠየቅ በተመለከተ በስነስርዓቱ መክፈቻ ላይ ለሟች ወገኖች በማስረዳት ከሀዘናቸው እንዲጽናኑና ችግሩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ሁለቱም ወገኖች እንዲተባበሩ ይጠይቃል። የገዳይ ወገኖችም ይቅርታ መጠየቃቸውን ለመግለጽ እንባ ማድረቂያ በሚል የተወሰኑ የወግ እቃዎችና ንብረቶችን (ለምሳሌ በአንገት የሚጠለቅና ለጥሉሽ የሚሰጥ ድሙኝ የሚባል ዉሌ፣ ጦር፣ ጋር የሚባል በጭፈራ ጊዜ በእግር ላይ የሚታሰር ቃጭል፣ የተለያዩ የዉሌ ንግ ንጦች ወዘተ) ለሟች ወገን ይሰጣሉ። የቶቺንግ ስነስርዓት የሚካሄድበት ዋና ምክንያት ቀደም ሲል ከተገለጸው በተጨማሪ ተመጣጣኝ የሆነ የደም ካሳ ተከፍሎ ችግሩን በሽምግልናና በእርቅ ለመፍታት ከስምምነት ላይ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ ነው። ከዚህ በኋላ ዋናው የእርቅ ስነስርአት የሚደረግበትን ሁኔታ የሚያመቻቹት የችሎት ወይም ቡራ ጆዶንጎዎች ናቸው።

ጆዶንጎዎች በቂ ጊዜ ወስደው ስለወንጀሉ አፈጻጸም ተጨማሪ ማጣራት ካደረጉ በኋላ ለኚያ ወይም ኳሮ ሪፖርት ያቀርባሉ። በመቀጠልም የገዳይና የሟች ወገኖችን

በተዋት ወይም ቡሩ ላይ ጠርተው እንደገና ክርክርና ውይይት ይደረጋል። ይህንን በተመለከተ አቶ ሀኪም ኡፓራ እንዳሉት «ክርክርና ውይይቱ በዋናነት የሚያተኩረው ስለካሳው አይነትና መጠን ላይ ነው። ስለወንጀሉ አፈጻጸም ሁኔታ የምስክርነት ቃላቸውን የሚሰጡ ሰዎች ካሉም መስጠት ይችላሉ። የምስክሮች ቃል የሚሰማው ስለወንጀሉ አፈጻጸም ተጨማሪ ማስረጃዎችን ለማግኘት ሲባል ነው» (ታህሳስ 19፣1999)። በዋናው የእርቅ ቀን የሁለቱም ወገን ተወካዮችና ገዳይ ተሟልተው መገኘት አለባቸው። ተሟልተው መገኘታቸው ካልተረጋገጠ ጆዶንጎው ስራውን አይጀምርም። ስነስርዓቱ ሲካሄድ የገዳይና የሟች ወገን፣ ምስክሮችና ታዳሚዎች የሚቀመጡት ከጆዶንጎዎች ግራና ቀኝ ክብ ሰርተው ነው። ከመሀል ላይ ደግሞ ገዳይና ከሟች ወገን የተወከለ ሰው ጎን ለጎን ሆነው ይቀመጣሉ። አረንጓዴ ቅጠል፣ ሟች የተገደለበት ጦር ወይም አምሳያው፣ የበቆሎ ወይም የማሽላ ዱቄትና አንድ ድንጋይ ደግሞ ከጆዶንጎዎች ፊት ለፊት ይቀመጣል። አረንጓዴው ቅጠል ግጭቱን በመግባባት መንፈስ እንደሚፈቱ ያላቸውን ተስፋና ምኞት መግለጫና የሰላም ትዕምርት ተደርጎ የሚታይ ነው (የተቀሩት ቁሳቁሶች ትምዕርት በገጽ 64 ተርቦአል)። ሁሌም እንደሚደረገው ስነስርዓቱ ሲጀመር ሰብሳቢው ዳኛ ስለተከሰተው ሁኔታ ዝርዝር ማብራሪያ በመስጠት ሁለቱም ወገኖች በመቻቻልና በመግባባት መንፈስ ችግሩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት እንዲተባበሩ ይጠይቃል። በመቀጠልም በካርሎክ ደንብ መሰረት የምስክሮች ቃልና የታዳሚዎች አስተያየት ካለ ይደመጣል። ምስክሮችና አስተያየት ሰጪዎች ሲናገሩ በጥሞና ከማዳመጥ ውጭ ማንም ሰው ጣልቃ እየገባ ማወክና የተናጋሪውን ሀሳብ አቅጣጫ ማስለወጥ አይችልም። እንዲህ ያለው ሁኔታ ድንገት ቢከሰት የጆዶንጎው ሰብሳቢ ጣልቃ ገብቶ ስነስርአት የማስጠበቅ ግዴታ አለበት። የምስክሮች ቃልና ከታዳሚዎች የሚሰጥ አስተያየት እንዳበቃ የጆዶንጎው ሰብሳቢ የተደረሰበትን የ"ጃፓ ኩምር" (ካሳ) ውሳኔ አይነትና መጠን ይፋ ያደርጋል።



በኢርቅ ሥነስርአቱ ላይ ገዳይና የሟች ተወካዮች በዚህ ሁኔታ ጎን ለጎን ይቀመጣሉ

የካሳ ክፍያው አይነትና መጠን ከተገለጸ በኋላ የገዳይና የሟች ወገን በውሳኔው ላይ ያላቸውን አስተያየት ይጠይቃሉ። የሟች ወገኖች ካሳው ያንሳል ብለው የመከራከር መብት ቢኖራቸውም ፍትሀዊ ዳኝነት አልተሰጠንም ብለው ከጆዶንጎው ሀሳብ የሚያፈነግጡ አሊጋጠሙኝም ሲሉ አቶ አቡላ ኡመድ አረጋግጠውልኛል። የገዳይ ወገኖችም እንዲከፍሉ በተወሰነባቸው የካሳ መጠንና አይነት ላይ ተነጋግረው ተቀብለናል ወይም በዝቶብናልና አስተያየት ይደረግልን ብለው መጠየቅ ይችላሉ። የካሳው መጠንና አይነት በዝቶብናል ወይም አንሶናል በሚል አለመግባባት ከተፈጠረ ጆዶንጎዎች ሁለቱንም ወገን በተናጥል አነጋግረው ወደ ስምምነት እንዲመጡ ይደረጋል። በዚህ ሁኔታ ድርድር ተደርጎ ከስምምነት ላይ ከተደረሰ አቅም ያለው በውሳኔው መሰረት የካሳ ክፍያውን ወዲያውኑ አንድ በአንድ ቆጥሮ ማስረከብ አለበት። በአንዴ አጠናቆ መክፈል ካልቻለ ደግሞ የጊዜ ገደብ ይሰጠዋል። የጊዜ ገደቡን ጠብቆ መክፈል ግን ግዴታ ነው። ይህ ካልሆነ ሌላ ግጭት ሊያስነሳ ይችላል።



ILS LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY



በአገር ሽማግሌዎች ፊት የካሳ ክፍያ ሲፈጸም

እንደ ወንጀሉ የአፈጻጸም ሁኔታ (ታስቦበትና ሳይታሰብ የተፈጸመ ግድያ ሊሆን ይችላል) ክፍና ዝቅ ቢልም ሟች ወንድ ከሆን እስከ 12 የሚደርሱ ከብቶች፣ ፍየል አርቢ በሆኑ አካባቢዎች ደግሞ ፍየሎች፣ ጦር፥ ጋር (በጭፈራ ጊዜ እግር ላይ የሚታሰሩ ቃጭሎች)፣ አሉደ (ከቀጭኔ ጭራ የሚሰራ በጭፈራ ጊዜ በክንድ ላይ የሚታሰር)፣ ሟች አዳኝ ከሆን ደግሞ የነብር ቆዳ ካሳ ይከፈላል። ሟች ሴት ከሆነች ግን የካሳ ክፍያው ለወንድ ከሚከፈለው ዝቅ ያለ ነው። በአሁኑ ጊዜ ራቅ ካሉ የገጠር አካባቢዎች በስተቀር የካሳ ክፍያው በገንዘብ እየተቀየረ በመሄድ ላይ እንደሚገኝ አቶ ኡጉታ አዲው ነግረውኛል። በገንዘብ የሚከፈል የካሳ ክፍያ እስከ 15,000 ብር ይደርሳል። በአኝዋዎች የካሳ አከፋፈል ደንብ መሰረት የተወሰነበትን ካሳ መክፈል ያልቻለ (ሟች ወንድ ከሆን) ሴት ልጁን፣ ሴት ልጅ ከሌለው ወንድ ልጁን፣ ልጅ ከሌለው ደግሞ እራሱን አሳልፎ ለሟች ወገን መስጠት አለበት። እራሱንና ወንድ ልጁን በካሳ መልክ አሳልፎ የሰጠ ለሟች ወገን በሎሌነት ያገለግላል። ሴት ልጅ ከሆነች ደግሞ ለሟች ወንድም ወይም ዘመድ ትዳራለች። ሟችና ገዳይ ዝምድና ካላቸውና ጋብቻ

መፈጸም ካልቻሉ ልጆቱ ለሌላ ተድሬ በሚገኝ ጥሉሽ የሟች ወንድም ወይም ዘመድ ይዳቡባቸዋል ይሁን እንጂ እንዲህ ያለ ሁኔታ የሚፈጠርበት አጋጣሚ አልፎ አልፎ እንደሆነ አቶ ኡጉታ አክለው ነግረውኛል። ምክንያቱም የአኝዋ ኑሮ በጋራ መተሳሰብ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ካሳ መክፈል ሳያቅተው ዘመዶቹና ቅርርብ ያላቸው የአካባቢው ነዋሪዎች አዋጥተው የመክፈል ማህበራዊ ግዴታ ስላለባቸው ነው። ከግድያ ወንጀል ጋር በተያያዘ ፓሞሊና ሸንተዋ በሚባሉ ሁለት የገጠር ቀበሌዎች በ1993 እና 1995 እ.ኢ.አ ስለተከሰቱ የግድያ ወንጀሎችና ስለተከናወኑ ሽምግልናዎች የሸንተዋ ቀበሌ ሊቀመንበር የነገሩን ነው በማለት አቶ ኡጉታ አዲው እንደሚከተለው አጫውተውኛል።

አቶ ኡመድ የተባሉ ከዘመዳቸው ጋር በመሆን ከብቶች ለመሸጥ ከኢታንግ አካባቢ ተነስተው ወደ ጋምቤላ ከተማ ሲመጡ ስለመሸባቸው ፓሞሊ የምትባል የገጠር ቀበሌ አንታቸው ዘንድ ለአዳር አረፉ። ማምሻውን በመጠጥ ሲዝናኑ አብሮአቸው የነበረ ሌላ ሰው እነ ኡመድ በነጋታው ወደ ጋምቤላ ከተማ ለመሄድ ጉዞ ላይ ሳሉ ከመንገድ አድፍጦ ለመዝረፍ አቶ ኡመድን ተኩሶ ገደላቸው። ከአቶ ኡመድ ጋር የነበረው ሰው ግን ሸሽቶ አመለጠ። ሸሽቶ የመለሰው የአቶ ኡመድ ዘመድ የአካባቢውን ሰው ጠርቶ ያስይዘኛል በሚል ፍራቻ ገዳይ እንዳሰበው ከብቶቹን ሳይዘርፍ ከአካባቢው ሸሽቶ አመለጠ። ፓሞሊ የሚኖሩ የኡመድ ዘመዶችም ስለግድያው ሁኔታ ለፖሊስ ሪፖርት አድርገው ገዳይ በሁለተኛው ቀን ተያዘ። ወንጀሉ በፍርድ ቤት ተጣርቶ ብይን እስኪሰጥም ገዳይ በእስር ቤት እንዲቆይ ተደርጎ ነበር። የሟች ወገን ግን በፍርድ ቤት መዳኘት አንፈልግም በማለት 10,000 ብር የደም ካሳ እንዲከፈላቸው የገዳይ ዘመዶች ለሚኖሩበት ቀበሌ ሊቀመንበር አመለከቱ። ሊቀመንበሩም የሟች ዘመዶች ከሚኖሩበት የፓሞሊ ቀበሌ ሊቀመንበር ጋር ከተወያዩ በኋላ ጉዳዩ በአገር ሽማግሌዎች እንዲታይ ተደረገ። የአገር ሽማግሌዎችም በደንቡ መሰረት ጉዳዩን ካጣሩ በኋላ 11 ከብቶች የገዳይ ወገን ካሳ እንዲከፍል ተደርጎ የእርቅ ስነስርዓት ሊካሄድ ችሉአል። እርቁ ሲከናወን አንድ በሬ ታርዶ የጉርቶንግ (ስለ ጉርቶንግ ከገጽ 64-65 ይመልከቱ) ስነስርዓት ተካሂዶአል (ታህሳስ 20፣1999)።

በባርሱኬ ደንብ መሰረት ሟች ወንድ ከሆነ የዕርቅ ስነስርዓቱ የሚጠናቀቀው ጉርቶንግ በማካሄድ ነው። ጉርቶንግ ካልተከናወነ ዕርቁ የጸና አይሆንም የሚል አመለካከት በአኙዋዎች ዘንድ አለ።ድርጊቱ የተፈጸመው ሸንተዋ በሚባል ቀበሌ ነው ብለው የገለጹን ሌላ ምሳሌ ደግሞ እንደሚከተለው ቀርቦአል::

አቶ ኡኩኝ አበላ ሁለት ሚስቶች ነበሩት:: አንደኛዋ መካን ስትሆን መካን ባልሆነችው ሁለተኛ ሚስት ትቀና ነበር። ይህች መካን ሴት አንድ ቀን በስካር መንፈስ ተነሳስታ ነፍሰ ጡር የነበረችውን ሁለተኛ ሚስት ገድላ ዘመዶቿ ወደ አሉበት ሸንተዋ ቀበሌ ሸሽታ በመሄድ እዚያ ሳለው የቀበሌ ሊቀመንበር እጇን ሰጠች። የሟች ቤተሰቦችም ለሸንተዋ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ሊቀመንበር የደም ካሳ እንዲከፍሏቸው አመለከቱ። በወቅቱ የደም ካሳው እንዴትና በማን ይከፈል የሚለው ውዝግብ አስነስቶ ነበር። በመጨረሻም የሸንተዋ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ሊቀመንበር ስለጉዳዩ ከአገር ሽማግሌዎች ጋር በመሆን ከተወያዩ በኋላ የገዳይ ወንድሞች ተይዘው እንዲከፍሉ ታዘዙ። የገዳይ ወንድሞች ግን አቅም ስላልነበራቸው ዘመዶቻቸው ቢጋራ አዋጥተው 15 ከብቶች ካሳ ተከፈለ። እርቅ ሲደረግም አንድ በሬ ታርዶ ጉርቶንግ ተካሂዶ ነበር (ታህሳስ 20፤1999)::

በባልና ሚስት መካከል በተፈጠረ ግጭት ሚስት ባሏን ከገደለች በደንቡ መሰረት ለሟች የሚከፈለው የካሳ ክፍያ ተከፍሎ ጉርቶንግ ይካሄዳል። ሟች ሚስት ከሆነች ግን የሚከፈለው ካሳ ባል ሲያገባት የከፈለውን ጥሎሽ እጥፍና ቲንጃት የሚባል በአንገት የሚጠለቅ ጨሌ፤ ከዝሆን ጥርስ የተሰራ አምባርና እነዚህን የመሳሰሉ የባህል ጌጣጌጦችን ነው። እነዚህ ጌጣጌጦች በብሔረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጣቸው ናቸው። ጉርቶንግ ግን አይካሄድም።

## 5.2.1.2 የጉርቶንግ ስነስርዓትና ክንዋኔዎች

እንዋዎች በመካከላቸውም ሆነ ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር በሚከሰቱ ግጭቶች የሰው ሕይወት ከጠፋ በባርሱኬ ደንብና ስርዓት መሰረት ለሟች ወገን ካሳ ይከፈላል። ሟች ወንድ ከሆነ ደግሞ "ጉርቶንግ" በተጨማሪ መካሄድ አለበት። ጉርቶንግ የሁለት

ቀላት ጥምር ሲሆን "ጉር" ማደልደም "ቶንግ" ደግሞ ጦር ማለት ነው። ጉርቶንግ ማለት ደግሞ የገዳይና የሟች ወገኖች ጦር አደልዱመውና የበሬ እናት በጦር ወግተው ዳግም ለበቀላ እንደማይፈላለጉ ቃል ኪዳን የሚገቡበት የካርሉክ ስነስርዓት ክንዋኔ አካል ነው። ቀደም ሲል እንደተገለጸው የሽምግልና ስራው ሲጀመር ሟች የተገደለበት ጦር ወይም አምሳያው፣ የበቆሎ ወይም የማሽላ ዱቂትና አንድ ድንጋይ ከጆድንጎዎች ፊት ለፊት የሚቀመጡበት ምክንያት ለጉርቶንግ ስነስርዓት ማከናወኛ ነው። የጉርቶንግ ስነስርዓት የሚጀመረው ጦር በማደልደም ሲሆን በመጀመሪያ የሟች ቀጥሎ የገዳይ ወገን ተወካዮች በስብሳቢው ዳኛ መሪነት በየተራ ለማደልደሚያ የተዘጋጀውን ድንጋይ በዱቂት እያበሱ የጦሩን ግራና ቀኝ ያደለዱማሉ። የጦሩን መደልደም ሰብሳቢው ዳኛ ካረጋገጠ በኋላ የሁለቱም ወገን ተወካዮች የጦሩን እጀታ በጋራ ይዘው ጫፉ እስኪታጠፍ ወይም እስኪደሉዱም እንደገና በድንጋይ ላይ ይቀጠቅጡታል። በዚህ ጊዜ የስነስርዓቱ ታዳሚዎች ተነስተው ደስታቸውን በጭብጨባና በማውካካት ይገልጻሉ። የደለደመውና ጫፉ የታጠፈው ጦር በጆድንጎው አማካኝነት ለሟች ወገን ይሰጣል። ጦሩ የደለደመበት ድንጋ ደግሞ ከካርሉክ ዛፍ ስር ይቀበራል። የደለደመው ጦር ትዕምርት የሰው ደም የፈሰሰበት ጦር ከአገልግሎት ውጪ መሆኑንና ዳግም ለግድያ እንደማይፈላለጉ የገቡትን ቃል ኪዳን መግለጫ ትዕምርት ነው። ጦሩ የደለደመበት ድንጋይ የሚቀበረው ምንም አይነት ግጭት በመካከላቸው ዳግም ላይከሰት መወገዱን ለማረጋገጥ ነው። ዱቂቱ ደግሞ የሰላም ትዕምርት ነው በማለት አቶ ዶል አኳይ የሚከተለውን ነግረውኛል።

> ጦር የሚደለዱመው ከእንግዲህ ብቀላ እንደማይፈጸምና እርቅ መደረጉን ለመግለጽ ነው። ጦሩ የደለደመበት ድንጋይ የሚቀበረው ለግጭት የሚዳርጋቸው ነገር ዳግም ላይከሰት መወገዱን ለማሳየት ነው። ሰላም ከሌለ ለዱቂት የሚሆን እህል ዘርቶ ማምረት አይቻልም። ስለዚህ ዱቂቱም እንደ የሰላም ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል። የበሬ እናት በጦር የሚወጋበት ምክንያት ደግሞ የገባውን ቃል ጥሶ የሰው ደም ያፈሰሰ ደሙ እንደዚህ በሬ ደም ይፍሰስ ብሉ ለመርገም ነው (ታህሳስ 24፣1999)።



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY



*በእርቅ ሥነሥርአት ላይ ጦር የማደልደም ስነስርአት ሲከናወን*

ከጦር ማደልደም በኋላ መሃላና የበሬ አናት በጦር የመውጋት ስነስርዓት ይከናወናል (በሬውን የሚያቀርበው የገዳይ ወገን ነው)። የበሬው አናት በጦር ከመወጋቱ በፊት ግን የገዳይና የሟች ወገን ተወካዮች በየተራ እየተነሱ ለጉርቶንግ የቀረበውን በሬ ጀርባ በዱቄት እያበሱ ከእንግዲህ በጠላትነት ላለመተያየት ቃል መግባታቸውን በተመለከተ ንግግር ያደርጉና የገቡትንም ቃል እንደማይጥሱ በመሀላ ያረጋግጣሉ። የቃለ መሀላ ስነስርዓት ከተከናወነ በኋላ ለጉርቶንግ የቀረበው በሬ ከጆደንጎዎቹ በአንዱ መሀልአናቱን ይወጋና ይታረዳል። ስጋውም ለሟችና ለገዳይ ወገኖች እኩል ይከፋፈላል። በክፍፍሉ አድሉ ካለ እርቁ ከልብ አልተደረገም ስለሚባል ዳግም ግጭት ሊከሰት ይችላል የሚል እምነት አለ። ስለዚህ እያንዳንዱ የበሬው ብልት ያለ አንዳች አድሎ ለሁለቱም ወገን እኩል እንዲከፋፈል ጆደንጎዎች ልዩ ጥንቃቄ ያደርጋሉ። የገዳይና የሟች ወገኖች ድርሻ ድርሻቸውን ከወሰዱ በኋላ ለጆደንጎዎች፣ ለዘመዶቻቸውና ለስነስርዓቱ ታዳሚዎች መልሰው ያከፋፍላሉ። እኘዋዎች ያገኙትን ተካፍለው በጋራ የመኖር ባህል ስላላቸው ለጉርቶንግ የቀረበውንም በሬ ሥጋ ሲጋራ ይከፋፈላሉ። ይህን በተመለከተ አቶ ሀኪም ኡፓራ እንዳሉት "በክላ የተገኘ ከብትም ሆነ ሌላ ነገር ለጋራ ጥቅም ይውላል እንጂ ግለሰቡ ብቻውን አይጠቀምበትም። የተገኘውን ተካፍሉ መብላት ለእኛ እኘዋዎች አይነተኛ መገለጫ ባህላችን ነው" (ታህሳስ 24፣1999)።



ከኡር'ዎ ወጊዳ የተጎዳዉ መሸርት ለካርቶንግ የቀረበውን በሬ በዱቄቱ ደርባውን እያሳሉ ዳግም ወደ ግጭት እንደማይመለሱ በመግለጽ የቃለ መሀላ ስነስርዓት ሲካሄድ

## 5.2.2 እቻንግ ዶዎቶ

በሁለት የአኝዋ ቀበሌዎች ወይም አጎራባች ብሔረሰቦች መካከል ግጭት ሲፈጠር የሚፈታው "እቻንግ ዶዎቶ" በሚባል የውይይትና ዕርቅ ስነስርዓት ነው። በአቶ ኡጉታ አዲው አገላለጽ "እቻንግ ዶዎቶ እንደ የጋራ ትብብር፣ ህዝባዊ ውይይትና የጋራ ስምምነት ላይ የሚደረስበት ጉባኤ (Conference) ተደርጎ ሊታይ ይችላል" (ታህሳስ 10፣1999)። ግጭቱ የተከሰተው በአኝዋ ቀበሌዎች መካከል ከሆነ ከሁለቱም ቀበሌዎች ተወክለው በሽምግልና የሚሳተፉት ካርዋንግ (የአስተዳደሩ ተወካይና የጆዶንጎው ሰብሳቢ) ኛቱዌል (መረጃ ሰብሳቢ)፣ ኝቡርና ኝኬና የሚባሉ የአስተዳደሩ ባለስልጣናትና ከህዝቡ የተወከሉ የአገር ሽማግሌዎች ናቸው።

በእቻንግ ዶዎቶ መፈታት ያለበት ግጭት በአኝዋ ቀበሌዎች መካከል ከተከሰተ በመጀመሪያ የሁለቱም ቀበሌ ኳሮዎች ችግሩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

በተወካዮቻቸው በኩል መልዕክት በመላላክ በጉዳዩ ዙሪያ ሀሳብ ይለዋወጣሉ። በሀሳብ ከተግባቡ በኋላ ከሁለቱም ቀበሌዎች የተውጣጡ የአገር ሽማግሌዎች በጋራ ሆነው አቻንግ ዶምቶ የሚካሄድበትን ቅድመ ሁኔታ ያመቻቻሉ። ቅድመ ሁኔታዎቹም የሁለቱም ወገን የአገር ሽማግሌዎች በግጭቱ የተሳተፉ የየቀበሌዎቻቸውን ነዋሪዎች በማሰባሰብ እርቅ እንዲደረግ ማወያየት፣ ጥፋተኛም ካለ ይህንኑ አምኖ እንዲቀበልና በአቻንግ ዶምቶ ላይ ይቅርታ እንዲጠይቅ ማድረግ ነው። ሌላው ተግባራቸው የጠፋ የሰው ሕይወትና የወደመ ንብረት ካለ አጣርቶ ጥፋተኛ ማን እንደሆነ መለየትና ካሳ የሚከፈል ከሆነም ይህንኑ ማመቻቸት ነው። በመጨረሻም በጋራ ተገናኝተው አቻንግ ዶምቶ የሚካሄድበትን ቀን ወስነው ለሁለቱም ቀበሌ አማካኝ የሆነ ቦታ መርጠው ህዝቡ በስነስርዓቱ ላይ እንዲገኝ ያደርጋሉ።

ለግጭቱ መቀስቀስና ለደረሰው ጥፋት ተጠያቂ የሚሆነው ወገን የሚታወቅ ከሆነ ግን እርቅ መፈለጉን ቀድሞ ማሳወቅ ይጠበቅበታል። ግጭቱ የተከሰተው በአኝዋና ኑዌር መካከል ከሆነና ጥፋተኛነቱን ያመነው የኑዌር ቀበሌ ከሆነ የይቅርታና ዕርቅ ጥያቄውን በአገር ሽማግሌዎች በኩል የሚያቀርበው ለአኝዋ ቀበሌ ኚያ ወይም ኳሮ ነው። የአኝዋ ቀበሌ ከሆነ ደግሞ ኚያው ወይም ኳሮው ኛቱዌል በሚባለው መልዕክተኛ በኩል ለኑዌር ቀበሌ የጎሳ መሪ ወይም ታዋቂ የአገር ሽማግሌዎች መልዕክት ይልካል። የይቅርታና ዕርቅ ጥያቄ የቀረበለት ቀበሌ መሪና የአገር ሽማግሌዎች ተሰብስበው በጉዳዩ ላይ ይመክሩና ምላሻቸውን በመልዕክተኛ በኩል ያሳውቃሉ። የከፋ አለመግባባትና የከረረ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር እርቅ የጠየቀን ወገን እንቢኝ አይባልም። አለመግባባትና የከረረ ሁኔታ ከተፈጠረ ደግሞ በሶስተኛ ወገን (በመንግስት ወይም በአጎራባች ቀበሌ የአገር ሽማግሌዎች) አነሳሽነት ረዘም ላለ ጊዜ ውይይትና ድርድር ተካሂዶ የእርቅ ሂደቱ ይጀመራል። ከስምምነት ላይ ከተደረሰ በሁለቱም ቀበሌዎች አማካኝ የሆነ ስፍራ ላይ ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው በአገር ሽማግሌዎች ሰብሳቢነት አቻንግ ዶምቶ ተዘጋጅቶ ህዝባዊ ውይይት ይካሄዳል።

በውይይቱ የሁለቱም ቀበሌ ነዋሪዎች፣ የጎሳ መሪዎቹና እንደ አስፈላጊነቱም የአጎራባች ቀበሌ መሪዎችና የአገር ሽማግሌዎች እንዲሁም የመንግስት ተወካዮች ተሳታፊ ይሆናሉ። ውይይቱ የሚጀመረው ቀደም ሲል ስለሁኔታው ማጣራት ያደረጉ የአገር ሽማግሌዎች በየተራ እየተነሱ በተፈጠረው ግጭትና በደረሰው ጉዳት

ማዘናቸውን በመግለጽ ስለግጭቱ አነሳስ፣ ስለወደመ ንብረትና የጠፋ የሰው ህይወት በዝርዝር ከገለጹ በኋላ ነው። በመቀጠልም የአቻንግ ዶዎቶ ተሳታፊዎች አስተያየታቸውንና የምስክርነት ቃላቸውን በመስጠት ውይይት ይካሄዳል። ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ካሰም ካሳ እንዲከፈል ይደረጋል። የተዘረፉ ከብቶችና እህል ደግሞ ለባለቤቶቹ ይመለሳል። ምርኮኛ ካለም ይለቀቃል።

ግጭቱን የቀሰቀሱ ሰዎች ተለይተው ከታወቁ ደግሞ በአገር ሽማግሌዎች ተወቅሰው ዳግም ተመሳሳይ ድርጊት እንዳይፈጽሙ ምክርና ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸዋል። የሽማግሌዎችን ቃልና በአቻንግ ዶዎቶ የተደረሰበትን ስምምነት ጥሶ ወደ ግጭት የሚያመራ ድርጊት የሚፈጽም ፕራሱ ጦር መልሶ ይወጋው፣ የሰው ደም ካፈሰሰ የራሱና የዘመዶቹ ደም ይፍሰስ" ተብሉ ይረገማል። አቻንግ ዶዎቶ የሚጠናቀቀው ጉርቶንግ በማካሄድ ሲሆን ለጉርቶንግ የሚውሰውን በሬ የሚያቀርበው ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ወገን ነው። ተጠያቂ የሚሆን ወገን ከሌለ ሁለቱም ወገኖች በየበኩላቸው አንድ በሬና አንድ ጦር ያቀርቡና ቀደም ሲል በተገለጸው መሰረት የጉርቶንግ ስነስርዓት ይከናወናል። በጉርቶንግ ያደለደሙትን ጦር በየተወካዮቻቸው አማካኝነት ተለዋውጠው በቀበሌው ወይም ጎሳ መሪዎች የቤት ጣሪያ ስር ለዘላለም እንዲኖር ይደረጋል። የደለደመው ጦር ከእንግዲህ አብሮ በሰላም ለመኖር ቃል ኪዳን የማሰሪያ ትዕምርት ተደርጎ ይታያል። ቃል ኪዳናቸውን ላለማፍረስም መሀላ ይፈጽማሉ። የአቻንግ ዶዎቶ ዋና አላማም ግጭቶችን በውይይት በመፍታት አብሮ በሰላም የመኖር ባህልን ማጠናከር ነው። ይሁን እንጂ አንዳንዴ በተለይ በአኝዋና ኑዌር መካከል የሚደረገው ዕርቅ በአኝዋ ቀበሌዎች መካከል እንደሚደረገው የጸና ሆኖ አይስተዋልም። ይህንን የሚያጠናክር አቶ አዱኣ ኡመድ እንዲህ ሲሉ ነግረውኛል።

ሊጋምቤላ ክልል ሰላምና ጸጥታ መደፍረስ አንዱ ምክንያት በአኝዋዎችና ኑዌሮች መካከል የሚከሰቱ ተደጋጋሚ ግጭቶች ናቸው። በሁለቱ ቤተሰቦች መካከል የሚደረግ ዕርቅም በአኝዋ ቀበሌዎች መካከል እንደ ሚደረገው የጸና አይደለም። ለዚህ አንዱ ምክንያት አርብቶ አደር የሆኑት ኑዌሮች ለከብቶቻቸው ግጦሽና ለእርሻ የሚሆን መሬት ፍለጋ አኝዋዎች ወደ ሚኖሩበት አካባቢ ዘልቀው መግባታቸው ስለማይቀር ነው። በዚህ



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ምክንያት ዛሬን ድረስ አልፎ አልፎ ግጭቶች ሲከሰቱ ይስተዋላል (ታህሳስ 10፣1999)።

የክልሉ መንግስት በአሁኑ ጊዜ ሀገረሰባዊ ዘዴዎችን በመጠቀም ግጭቶችን ለመፍታት እንዲቻለው የጆዶንጎ (አገር ሽማግሌዎች) አማካሪ ምክር ቤት አቋቁሞ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል። ጆዶንጎዎቹ ከየብሔረሰቡ የተውጣጡ ሲሆኑ ተግባራቸውም በተደጋጋሚ እየተከሰተ ያለውን የጸጥታ ችግርና የብሔረሰቦች ግጭት በአገሬው ባህል መሰረት ለመፍታትና ህብረተሰቡን ስለሰላም በማስተማር ለክልሉ ሰላም ግንባታ አገዛ ማድረግ ነው። በፖለቲካዊ አመለካከት ልዩነት፣ በስልጣንና የወረዳዎች በጀት ክፍፍል ባስከተለው ውዝግብና መንስኤያቸው በውል ተለይተው በማይታወቁ ምክንያቶች በርካታ ግጭቶች ከ1983 እ.ኢ.አ ወዲህ በክልሉ ተከስተው እንደነበር አቶ ጶምስ ዶንግ የክልሉ ጸጥታ፣ፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች ቢሮ ሀላፊ ነግረውኛል (ታህሳስ 13፣ 1999)። በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ግጭቶችን በሀገረሰባዊ ዘዴዎች ለመፍታት ጥረቶች እየተደረጉ መሆናቸውን በመግለጽ የክልሉ አማካሪ የአገር ሽማግሌዎች ምክር ቤት አባል የሆኑት አቶ ሀኪም አጋሬ በ1990 ዓ.ም ኢታንግ ወረዳ ላይ በአኙዋዎችና ኑዌሮች መካከል ተፈጥሮ የነበረው ግጭት በአቻንግ ዶዎቶ መፈታቱን እንደሚከተለው ነግረውኛል።

> በ1990 እ.ኢ.አ ኢታንግ ወረዳ ላይ በአኙዋዎችና ኑዌሮች መካከል ከፍተኛ የሚባል ግጭት ተከስቶ ነበር። በግጭቱ ንጹሀን ዜጎችም ሞተዋል። ቤቶች ተቃጥለዋል፣ የንብረት ዘረፋም ተካሂዷል። ሁኔታው እየተባባሰ በመሄዱ የክልሉ መንግስት ከአገር ሽማግሌዎች ጋር በመሆን ችግሩ በውይይትና በሽምግልና እንዲፈታ አቻንግ ዶዎቶ በተለያዩ ቀበሌዎች ተደርጓል። አቻንግ ዶዎቶ ላይ በተደረገ ውይይት ጥፋተኞችን ለይቶ በማውጣት መንግስት እርምጃ እንዲወስድባቸውም ተደርጓል። በመጨረሻም ከየቀበሌዎች የተውጣጡ ተወካዮችና የአገር ሽማግሌዎች በተገኙበት ጉርቶንግና የእርቅ ስነስርዓት ጋምቤላ ከተማ ላይ ተካሂዷል። በስነስርዓቱ ላይ ሁለቱም ወገኖች ያመጡትን ጦር በማዶልዶም በተወካዮቻቸው አማካኝነት ተለዋውጠው ዳግም ላለመጋጨት ቃለ መሀላ ፈጽመዋል። በአካባቢዉ እስካሁን ድረስ የከፋ ግጭት ሲከሰት አይስተዋልም (ታህሳስ 18፣1999)።

አቶ ሀኪም አከለው እንደገለጹልኝ እስካሁን ድረስ የጆድንን አማካሪ ምክር ቤት እያደረገ ባለው እንቅስቃሴ ህብረተሰቡ ድጋፍ እያደረገላቸው ይገኛል፡፡ አቶ ኡጉታ እንደነገሩኝ ደግሞ ዛሬም ቢሆን በፍርድ ቤት ቅጣት ተበይኖበት የእስር ዘመኑን የጨረሰ እንኳ ወደ ህብረተሰቡ ተቀላቅሎ በሰላም ለመኖር በእኝዋ ባህል መሰረት ካሳ ከፍሎ እርቅ መደረግ አለበት፡፡ የክልሉ ፍትህ ቢሮም ከወንጀለኛ ህጉ ጋር የማይጻረሩ ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን እንደሚያበረታታ የጋምቤላ ከተማና ዙሪያ ወረዳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቃቤ ህግ ባሙያ የሆኑት አቶ ኡማን ኡጁሉ ነግረውኛል፡፡

## 5.2.3 ካርጎእል ሉፐ

በሰፈር ውስጥ የሚከሰቱ መለስተኛና አነስተኛ ግጭቶችን እንዲመለከት ኃላፊነት የተሰጠው የካርሉክ ተቋም "ካርጎእል ሉፐ" ይባላል:: ካርጎእል ሉፐ እንደመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚታይ ሲሆን ሰብሳቢ ዳኛው "ኳይ አቴ"፣ ጉዳዩ ኳይ አቴት ከሚሰበስበው ጆዶንን አቅም በላይ ከሆነ ደግሞ ከአስተዳደሩ ከፍተኛ ባለስልጣናት አንዱና የሰፈር ሹም የሆነው ኘቡር ይባላል፡፡ የካርጎእል ሉፐ ጆዶንን ሰብሳቢ ኘቡር በሚሆንበት ጊዜ ኳይ አቴት እንደ ምክትል ሰብሳቢና ቀደም ሲል በእሱ ሰብሳቢነት የተከናወኑ ተግባራት ካሉ ሪፖርት አቅራቢ በመሆን ይሰራል፡፡ ኳይ አቴት በሚመራው ካርጎእል ሉፐና ጆው ዊማች (የቤተዘመድ ሽምግልና) ሊፈቱ ያልቻሉ ጉዳዮች በቀጥታ ሪፖርት የሚደረጉት ለኘቡር ነው፡፡ የዳኞች ቁጥርም ሰባሳቢውን ጨምሮ ከ3-5 ይደርሳሉ፡፡

አነስተኛም ሆነ መለስተኛ የሰፈር ውስጥ ግጭት ሲከሰት ጥፋቱን አምኖ እርቅ እንዲደረግ የፈለገ ወገን በመጀመሪያ ለኳይ አቴት ያስታውቃል፡፡ ኳይ አቴትም ስለጉዳዩ ከጆዶንንዎች ጋር ይወያይና ጥፋተኛውን ጠርቶ ያነጋግራል፡፡ በዚህ ሁኔታ ስምምነት ላይ ከተደረሰ እርቁን ለማካሄድ ቀን ቀጠሮ ይያዛል፡፡ በእኝዋዎች ዘንድ ጥፋተኛ መሆኑን ያመነ ሳይጠፋው ጥፋት አስቀድሞ ይቅርታ ለመጠየቅ ዝግጁ መሆኑን ካላሳወቀ ተበዳዩን ከማስቀየሙም በላይ ተጨማሪ በደል እንዳደረሰ ተደርጎ ይታያል፡፡ አቶ አቡላ ኡመድ እንዳሉት "ጥፋትን አምኖ ይቅርታ መጠየቅ ሁኔታዎችን ለማረጋጋትና የዕርቅ ሂደቱን ለማፋጠን እገዛ ያደርጋል" (ቃለሳስ 7፣1999)፡፡ ጥፋተኛ ጥፋቱን አምኖ ይቅርታ ለመጠየቅ ዝግጁ ካልሆነና ያጠፋው ጥፋት ካሳ የሚያስከፍል ከሆነ በደል የደረሰበት

ሰው ካሳ እንዲከፍለው ለካይ አቱት ያመለክታል። ሁለቱም ወገኖች ጉዳያቸውን ለካይ አቱት ካላቀረቡና ወደ ባሰ ግጭት ሊያመራ የሚችል አዝማሚያ ከተፈጠረ ጆዶንጎው ጣልቃ ገብቶ ድርድርና እርቅ የሚደረግበትን ሁኔታ ያመቻቻል። ችግሩ ከፍተኛ ወይም ካይ አቱት ከሚመራው ካርጎአል ሉፕ አቅም በላይ ከሆነ ደግሞ ስለጉዳዩ ለኝቡር ሪፖርት ይደረጋል። እዚህ ደረጃ ከደረሰ ለችግሩ የመጨረሻ እልባት ይሰጣል። የተጋጩ ወገኖችም ኝቡር ከሚመራው የካርጎአል ሉፕ ውሳኔ ውጭ መሆን ባህሉ አይፈቅድላቸውም። በውሳኔው መሰረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደ ጣፋቱ መጠን ለተበዳይ ካሳ ይከፍላል። ዳግም በጠላትነት ላለመተያየትም ቃለ መሃላ ይፈጽማሉ። ጆዶንጎዎችም ዳግም ተመሳሳይ ድርጊት እንዳይፈጸም ምክርና ማስጠንቀቂያ ይሰጣሉ።

አንዳንድ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ተፈጥረው ነገሩን ለማለዘብና ድርድር ለማካሄድ ሲባል የእርቅ ሂደቱ ለተወሰነ ጊዜ ሊራዘም ቢችልም በካርሉክ ደንብ መሰረት ግጭቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ መፍትሄ ማግኘት አለባቸው። በካርጎአል ሉፕና ጆው ዊማች የሚታዩ ጉዳዮች ውስብስብነት ስለሌላቸው መፍትሄ የሚያገኙት በአጭር ጊዜ ውስጥ ነው። "ባልተገባ ሁኔታ ግጭቶችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመፍታት መቻሉ ጉዳት የደረሰበት ወገን በስሜት ተነሳስቶ ብቀላ እንዳያካሂድ ወይም ነገሮች ተካረው ወደ ከፋ ደረጃ እንዳይሸጋገሩ ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር ያስችላል" በማለት አቶ ኡጉታ አዲው ገልጸውልኛል (ታህሳስ 9፣1999)።

በጭፈራና መሰል ቦታዎች በሚነሳ ግጭት ሴት ልጅ በወንድ ከተደበደበችና የአካል ጉዳት ከደረሰባት ነገሩ እየተባባሰ ሄዶ በቤተሰብ መካከል የቡድን ጠብ ሊነሳ ይችላል። ይህ እንዳይከሰት ካይ አቱት ወይም ኝቡር ጣልቃ ገብቶ ግጭቱ በካርጎአል ሉፕ እንዲፈታ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። እንዲህ ያለው ሁኔታ ሲፈጠር በመጀመሪያ ካይ አቱት ወይም ኝቡር ሁለቱንም ወገኖች በተናጥል አነጋግሮ መረጃዎችን ያሰባስብና ስለ ሁኔታው ከጆዶንጎዎች ጋር ይወያያል። በመቀጠልም ሁለቱም ወገኖች በካርጎአል ሉፕ ካርሉክ ላይ ተገኝተው ዕርቅ እንዲያደርጉ ቀጠሮ ይያያዛል። በቀጠሮው ቀን ሁለቱም ወገኖች ስለተፈጠረው ሁኔታ እንደገና ለጆዶንጎዎች ካስረዱ በኋላ እንደሁኔታው ምስክር ካስፈለገ የምስክሮች ቃል ይደመጣል። ውይይትና ክርክርም ይካሄዳል። አስተያየት መስጠት የሚፈልግ ታዳሚ ካለም መስጠት ይችላል።

ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ባደረሰው ጉዳት መጠን ካሳ እንዲከፍል ይወሰንበታል፡፡ በመጨረሻም ዳግም ተመሳሳይ ጠብ እንዳይከሰት በጀዶንጎዎች ማስጠንቀቂያና ምክር ተሰጥቶ ዕርቅ ይደረጋል፡፡ ጉዳት ያደረሰው ወገን ጥፋቱን በማመን አስቀድሞ ይቅርታ ከጠየቀ ደግሞ ላደረሰው ጉዳት ካሳ ከፍሎ እርቅ እንዲደረግ መጠየቅ አለበት፡፡

ግጭቱ የተከሰተው በመሬት ይገባኛልና በወሰን ከሆነ መፍትሄ የሚሰጠው ኘቡር በሚመራው ካርንአል ሉፐ ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ ግጭት ሲፈጠር ተበደልኩ ባይ በመጀመሪያ ጉዳዮን ለኘቡር ያሳውቃል፡፡ ኘቡርም ከጀዶንጎዎች ጋር ተነጋግሮ ሁለቱም ወገኖች በቀጠሮ ካርንአል ሉፐ ተገኝተው በጉዳዩ ላይ ውይይትና ክርክር ይደረጋል፡፡ ምስክሮች ካሉም ቃላቸውን ይሰጣሉ፡፡ ከታዳሚዎችም አስተያየት ይሰጥና ላሸነፈው ወገን ይወሰንለታል፡፡ ተቃራኒው ወገንም የችሎቱን ውሳኔ የማክበር ግዴታ አለበት፡፡ ስለተፈጠረው ሁኔታ ሁለቱም ወገኖች ለኘቡር ሳያመለክቱ ቀርተው ነገሩ እየተባባሰ መሄዱን ኘቡር ካወቀ ከጀዶንጎዎች ጋር ተነጋግሮ በጉዳዩ ጣልቃበመግባት ቀደም ሲል እንደተገለጸው ችግሩ በካርንአል ሉፐ እንዲፈታ ያደርጋል፡፡ ከእርቅ በኋላ ሁሌም እንደሚደረገው ጀዶንጎዎች ባህላዊ መጠጥ ይጋበዛሉ፡፡ የግብዣው ወጪ የሚሸፈነው ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘው ወገን ወይም በሁለቱም ሊሆን ይችላል፡፡ ግብዣ የሚደረግበት ዋናው ምክንያት በጀዶንጎዎች ጥረት ግጭቱ በመፈታቱ የተሰማቸውን ደስታ ለመግለጽ ነው፡፡ ግብዣው ሌላም ፋይዳ እንዳለው አቶ ኡጉታ እንዲህ ሲሉ ነግረውኛል "ግብዣ ላይ ሁሉም የልቡን አውጥቶ ስለሚናገር ለግጭት በሚዳርጉ ጉዳዮችና ሰላማዊ ግንኙነቶች በሚጠናከሩበት ሁኔታ ላይ ለመነጋገር መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል" (ታሁሳስ 8፣1999)፡፡

የግሉ ስለመሆኑ የማይታወቅ ንብረት ይዞ የተገኘ (የሰረቀ) ወይም የዘረፈ (ለምሳሌ በሬ፣ ላም፣ ፍየል) በአካባቢው ነዋሪዎች ጥቆማ ኘኩጉ በሚባለው የአስተዳደሩ ባለስልጣን በኩል ጉዳዩ ተጣርቶ ለካርንአል ሉፐ ይቀርባል፡፡ ጥፋተኛ የተባለውም በቀጠሮ ካርንአል ሉፐ ላይ ተገኝቶ ስለሁኔታው እንዲያስረዳ በኘኩጉ ይታዘዛል፡፡ ካርንአን ሉፐ ላይ ተገኝቶ ንብረቱ የግሉ ስለመሆኑ በማስረጃ ማረጋገጥ ካልቻለ እንደ ሰረቀ ወይም እንደ ዘረፈ ተቆጥሮ ይነጠቅና ባለቤቶቹ ወደ አካባቢው ዘልቀው ግጭት እንዳይፈጥሩ ሲባል ከመሪዎች ዘንድ ወይም ከሌላ ሰው በአደራ ይቀመጣል፡፡ ባለቤቱ ሲታወቅም የተሰረቀበት ንብረቱ እንዲመለስለት ይደረጋል፡፡ ወንጀለኛውም ከተመሳሳይ

ድርጊት እንዲቆጠብ ምክርና ከባድ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል። ይህን በተመለከተ አቶ ታሉ አኢያ እንዳሉት ዝንቡሩ የእኛዋ ባህል ስርቆት እንደ ትልቅ ነውርና ወንጀል ይቆጠራል። ወድቆ የተገኘ ንብረት ቢሆንም እንኳ ባለቤቱ እስኪገኝ በአደራ ይቀመጣል እንጂ "ጎንፆ" በግል ሊጠቀምበት አይችልም። በአሁኑ ጊዜ ግን ይህ ባህል እየተሸረሸረ በመሄዱ በተለይ በከተሞች አካባቢ ስርቆትና ዝርፊያ ተበራክቶ ይስተዋላ" (ታህሳስ 17፣1999)።

የሰው ንብረት ተውሶ ወይም ተበድሮ የካደም ክስ የሚመሰረትበት በካርጎአል ሉፕ ላይ ነው። በቀጠሮ እለት ከሳሽና ተከሳሽ ከነምስክሮቻቸው በካርጎን ሉፕ ላይ ተገኝተው ክርክር ይደረጋል። የችሎቱ ታዳሚዎችም አስተያየት መስጠት ይችላሉ። ጉዳዩ ቀጠሮ የሚያስፈልገው ከሆነም በሌላ ቀጠሮ ክርክሩ ሊቀጥል ይችላል። በመጨረሻም የምስክሮች ቃልና የታዳሚዎች አስተያየት ተደምጦ ጆዶንጎዎች ግራ ቀኙን ካዳመጡ በኋላ ውሳኔ ይሰጣሉ። ተከሳሽ ጥፋተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ የተዋሰውን ወይም የተበደረውን ለባለቤቱ እንዲመልስ ቀጠሮ ይሰጠዋል። በተሰጠው ቀጠሮ ካልመለሰ በድጋሚ ካርጎአል ሉፕ ቀርቦ ማስጠንቀቂያ ይሰጠውና ዋስ ጠርቶ በቀጠሮ ይለቀቃል። ከዚህ በኋላ ተከሳሽ ውሳኔውን ካላከበረ ተጠያቂ ዋስ ነው።

የህብረተሰቡን ወግና ልማድ ጥሶ ነውር የሚባሉ ተግባራትን የፈጸመ፣ በስካር መንፈስ እየተንሳሳ ተደጋጋሚ ሁከት የሚፈጥር ወዘተ ሲገኝ በኝኩጉ በኩል ጉዳዩ ተጣርቶ ካርጎአል ሉፕ ይቀርባል። እንዲህ ያሉ ተግባራት የሚፈጽሙትን ተከታትሎ እንዲቀጡና ከጥፋታቸው እንዲታረሙ የማድረግ ኃላፊነት የተሰጠው ኝኩጉ ለሚባለው የአስተዳደሩ ባለስልጣን ነው። በኝኩጉ ክስ የተመሰረተበት በቀጠሮ ካርጎአል ሉፕ ተገኝቶ ስለፈጸመው ድርጊት ማብራሪያ እንዲሰጥ ይጠየቃል። ተከሳሽም ለተጠየቀው ማብራሪያ ከሰጠ በኋላ ድርጊቱን አምኖ ይቅርታ እንዲጠይቅ ይደረጋል። የካርጎአል ሉፕ ጆዶንጎዎችም ግለሰቡን በፈጸመው ድርጊት ኮንነው ዳግመኛ ተመሳሳይ ድርጊት እንዳይፈጽም ምክርና ማስጠንቀቂያ ይሰጡታል። በተከሳሽ ድርጊት ተበደልኩ የሚል ሰው ካለም ጉዳዩ ተጣርቶ ተበዳዩን ይቅርታ እንዲጠይቅና እስከ 50 ብር የሚደርስ ካሳ እንዲከፍል የሚደረግበት አግባብ አለ። በዚህ አይነቱ ጥፋት የተገኘን ካሳ ሁለቱም ወገኖች ከጆዶንጎዎች ጋር በመሆን ባህላዊ መጠጥ ይጋበዙበታል እንጂ ለግለሰቡ አይሰጥም። የጆዶንጎዎች ቃል ስለሚከበር እንዲህ ያለውን ጥፋት ፈጽሞ ወቀሳ



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

የደረሰበትና ምክር የተሰጠው ሰው ዳግመኛ ተመሳሳይ ድርጊት ከመፈጸም ይጠነቀቃል ሲሉ አቶ ኡጉታ ነግረውኛል (ቃህሳስ 17፣1999)።

## 5.2.4 ጆጨ ዊማች

"ጆው ዊማች" (የቤተዘመድ ሽምግልና) ከካርሱክ አይነቶች አንዱ ሲሆን በዚህ ተቋም የሚታዩ ጉዳዮች የቤተሰብ በተለይ ደግሞ የባልና የሚስት ግጭቶች ናቸው። የጆው ዊማች ሰብሳቢና አባላት የሚመረጡት ከቤተዘመድ አባላት መካከል ሲሆን ሽምግልናው የሚካሄደው "ዊማች" በሚባል በየሰፈሩ ለመሰብሰቢያና መመገቢያ ተብሎ በተዘጋጀ የሳር ዳስ ውስጥ ነው። በባልና ሚስት መካከል ግጭት ሲፈጠር ተበደልኩ ባይ ጉዳዩን በመጀመሪያ ለጆው ዊማች ሰብሳቢ ያሳውቃል። የጆው ዊማች ሰብሳቢም ጾደንጎምቹን ሰብስቦ በጉዳዩ ላይ ይመክራል። ባልና ሚስትንም በተናጥል እየጠራ ያነጋግራል። በመጨረሻም ባልና ሚስት በማገባር ተገናኝተው በደላቸውን ከጆዶንጎውፊት እንዲናገሩ ይደረጋል። በዚህ ሁኔታ ባልና ሚስት ከጆዶንጎው ጋር በመሆን ችግራቸውን በውይይት መፍታት ከቻሉ ያለአንዳች ውጣ ውረድ ተመክረውና ተወቅሰው ይታረቃሉ። ከእርቅ በኋላም ከጆዶንጎዎች ጋር በጋራ ሆነው ቦርዴ (ባህላዊ መጠጥ) ይጠጣሉ (ጋባዥ ባልና ሚስት ናቸው)።

ባልና ሚስት መካከል የተከሰተው ግጭት ከረር ያለ ከሆነና ጥፋተኛ ባል ሆኖ ከተገኘ በሚስቱ ላይ ላደረሰው በደል እንደ ሁኔታው አንድ ፍየል ወይም ከ50 ብር የማይበልጥ ካሳ ለሚስቱ እንዲከፍል ይደረግና ይታረቃሉ። ጥፋተኛ ሚስት ሆና ከተገኘች ግን ወደ ወላጆቿ ሄዳ ምክር ተቀብላ እንድትመለስ ይነገራታል። ወደ ወላጆቿ ከመሄዷ በፊት ወይም መሄዷን ተከትሎ ስለጉዳዩ ለአባቷ ወይም ለወንድሞቿ የሚያስረዳ መልዕክተኛ በጆው ዊማች ይላካል።

ተመክራ እንድትመለስ ወደ ወላጆቿ የተላከች ሚስት እስከምትጠየቅ ድረስ በጆው ዊማች የተነገራትን ለወላጆቿ አትናገርም። ውላ አድራ ግን በአባቷ ወይም ወንድሞቿ መጠየቋ አይቀርም። የመጣችበትን ምክንያት ተጠይቃ ከተናገረች በኋላ በቅርብ ያሉ ዘመዶችና ጎረቤቶች ዊማች ላይ ተሰብስበው ከጆው ዊማች የተላከው መልዕክት ይነገራቸዋል። ልጃቸውም ተጨማሪ ማብራሪያ እንድትሰጥ በድጋሚ

ትጠየቃለች። ዘመዶቿና ጎረቤቶች ተሰብስበው የሚወያዩት በደንቡ መሰረት ልጃቸውን መክረውና ካሳውን አሟልተው ወደ ባሏ የምትመለስበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እንጂ የጾው ቸግች ውሳኔን መሻር ወይም ይግባኝ መጠየቅ አይችሉም። ተመክራ የምትመለስ ሚስት ለባሏ ካሳ መክፈል አለባት። ቤተሰቦቿ ለካሳ የሚሆን ፍየል (ፍየል ከሌለ ተመጣጣኝ ገንዘብ ወይም ስጦታ) ቦርዶ ወይም አታርቡብ (ባህላዊ መጠጥ) አዘጋጅተውላት በባልንጀሮቿና እማወራዎች አጃቢነት ወደ ባሏ ይልኳታል። ተመክራና በጥፋቷ ተጸጽታ መመለሷን በቅርብ ወዳጆቹ አስጠይቶ ካላረጋገጠ ባል ሚስቱ እንደመጣች እጇን ዘርግቶ አይቀበላትም። ጥፋቷን አምና በምክር የተመለሰች ሚስት ይቅርታ መጠየቋን ለመግለጽ ለባሏ ያመጣችውን ካሳ ታስረክባለች። ከዚህ በኋላ እርቅ ተደረገ ማለት ነው። የጾው ቸግች ጆዶንጎዎችና አብረዋቸው ያሉ ሰዎችም ከቤተሰቦቿ የመጣችውን ባህላዊ መጠጥ ይጋበዛሉ።

በጾው ቸግች መፍትሄ ያላገኘ የባልና ሚስት ጉዳይ በኝቡር ሰብሳቢነት ለሚሰየመው ጆዶንጎ ይተላለፋል። እዚህ ደረጃ ከደረሰ በቀጥታ ፍቺ ይፈጸማል እንጂ ድርድርና ሽምግልና አይካሄድም። ፍቺ ሲካሄድ ጥፋተኛ ሚስት ሆና ከተገኘች ለጋብቻ የተከፈለውን ጥሎሽ ለባሏ የመመለስ ግዴታ አለባት። ጥፋተኛው ባል ከሆነና ልጆች ካሏቸው ለባልየው ጥሎሹ ሳይመለስለት ፍቺው ይፈጸማል። ልጆቹም ከሚስት ወላጆች ወይም ዘመዶች ዘንድ ተሰጥተው ያድጋሉ።

## 5.2.5 ግርፋትና እርግማን የሚያስከትሉ ድርጊቶች

ቀደም ሲል እንደገለጽኩት በአኝዋዎች ዘንድ በተደጋጋሚ ሲከሰቱ ከሚስተዋሉ ግጭቶች አንዱ ከጋብቻ ጥሎሽ ጋር የተያያዘ ነው። በአኝዋ የጋብቻ ባህል መሰረት አንዲት ወጣት ማርገዟ ከታወቀ ከማን እንዳረገዘች መጀመሪያ በወላጆቿ ትጠየቃለች። ከማን እንዳረገዘች ከታወቀ በኋላ ሰውየው ጥሎሽ እንዲከፍል ይጠየቃል። ጥያቄውን ተቀብሎ በተወሰኑ ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ በልጅቷ ቤተሰቦች ተይዞ ጀርባው እስኪላጥ ይገረፍና የጊዜ ገደብ ተሰጥቶት በድጋሚ ጥሎሹን እንዲከፍል ይነገረዋል። በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልከፈለ እንደገና ተይዞ ይገረፋል። የግርፊያ ቅጣቱን ተቀብሎ ጥሎሹን መክፈል የቻለ ከልጅቷ ጋር ጋብቻ የመፈጸም መብቱ የተጠበቀ ነው። ተገርፎም ቢሆን ጥሎሹን መክፈል ካልቻለ ግን ሁለተኛ ከልጅቷ ዘንድ እንዳይደርስ



ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

እንዲ ያሟልበታል። እንዲውን ጥሶ ከተገኘ እንደገና ተደቦ ይገረፋል። የጠለፋ ተግባር የፈጸመም በሴቷ ወገን የሚጠየቀው ጥሎሽ ብቻ ነው። ጥሎሽ ያልከፈለ ግን መገረፍ አይቀርለትም። ይህን በተመለከተ በ1992 እ.ኢ.አ በጋምቤላ ወረዳ ኡሚኒጋ ቀበሌ የምትኖር አሬያት የምትባል ወጣት ኡጁሉ ከሚባል ወጣት በማርገዟ የተከሰተውን ሁኔታ አቶ ኡፒቴ እንደሚከተለው ነግረውኛል።

> መሲባዊ ግንኙነት አድርገው አሬያት አረገዘች። በአረገዘች ስድስተኛው ወር ወጣት ኡጁሉ ኡመድና አሬያት ጊሎ በአንድ የጭፈራ ፕሮግራም ላይ ላይ ሆነ እየገፉ በመምጣቱ ወላጆቿ ከማን እንዳረገዘች ጠየቋት። አሪያትም ከኡጁሉ እንዳረገዘች ነገረቻቸው። የአሬያት ወላጆች በባህላቸው መሰረት ኡጁሉ ጥሎሽ እንዲከፍል በተደጋጋሚ ቢጠይቁትም ምላሽ ስላልሰጣቸው አንድ ቀን ጠዋት ላይ ይዘውት ወደ ሰፈራቸው በመውሰድ ጀርባው እስኪላጥ ከገረፉት በኋላ 2500 ብር ጥሎሽ እንዲከፍል በድጋሚ ጠየቁት። ኡጁሉም ጥሎሹን እንደሚከፍል ስለተስማማ የመክፈያ ጊዜ ገደብ ተሰጥቶት ተለቀቀ። ኡጁሉ ዳግመኛ እንዳይገረፍ ስለፈራና አሬያትንም ስለሚያፈቅራት በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ከተጠየቀው የጥሎሽ ገንዘብ ግማሹን ከዘመዶቹ አሰባስቦ ለአሪያት አባት ከሰጠ በኋላ ቀሪውን በሌላ ጊዜ እንደሚከፍል ተስማምተው ከአሪያት ጋር ትዳር መሰረተ። ቀሪውን ገንዘብ ከስድስት ወር በኋላ አጠናቆ እንደከፈለም አቶ ኡፒቴ ነግረውኛል (ቃሁሳስ 22፤1999)።

ሚስቱን ዘወትር የሚጨቀጭቅና የሚደበድብ ባል ደግሞ ከጥፋቱ እንዲታረም ተመክሮ ካልተመለሰ በሚስቱ ወንድሞች ወይም የቅርብ ዘመዶች ተደቦ ይገረፍና ከድርጊቱ እንዲቆጠብ በድጋሚ ምክርና ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል። ለሶስተኛ ጊዜ ተመሳሳይ ድርጊት ሲፈጽም ከተገኘ እንደገና ተገርፎ ካሳ እንዲከፍል ይገደዳል። በሰው ሚስት ላይ የሀይል ጥቃት የፈጸመም ያለ ጆደንጎ ጣልቃ ገብነት ተገርፎ ካሳ ይከፍላል። የሰው ሚስት መድፈር በአኙዋ ባህል እንደ ከፍተኛ ወንጀል ስለሚቆጠር ቅጣቱ ለገልግል አይቀርም።

አኝዋዎች እርግዝናንና መገለልን ስለሚፈሩ ይህ እንዳይደርስባቸው ልዩ ጥንቃቄ ያደርጋሉ። እርግዝናን አኝዋዎች "አቼኒ" ብለው ይጠሩታል። "አቼኒ ይረደርስብና

በሚል ስጋት ህጻናት ሳይቀሩ ታላላቆቻቸውን ያከብራሉ፣ ትዕዛዛቸውንም ይፈጽማሉ” በማለት አቶ አጉታ ነግረውኛል (ታህሳስ 5፣1999)። አንዳንዶ ከህብረተሰቡ የአኗኗር ሕጎችን በማፈንገጥ ተንኮል፣ ክፋትና ክህደት የፈጸመ፣ ወገኑን በድሎ ያስቀየመ፣ ሰው ገድሎ የደም ካሳ ያልከፈለ ወዘተ ተመክሮ እሻፈረኝ ካለ መገለልና እርግማን ይደርስበታል። እንዋዎች ዛሬን ድረስ እርግማን ይደርሳል የሚል ጽኑ እምነት አላቸው። “እቺን ጥፋተኛን የመቅጫ አንዱ መንገድ ነው። በእቺኒ የአዕምሮ ጭንቀት ውስጥ የገቡ፣ የታመሙና የሞቱ ሰዎች እንዳሉ አውቃለሁ። ሌሎች ሰዎችም በእቺኒ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች መኖራቸውን እንደሚያውቁ ነግረውኛል” ሲሉ አቶ ኝጎዎ አበላ ገልጸውልኛል (ታህሳስ 10፣1999)።

### ፩ የግጭት አፈታት በአኝዋ ረቶች

ተረት በማንኛውም ማህበረሰብ ያለና ህብረተሰቡ ትውልዱን ለማስተማሪያነት የሚጠቀምበት፣ ንጹና ጠቃሚውን እየለየ የሚነገርበት፣ ታሪኩንና ባህሉን የሚያስተላልፍበት የስነቃል አንድ አካል ነው። የማህበረሰቡ ልዩ ልዩ የህይወት ፍልስፍናዎች (World views) እሴቶች፣ ደንቦች፣ ህጎች ታሪካዊ ክንዋኔዎች ወዘተ በተረቶቹ ውስጥ ተካተው ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ ኖረዋል ። ስለዚህ የአንድን ማህበረሰብ ተረቶች ማጥናት በራሱ የህብረተሰቡን ልዩ ልዩ የሕይወት ገጽታዎች ለመረዳት ያስችላል።ይህን በተመለከተ ፈቃደ አዘዘ እንዳለው "የሥነሰብእ (Anthropology) ሊቃውንትም ስለአንድ ማህበረሰብ እምነት፣ አስተሳሰብ ፣ አደረጃጀት፣ አኗኗር፣ ወዘተ ሲያጠኑ መረጃዎቻቸውን ከሚሰበስቡባቸው ምንጮች አንዱ ስነቃል ስለሆነ ተረቶችንም መመልከታቸው አይቀርም" (1991፣53) ። በበርካታ የአኝዋ ተረቶችም የህብረተሰብ ልዩ ልዩ የህይወት ገጽታዎች ሲንጸባረቁ ይስተዋላል ። ከእነዚህ አንዱ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን ይመለከታል ። ተረት የማህረሰቡ የሕይወት ፍልስፍና ነጸብራቅ እንደመሆኑ በአኝዋዎች የዕለት ተዕለት ህይወትና በተረቶቻቸው የሚከሰቱ ግጭቶች አፈታት ተመሳሳይነት አለው። በሽምግልና፣ በውይይት አንዳንዴ ደግሞ ጉልበትን ወይም ሀይልን በመጠቀም ግጭቶችን መፍታት የተለመደ ነው ። ከዚህ በመቀጠል ለምሳሌ ያህል በተመረጡ አንዳንድ ተረቶች (ተረቶቹ አባሪ ተደርገው ቀርበዋል) ውስጥ የግጭት አፈታትን የሚገልጽ ትንተና በአጭሩ ቀርቧል ።

## አኝዋ ተረቶች የግጭት አፈታት ላይ የተደረገ ትንተና

በተረት አንድ በአይጥና ዝንጀሮ መካከል ለተከሰተው አለመግባባት ምክንያቱ እምነት ማጉደል ወይም ለወዳጅ ታማኝ ሆኖ አለመገኘት ነው። በበርካታ ተረቶች ውስጥ ትናንሽና አቅመ ደካማ እንስሳት በብልጣብልጥ ባህሪያቸው ከእነሱ በላይ ጉልበትና ሀይል ባላቸው ላይ ድልን ሲቀዳጁ ማየት የተለመደ ቢሆንም በተረት አንድ የታየው ግን ከዚህ የተለየ ነው። ምክንያቱም አይጥ ለማምለጫነት ባቀረበችው ሃሳብ ስትረታ እናያለን። ግጭቱ የተቋጨበት ሁኔታ እምነት ያጎደለና ወዳጁን የከዳ ከቅጣት እንደማያመልጥና ህብረተሰቡም ከእንዲህ ያለ ተግባር እንዲቆጠብ የሚያስተምርና የሚያስጠነቅቅ ጭምር ሆኖ እናገኘዋለን። ግጭቱ የተፈታውና ሀቁ የወጣው አይጥ ዝንጀሮን ለመግደል



ILS LIBRARY

የሰረቀው ተንኮል መልሶ እራሷን ሲያጠፋት በመቻሉ ነው። በእንዋዎች የእለት ተእለት ህይወት ዉስጥም በመገኛቸ ላይ ተገቢ ያልሆነ በደል የሚፈጽምና ሽረኛ እንደ ጥፋተኛ ተቆጥሮ የሚቀጣበት አግባብ አለ።

በተረት ሁለት ውስጥ የተከሰቱ ግጭቶች ሁለት ሲሆኑ የተፈቱትም በሁለት የተለያየ መንገድ ነው። የመጀመሪያው ግጭት የተከሰተው በአንበሳና ከርከሮ መካከል ሲሆን የግጭቱ ምክንያት አንበሳ ሀይሉን ተጠቅሞ ከርከሮን ሊበላ ማሳደዱ ነው። በሁለቱ መካከል የተፈጠረውን ግጭት ጃርት የፈታችውም ሀይሏን ተጠቅማ ነው። ሀይሉን በመጠቀም የተፈጠረ ግጭት በሀይል ሲፈታ እናያለን። ጃርት አንበሳን ባትገድለው ኖሮ ከርከሮ በአንበሳ ከመበላት ላይተርፍ ይችል ነበር። የጃርትን ውለታ አልረሳም ያለው ከርከሮም ወደ ድርድርና ውይይት ለመምጣት ፍላጎት ያሳየው በጅብ ተገዶ ነው። ጉዳያቸውን በውይይትና በድርድር መፍታት ባለመቻላቸው ደግሞ ጉዳዩ በእንስሳት አገር ሽማግሌዎች እንዲታይ ተደርጓል። ሁለተኛው ግጭት ተከስቶ የምናገኘው በጃርትና ከርከሮ መካከል ነው። መፍትሔ የተደረገለት ደግሞ በሽምግልና ነው። ጃርት ከርከሮ ውለታዬን አልመለሰም በሚል ጅብ በከርከሮ ላይ አደጋ እንዲያደርስ ገፋፍታለች። ይሁን እንጂ ሀይልን በመጠቀም ግጭትን መፍታት ተገቢ አካሄድ እንዳልሆነ በተረቱ ተንጸባርቋል። ስለዚህ ጉዳዩ ወደ እንስሳት አገር ሽማግሌዎች ተመርቶ እንዲፈታ ተደርጓል። ሌላው ከተረቱ የምንረዳው ይቅርታ ከፍ ያለ ዋጋ እንዳለው ነው። ጅብ ከርከሮን ሊበላው ሲል ይቅርታ በመጠየቁ ነው ከመሞት ተርፎ በኋላ ላይ ከጃርት ጋር ለመወያየት ከጅብ ጋር ተያይዘው የሄዱት።እንዋዎችም ለይቅርታ ከፍ ያለ ዋጋ ይሰጣሉ።

በእንዋ የግጭት አፈታት ባህል መሰረት በውይይት ሊፈታ ያልቻለ ግጭት የሚታየው በአገር ሽማግሌዎች ነው። የአገር ሽማግሌዎችም የግጭቱን ምክንያት ከመረመሩ በኋላ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘን ካሳ እንዲከፍል ያደርጋሉ። በተረት ሦስት የተፈጠረው ግጭትም በአገር ሽማግሌዎች መፍትሔ ሲደረግለት እናያለን። የአገር ሽማግሌዎቹ በዶሮዋ ባለቤት ላይ ሲወስኑ የሰጡት ምክንያት ውሻዋ በዶሮዋ ትንኮሳ ተደንብራ ስትሮጥ ጥጃዋ ባትደነብር ኖሮ ህጻኑ አይሞትም ነበር የሚል ነው። ለዚህም ነው የመጀመሪያዋ ተንኳሽ (ዶሮ) ጥፋተኛ ሆና የተገኘችው። ስለዚህ የተሰጠው ውሳኔ በምክንያትና ውጤት (cause and effect) ላይ የተመሰረተ ነው ማለት ይቻላል። በተረት አራትም እናቶቹ በመካከላቸው በተፈጠረ ግጭት ወደ ጠብ አላመሩም። ጉዳያቸውን በቀጥታ ያቀረቡት ለአገር ሽማግሌዎች ነው። የአገር ሽማግሌዎቹ የእንዋን የአገርን ባህል መሰረት በማድረግ ነው ዝሆኑ ለሚገባው ወገን እንዲሰጥ የወሰኑት።



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ነዋቶም የደንየኛል ጥያቄ ሲያቀርቡ ዝሆኑን ለማግኘት ብለው ከተፈጠረው እውነታ ውጭ ሀሰት አልተናገሩም። በእኛዋ ዘንድ ከካርሱኩ ፊት ቀርቦ ሀሰት መናገር የተከለከለ ስለመሆኑ ቀደም ሲል በክፍል አምስት መገለጹ ይታወሳል:: ይህ ሁኔታ በዚህ ተረትም ታይቷል።

በተረት አምስት ለተፈጠረው ግጭት መንስኤ የራስ ባልሆነ ንብረት መጠቀም፣ ዘርፎ ወይም ሌብነት ተደርጎ ሊታይ ይችላል:: የግጭቱ ቆስቋሽም ጅብ ነው:: ጅብ ጉልበቱን ተጠቅሞ የአመልን ፍየሎች ፣ በጎች ፣ ልጆችና ሚስቶቹን እየነጠቀ ባይበላ ኖሮ አመል በጅብ ላይ በቀላ ለመፈጸም አይንሳሳም ነበር:: አመል ጅብን የተበቀለው በዘዴ ነው። በተረቱ እንደተገለጸው አመል እራሱን የሞተ ሰው አስመስሎ በመተኛት የበጎ አቶሉ ከእነ ልጆቹ በጦር ወግቶ ሊገድላቸው ችሉአል:: በሰላማዊ መንገድ ሊፈቱ የማይችሉ ግጭቶችን በሀይል መፍታት በግጭት አፈታት ሂደት የተለመደ ነው:: አመል ጠላቱን ለመበቀል የተጠቀመውም ይህንኑ ነው።

በተረት ስድስት ለተከሰተው ግጭት አንዱ ምክንያት ሌብነት (ጥንቸልና ቀጭኔ ከሰው ማሳ ገብተው ፍራፍሬ መስረቃቸው) ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ለወዳጅ ያለን ታማኝነት ማጉደል (ጥንቸል ለወደጇ ቀጭኔ ታማኝ አለመሆኗ) ነው:: ከተረቱ አትኩሮታችንን ሊስብ የሚችለው የድርጊቱ መከሰት ሳይሆን ጥፋተኛ ላይ የተወሰደው እርምጃ በእኛዋ የእለት ተዕለት ህይወት ከምናየው የቅጣት አይነት ጋር ተመሳሳይ መሆን ነው። ለምሳሌ በክፍል አምስት እንደተገለጸው ለጋብቻ ጥሎሽ ያልከፈለ በቀጥታ ተይዞ በግርፋት ይቀጣል። ቀጭኔም ከገበሬው ማሳ በመገኘቷ የተቀጣችው በግርፋት ነው። በሌላ በኩል ጥንቸል ላጠፋችው ጥፋት ይቅርታ ጠይቃ ከቀጭኔ ጋር ባለመታረቋ በቀላ ተፈጸሞባታል። በአጠቃላይ በተረቱ የታየው ሀይልን በመጠቀም ጥፋተኛ የሚቀጣበት አግባብ መኖሩን ነው።

በተረት ውስጥ ሀይለኞች በደካሞች፣ ጉልበተኞች በአቅመ ቢሶች ሲሸነፉ ማየት የተለመደ እንደሆነ ቀደም ሲል ተገልጾአል:: ይህ የተረት ባህርይ እንደተጠበቀ ሆኖ ግጭቶችና አለመግባባቶች በሰላማዊ መንገድ ብቻ መፈታት አለባቸው ከሚለው የእኛዋዎች አመለካከት አንጻር ስናየው ተረት ሰባት ጉልበተኞችንና ትዕቢተኞችን የሚቀጣ ሆኖ እናገኘዋለን። በሌላ በኩል ደግሞ ጉልበተኛንና ትዕቢተኛን በዘዴ ማሸነፍ እንደሚቻል ብቻ ሳይሆን ደህናው አማራጭ በተሻለ ሁኔታ ለድል እንደሚያበቃ የሚነግረን ተረት ነው። በዝሆንና እንቁራሪት መካከል ለተከሰተው ግጭት ምክንያት ዝሆን እንቁራሪትን በንቀትና በትዕቢት ማየቱ ነው:: በውድድሩ እንደታየው ግን አሸናፊ ሆኖ የተገኘው ጉልበተኛው ዝሆን ሳይሆን ደካማዋና ብልጧ እንቁራሪት ናት:: በሌላ በኩል ጉልበትና ብልሀት ተወዳድረው ብልሃት አሸነፈች ማለት ይቻላል:: ብልሀት ውስጥ

ገን ብቶላ መኖሩንም እናያለን። እንቁራሪት ዝሆንን ልትበቀለው ፈልጋ ነው በዘዴ ከአቅሙ በላይ ውሃ ጠጥቶ እንዲሞት ያደረገችው።

በአንፃሩ የአኗኗር ባህል እንግዳን ተቀብሉ ማስተናገድ የተለመደ ነው። ይሁን እንጂ ግንኙነታቸው እንግዳ ባህሉ ከሚፈቅደው ደንብና ስርዓት አፈንግጦ የተለየ ባህርይ ማሳየት የለበትም። ባህሉ ካስቀመጣቸው ደንቦችና እሴቶች ያፈነገጠ በቤተሰቦቹ ከፍ ሲልም በህብረተሰቡ መገለልና እርግማን ይደርስበታል። እርግማንና መገለል የደረሰበት ደግሞ ከህብረተሰቡ ጋር ተቀላቅሉ በሰላም ለመኖር አይቻለውም። በተረት ስምንት ሆዳሙ ሰውዬ ላይ የተወሰደው የጋራ እርምጃም (Collective action) እላይ ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይ ነው።

የተረት ዘጠነኛ ግጭት የተፈታው ደግሞ በዘዴና በውይይት ነው። ለባልና ሚስት ግጭት ምክንያት ቅናትና ጭቅጭቅ ነው። በአጉል ጥርጣሬና ቅናት ጭቅጭቁን እንዲተው ሚስት ባሏን ለመምከር ሞክራ ነበር። ምክር በራሱ ግጭትን በሰላማዊ መንገድ የመፍቻ አንድ መንገድ ነው። ይህ ሲሳካ ባለመቻሉ ሚስት የፈለገችውን ብታደርግ ባል ሊቀበላት እንደማይችል በተግባር ማሳየትን እንደ አማራጭ ተጠቅማ የተፈጠረውን ግጭት ለመፍታት ችላለች። ለውይይትና ለድርድር አሻፈረኝ ያለ የተቃረነው ወገን አቅም እንዳለውና ተጽዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል ሲረዳ ወደ ውይይትና ድርድር ለመምጣት መገደዱ አይቀርም። በመሆኑም ባል በሚስቱ ላይ ያደረበትን አጉል ጥርጣሬ ሚስት ብታደርገው እንኳ ጭቅጭቅ መፍትሔ እንደማይሆን በመረዳቱ የሚስቱን ሃሳብ ተቀብሉ በመከተላቸው የተፈጠረውን ግጭት በውይይት ለመፍታት ከስምምነት ላይ መድረሳቸውን እናያለን። በተረቱ ሴቶችም ግጭቶችን ለመፍታት አቅም አላቸው የሚል የስርአተ ጾታ (gender) ጉዳይ ተንጸባርቋል ለማለት ይቻላል

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

## ማጠቃለያ

አኝዋዎች በኒያና (ንጉስ) ኳር (የቀበሌ ሹም ወይም አስተዳዳሪ) የሚመሩ ሁለት አይነት ነገር ግን ተመሳሳይ አወቃቀርና አደረጃጀት ያላቸው ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርአት አላቸው። ከክልሉ አስር ወረዳዎች መካከል የአበቦና የጆር ወረዳዎች በከፊል የሚተዳደሩት በኒያ ሲሆን በቀሩት ወረዳዎች ያሉ ቀበሌዎች ግን በኳር ነው። እያንዳንዱ ቀበሌም የራሱ የሆነ ሉአላዊ ነፃነትና ኳር አለው። ማንኛውም ኳር በሌላ ቀበሌ ጣልቃ የመግባት መብት የለውም። በአንድ ቀበሌ የሚኖሩ አኝዋዎች የአንድ ንኡስ ጎሳ አባል የሆኑና ግንኙነታቸውም በዝምድና የተሳሰሩ ሲሆን ኳር የሚመረጠውም ከኳር ቤተሰብ የዘር ግንድ ነው። ኳሮዎች በኒያ አስተዳደር ውስጥ ስልጣን መያዝ ያልቻሉና ከተከታዮቻቸው ወደ ሌላ አካባቢ በመሄድ የቆረቆሩዋቸውን ቀበሌዎች የሚመሩ ናቸው። ከዚህ አንጻር ሲታይ ኳሮዎች ከኒያ ዝርያዎች ጋር ዝምድና ያላቸው ናቸው። ኒያም ቢሆን በሌሎች የግዛት ክልል ጣልቃ በመግባት ተጽዕኖ ለማሳደር የሚያስችል ምንም አይነት ስልጣን የለውም። ስልጣኑ በግዛት ክልሉ ብቻ የተወሰነ ነው።

በጥናቱ እንደታየው በሁለቱም ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርአቶች አንድ ኒያ ወይም ኳር ሲሞት በአባቱ ኑዛዜ መሰረት የተመረጠ ወንድ ልጁ ስልጣኑን ይወርሳል። ሴቶች ግን ስልጣን ለመውረስ አይፈቀድላቸውም። ስልጣን ወደ ልጅ የሚተላለፈው በአባት ኑዛዜ መሰረት ቢሆንም ወራሽ በደንቡ መሰረት ለመሪነት የሚያበቁ መስፈርቶችን ካላሟላና ህዝባዊ ድጋፍ ከሌለው በስልጣን መቆየት አይቻለውም። የአኝዋ መሪዎች በስልጣን ላይ መቆየት የሚችሉት የህዝቡን ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶች ማሟላት እስከቻሉ ድረስ ብቻ ነው። ይህን ማድረግ ካልቻሉ በሰላማዊ መንገድ ወይም አጌም እየተባለ በሚጠራ ህዝባዊ አመጽ ከስልጣን ወርደው በምትካቸው ሌላ ይመረጣል። እንዲህ ያለው የህዝብ መብትና ነጻነት ከኒያ ይልቅ በኳር አስተዳደር ጎልቶ ይስተዋላል። ኒያን የሚያሰጋው ስልጣኑን በሚቀናቀኑ በእናት የማይገናኛቸው ወንድሞቹ (ኒያዎች ከአንድ በላይ ካላቸው ሚስቶች በርካታ ልጆች ሊኖሯቸው ይችላል) ተቃውሞና አመጽ ካስነሱ ብቻ ነው። በአስተዳደሩ ደንብ መሰረት መሪው ህዝብን ማስተባበር የሚችል፣ በየጊዜው ግብር የሚያበላ፣የተቸገረን፣ የሚረዳ፣ ከመጥፎ ስነምግባሮች የራቀ፣ ለግል ጥቅሙ የማይሯሯጥ፣ ለህዝብ ከበሬታ ያለው ወዘተ መሆን አለበት። ይህን ያላሟላ ለስልጣን አይበቃም። ስልጣን ላይ ያለም ቢሆን እነዚህን መስፈርቶች በጎደለ ጊዜ ከስልጣን እንዲወርድ የሚደረግበት ስርአት አለ። ህዝቡም ለመሪው ተገቢውን ክብርና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት።

የመሪነት ስልጣን በውርስ የሚገኝ ቢሆንም መስፈርቶችን ያጓደሉና የህዝብ ድጋፍ ያጡ ደግሞ በሰላማዊ መንገድ ወይም በሀይል ከስልጣን የሚወገዱበት አግባብ

አሉ፡ በእነዚህም የህይወት ፍልስፍና (World view) የስልጣን ምንጭ ህዝብ፣ ለስልጣን የሚበቃም ደንቡና ስርዓቱ በሚፈቅደው መሰረት የህዝብን ይሁንታ ያገኘ ብቻ ነው የሚል ግንዛቤ አለ ማለት ይቻላል። ሕዝብ በመረጠዉ መሪ ላይ እምነቱ ካጣና ሁኔታውን መቀጠል ካልቻለ በሰላማዊ መንገድ ከስልጣን እንዲወርድ ማድረግ ደግሞ እንዱ የዲሞክራሲ ባህል መገለጫ ነው። ከዚህ አንፃር ስታይ የእኛዋ ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርዓት የዲሞክራሲ ባህሪያት እንዳሉት ለመገንዘብ ተችሎአል።

በሁሉቱም የአስተዳደር ስርአቶች እንደታየው ተዋረዱን የጠበቀ አስተዳደራዊ መዋቅርና ባለስልጣናትም አሉ። ከፍተኛ የሆኑ አስተዳደራዊ፣ ፖሊቲካዊና ማህበራዊ ጉዳዮች በራያ ተመክሮ ውሳኔ የሚተላለፈው ደግሞ በመማክርት ሸንጎ ነው። ይህ የመማክርት ሸንጎ በኘያ አስተዳደር «ችምት» በኣሮ ደግሞ «ጀቡራ» እየተባለ ይጠራል።

በእነዋ ሀገረሰባዊ አስተዳደርም ሆነ የፍትህ ስርዓት ማንኛውም ግጭት መፈታት ያለበት በባርሎክ የግጭት መፍቻ ተቋም ስነስርዓትና ልማዳዊ ህጎች መሰረት በሰላማዊ መንገድ ብቻ ነው። ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችና ተቋማት በማንኛውም ማህበረሰብ የሕይወት ተሞክሮ ላይ ተመስርተው የተፈጠሩና የሕብረተሰቡን ይሁንታ ያገኙ በመሆናቸው ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የጎላ ድርሻ አላቸው። እነዋዎችም በባርሎክ ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋምና ልማዳዊ ህጎቻቸው መሰረት ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ እየፈቱ ለዘመናት አብረው ለመኖር ችለዋል። በካርሎክ ተቋም የዳኝነት ስራን የሚያከናውኑ ጀዶንጎዎች (የአገር ሽማግሌዎች) ናቸው።ይህ ሁኔታ በተረቶቻቸውም ጎልቶ ይስተዋላል። ጀዶንጎዎች ልማዳዊ ህጎችን መሰረት አድርገው ለመስራት ችሎታ ያላቸው ፣ አድሉ የማይፈጽሙና ለህሊናቸው ብቻ የሚገዙ ናቸው የሚል የጋራ ስምምነት ስላለ በህብረተሰቡ ዘንድ አመኔታ የተጣለባቸው ናቸው። ህብረተሰቡም የጀዶንጎዎችን ውሳኔ ያከብራል፣ በውሳኔ አሰጣጥ ላይም አስተያየት በመስጠት ተሳትፎ ያደርጋል። በማንኛውም የካርሎክ ስነስርአት ላይ ሆነ ብሎ ፍትህ ማቀነትና በሐሰት መመስከር እንደነውር የሚታይና የተወገዘ ነው።

በእነዋ ልማዳዊ ህግ መሰረት ከተከሰተው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ እንዲከፈልና እርቅ እንዲደረግ ከማድረግ ባለፈ በማንኛውም ሁኔታ ወንጀለኛን በሞት መቀጣት የተከለከለ ነው። በተለያዩ ምክንያቶች ለሚከሰቱ ግጭቶችና ግጭቱን ተከትሎ ለሚደርስ የንብረትና የአካል ጉዳት ሊከፈል በሚገባ የካሳ አይነትና መጠን ላይ የጋራ ስምምነት ያለ ሲሆን በጋራ ስምምነቱ መሰረት ካሳውን መክፈል ግዴታ ነው። በካርሎክ ተቋምና ሀገረሰባዊ ህጉ ደንቡና ስነስርአት ግጭቶች በዋናነት የሚፈቱት በሽምግልና ፣ በድርድርና በውይይት ቢሆንም በተወሰነ ደረጃ ደግሞ በግርፋት ሊያስቀጡ የሚችሉ



ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

ተለያይተው የተቀመጡ ጥፋቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ የሰው ሚስት የደፈረና ጥሎሽ ያልከፈለ ያለ አገር ሽማግሌዎች ጣልቃ ገብነት ተይዞ በግርፋት ይቀጣል፡፡ እርግማንና መገለልን የሚያስከትሉ ጥፋቶችም አሉ፡፡ ለምሳሌ ደሃ ወገኑን ያገለለ ፣ ስግብግብ ወዘተ እርግማን ያደረሰባቸው ወይም ከወገኑ የመገለል እጣ ይገጥመዋል፡፡ ካሳ ለመክፈል አሻፈረኝ ያለ ደግሞ በቀል ሊፈጸምበትም ይችላል፡፡ ካሳ እንዲከፈል የሚደረገው ብቀላ እንዳይፈጸም ለመከላከል ጭምር ነው፡፡ በተለያዩ የአኝዋ ቀበሌዎች ወይም አጎራባች ብሔረሰቦች መካከል ግጭት ሲከሰት የሚፈታው ደግሞ «አቻንግ ዶዎቶ» (ህዝባዊ ኮንፈረንስ) በሚባለዉ ነው፡፡ በአቻንግ ዶዎቶ የተጋጩ ቀበሌ ነዋሪዎች በመሪዎቻቸውና የአገር ሽማግሌዎች አስተባባሪነት ተገናኝተው የተከሰተውን ግጭት በውይይትና በሽምግልና ይፈታሉ፡፡

አኝዋዎች ሀገረሰባዊ የፍትህ ስርአታቸው ፍትሀዊና የህብረተሰቡን ፍላጎት ያማከለ ነው የሚል እምነት አላቸው፡፡ በክርሉክ የግጭት መፍቻ ተቋም መርህ መሰረት ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ከመፍታት በላይ የተጋጩ ወገኖችን በማስታረቅ ወደ ቀድሞ ሰላማዊ ግንኙነታቸው እንዲመለሱና በአካባቢው ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን ማስቻል ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ ጥፋተኛ ክርሉክ ቀርቦ በአገር ሽማግሌዎች የተወሰነበትን የካሳ ክፍያ መፈጸም አለበት፡፡ ሞት ያስከተለ ግጭት ከሆነ ደግሞ «ጎር ቶንግ» በሚባለዉ ዳግም ለቱም በቀል ላለመፈላለግ ቃል ኪዳናቸውን በመሀላ ያረጋግጣሉ፡፡ የገደለ ወንጀል ፈጻሚ በፍርድ ቤት የተቀጣ ወይም የእስር ዘመኑን ጨርሶ የተለቀቀም ቢሆን ከተጋጨው ወገን ጋር እንደ ቀድሞው በሰላም ለመኖር በባህሉ መሰረት የጎር ካሳ ከፍሎ እርቅ መደረግ አለበት፡፡ ይህ ካልሆነ ብቀላ መፈጸሙ ስለማይቀር ችግሩን በመንግስት ፍርድ ቤት ውሳኔ ብቻ ከመሰረቱ ለመፍታት ያቸግራል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ህብረተሰቡ ሀገረሰባዊ ተቋማቱ በመቻቻልና በሰላማዊ መንገድ ግጭቶችን ለመፍታት የማስተማሪያ መድረክም በመሆናቸው በክልሉ የሰላምን ባህል ለመገንባት በሚደረገው ጥረት የጎላ ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡ የክልሉ መንግስትም ከ1993 እ.ኤ.አ ወዲህ በአካባቢው ተከስተው የነበሩ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታትና ህብረተሰቡን ስለሰላም ለማስተማርና ለመቀስቀስ በሚደረገው እንቅስቃሴ እገዛ እንዲያደርጉ የአገር ሽማግሌዎች አማካሪ ምክር ቤቶችን በክልልና በወረዳ ደረጃ አቋቁሞ እየሰራ ይገኛል፡፡ የሽማግሌዎች አማካሪ ምክር ቤቶች ተግባራቸውን እያከናወኑ ያሉት ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን በመጠቀም እንደሆነ የምክር ቤቱ አባል የሆኑት አቶ ዑቢያ ኦታሬ ነግረውናል፡፡ ይህንን ስናይ በአካባቢው ሰላምና መረጋጋትን ለማስፈን ሀገረሰባዊ ተቋማቱ ጠቀሜታ እንዳላቸው መንግስት እየተገነዘበ የመጣ ይመስላል፡፡

ያሉንጊታ

1 ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋማቱ ለህብረተሰቡ ቅርበት ያላቸውና ፍትሀዊ እንደሆኑ የሚታመንባቸው ናቸው። ለግጭቶች መፍትሔ ከተሰጠ በኋላ በሰላም አብሮ ለመኖርና ግጭቶችን በጋራ ለመከላከል ቃል ኪዳን የሚገባበት ስርአትም አለ። ስለዚህ ለአካባቢው የሰላም ባህል ግንባታ ተቋማቱ ጉልህ ድርሻ ሊኖራቸው ስለሚችል ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።

2 ስለግጭት አፈታት ደንብና ስርአት ዕውቀቱ ያላቸው የአገር ሽማግሌዎች ዕውቀታቸውን ለወጣቱ ትውልድ እንዲያስተላልፉና ግጭቶችን በመከላከልና ከተከሰቱም ለመፍታት በሚደረግ እንቅስቃሴ ተሳትፎአቸውን ማጠናከርና ማበረታታት ያስፈልጋል።

3 የክልሉ ሰላምና መረጋጋት ሊመጣ የሚችለው በውጭ ሀይል ሳይሆን ህዝቡ በራሱ የባህል እሴቶች ተጠቅሞ ሙሉ ተሳትፎ ማድረግ ሲችል ነው። ስለሆነም የክልሉ መንግስት ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን መለስ ብሎ ሊያጠናቸውና ሊጠቀምባቸው ይገባል።

4 ከወጣቱ ትውልድ ዘንድ ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋማትና የመሳሰሉ ጠቃሚ የባህል እሴቶች በቂ ግንዛቤ ያለ መስሎ አይታይም። ስለዚህ ስለተቋማቱ ጥናት ማካሄድና መጪው ትውልድ በአግባቡ እንዲያውቃቸውና ስለፋይዳቸው እስከ ታችኛው ማህበረሰብ ወርዶ ማስተማር ያስፈልጋል። በተለይ የባህልና ትምህርት ቢሮዎች በዚህ ዙሪያ ሰፊ ስራ መስራት ይጠበቅባቸዋል። ይህ ጉዳይ በክልሉ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥም ሊካተት ይገባል።

5 ግጭቶችን ለመከላከልና ለመፍታት የሚያስችሉ ፖሊሲዎችና ህጎች ሲወጡ ፖሊሲ አውጪዎች ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን በአግባብ ማጤንና የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ያስገባ ፖሊሲ ለማውጣት ሊጠቀሙባቸው ይገባል።

## ዋቢ መጻሕፍት

### በአማርኛ የተጻፉ ምንጮች


ባይለየኝ ጣሰው፣ የእኛዋ ቀራቶች (ሌር ዋቹ እኛዋ)፣ አዲስ አበባ፣ርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ 1995።

የኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሕግ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1952።

የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1930።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1987።

የጋምቤላ ነጋሪት ጋዜጣ፣ የጋምቤላ ሕ/ብ/ክ/መንግስት ሕገ መንግስት ማጽደቂያ አዋጅ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1997።

ፈቃደ አዘዘ፣ የስነቃል መምሪያ፣ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፣ 1991።

Abraham Sewonet . 2004. "Breaking the Cycle of Conflict in Gambella Region." In Pankhurst Alula and Francois Piguect. (eds.). People, Space and the State: Migration,Resettlement and Displacement in Ethiopia. Addis Ababa.

Assefa Abebe.2005. "Indigenous Mechanisms for the Prevention of Conflict: The Experience of the Oromo." In Proceedings of the second National Work shop of the Ethiopian Chapter of OSSREA. Addis Ababa.

Bahru Zewde.1976. Relation between Ethiopia and the Sudan. Western Ethiopian Frothier (1898 - 1935). Ph.D. thesis, School of Oriental and African Studies, University of London.

Bahru Zewde and Pousewang, Siegfried.(eds.).2002. Ethiopia: The Challenge of Democracy from Below. Sweden: Elanders Gotab.

Bayelign Tassew. 1999. "An Anyuaa Oral Prosse Narratives and its Social Functions." M.A thesis. Department of Ethiopian Language and Literature, school of Graduate Studies, Addis Ababa University.

______ "An Anyuaa (Anuak) Myth and its Implication in "Kwor"." In the Proceedings of the first National Workshop of the Ethiopian Chapter of OSSREA. Addis Ababa: Image Printing Press.

Befekadu Zeleke and Diribssa Abate. 2005. "Inter-State Ethnic Conflict:Theory and Implications for Ethiopia." In Conflict in the Horn: Prevention and Resolution. Proceedings of the Second National Workshop of the Ethiopian Chapter of OSSREA. Addis Ababa.

Carol, E.R., Melvin E. and Peter N.P. 2002. Anthropology. India: Replika Press.

Central Statistical Authority. 1995. The 1994 Population and Housing Census of Ethiopia. Addis Ababa.

Charter of the United Nations. 1945.

Cohen, Percy.1968. Modern Social Theory. London: Heinemann.

Colson, Elizabeth. 1995. The Contentiousness of Disputes. In Pat Capalan. Understanding Disputes: The Politics of Argument. Oxford: Bery Publishers.

Coser, Lewis A. 1956. The Function of Social Conflict. New York:Basic Books Inc. Publishers.

David Rene. 1967. "Source of the Ethiopian Legal System." In Journal of Ethiopian Law. Vol. V, No.2.

Ellman. Antony O. 1972. "An Agricultural and Socio-Economic Survey of South Sudan Refugee Settlements and Surrounding Areas in Ethiopia." Institute of Agricultural Research.

Etal Fisher. 2000. Working with Conflict, Skills and Strategies for Action. London: Zed Books Ltd.

Evans Pritchard, E.E.1940. The Political System of the Anuak of the Anglo-Egyptian Sudan. London: Percy Lund, Humphries and Co.Ltd.

Fekade Azeze. Comp. 2004. "Some Studies on Traditional and Related Methods of Conflict Resolution." Unpublished Collection.

George Krzeczumowicz. 1965. "Code and Custom in Ethiopia." In Journal of Ethiopian Law. Vol. II, No.2.

Fry Douglas. 1996. Conflict and Aggression, In David Livenson and Melvin Ember. (eds.) Encyclopedia of Cultural Anthropology. New York: Henry Holt and Company, Vol. I.

Greenberg, J.H. 1963. The Languages of Africa. The Hague: Mouto and Co.

Haviland. William A. 1997. Cultural Anthropology. USA: Holt Rinehart and Winston, Inc.

Hoebel Adamson. (ed.).1966. Anthropology: The Study of Man USA: Mcgrawhill, Inc.

Hussein Jemma. 2005. "Ethnic Conflict as a Global Political Problem:Review of Conceptual and Theoretical Perspectives." In Conflict in the Horn: Prevention and Resolution. Proceedings of the second National Workshop of the Ethiopian Chapter of OSSREA. Addis Ababa.

Gluckman, Max. 1965. Custom and Conflict in Africa. Oxford: Basil Blackwell.

Kelemework Tafere and Mitiku Haile. 2005. "Indigenous Institutions of Conflict Resolution among the Ab' Ala Afar of North-Eastérn Ethiopia." In Proceedings of the Ethiopian Chapter of OSSREA. Addis Ababa.

Kurimoto. E. 1992. "Natives and Outsiders: The Historical Experience of the Anyuaa of Western Ethiopia. " In Journal of Asian and African Studies. No.43.

______ 2001. "Capturing Modernity among the Anyuaa of Western Ethiopia." In Kurimoto.(ed.). Rewriting Africa Towards Renaissance or Collapse? The Jaica Center for African Studies. National Museum of Ethnology, Oska.

1996. "People of the River: Subsistence Economy of the Anyuaa of Western Ethiopia." In Shunsato and Kurimoto. (eds.). Essay in Northeast African Studies. Koyoto: Northeast African Studies. Koyoto National Museum of Ethnology.

Lienhardt, Godfrey. 1957. "Anuak Village Headmen." In Daryll Forole.(ed.). London: Oxford University Press, Vol. 27.

Monique , Mekenkamp,Tongeren , van and Veen, Hans van de. (eds.).1999. Searching for Peace: An Overview of Conflict Perventation and Management Activities. The Netherlands: Haasbeek, Alphen Alb Rijn.

Muradu Abedo. 2003. "The Development of the Ethiopian Legal System." Note on Customary Law. Law Faculty, Addis Ababa University.

Organization of African unity Charter.1963. Addis Ababa.

Proceedings of the First National Conference on Federalism, Conflict and peace Building. 2004. Published by Minstry of Federal Affairs. Addis Ababa: United Printing Enterprise.

Simmel, Gerg. 1955. Conflict. New York: The Free Press.

Swingle, Paul. 1970. The Structure of Conflict. New York: Academic Press.

Tsega Endalew. 2005. "Luba Basa and Harma Hodha: Traditional Mechanisms for Conflict Resolution in Metekkel, West Gojam." In Conflict in the Horn: Prevention and Resolution. Proceedings of the Second National Work shop of the Ethiopia Chapter of OSSREA. Addis Ababa.

Wolfgang, Hienrich. 1997. Building the Peace: Experience of Collaborative Peace Building in Somalia (1993-1996). UK: Ipswich Book Company Ltd.



...S LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

## የመረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር

| ተ.ቁ | ስም | ጾታ | ዕድሜ የተነገረኝ በግምት ነው | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | [illegible] | ወ | 56 | በአንስተኛ የንግድ ስራ የተሰማሩና የክልሉ አማካሪ የአገር ሽማግሌዎች ምክር ቤት አባል ሲሆኑ ለረጅም ጊዜ በሽምግልና ስራ ተሳትፎ አድርገዋል:: ስለአኙዋ ባህልና ታሪክም በቂ ግንዛቤ አላቸው:: ስለሀረሰባዊ አስተዳደርም በሚገባ ያውቃሉ:: |
| 2 | [illegible] | ወ | 65 | በአሁኑ ጊዜ ጡረታ ላይ ያሉና ቀደም ሲል ኳሮ የነበሩ ናቸው:: ስለኳሮ አስተዳደር ታሪክም የሚያውቁ ናቸው:: |
| 3 | [illegible] | ወ | — | በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የዲሞክራታይዜሽን መምሪያ ቀጠባቂ መምሪያ ኃላፊ:: |
| 4 | [illegible] ኡመድ | ሴ | 42 | የክልሉ ሴቶች ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ሲሆኑ በተለይ ከጋብቻ ጋር በተያያዘ ስለሚከሰቱ ግጭቶች በበቂ ሁኔታ ያውቃሉ:: |
| 5 | [illegible] | ወ | 72 | ጡረተኛ ሲሆኑ ስለአኙዋ ሀገረሰባዊ አስተዳደርና ቃል ታሪኮች በበቂ ሁኔታ ያውቃሉ:: ቀደም ሲልም ኳሮ ነበሩ:: |
| 6 | [illegible] ኡመድ | ወ | 48 | በክልሉ ትምህርት ቢሮ የስርአተ ትምህርት ቡድን መሪ:: አቶ አቡላ ስለብሔረሰቡ (አኙዋ) ባህልና ታሪክ መረጃዎችን የማሰባሰብ ልምድ አላቸው:: |
| 7 | [illegible] ኡመድ | ሴ | 52 | የቤት እመቤት ሲሆኑ በልዩ ልዩ ማህበራዊ ጉዳዩች ተሳትፎ በማድረግ ይታወቃሉ:: |
| 8 | [illegible] ኡመድ | ወ | 70 | በተቢቃ ሥራ ላይ ያሉ ሲሆን ስለሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርአት የሚያውቁ ናቸው:: |
| 9 | [illegible] | ወ | 74 | በጡረታ ላይ ያሉ ሲሆን በተለይ በቀበሌዎችና በብሔረሰቦች መካከል ስለሚከሰቱ የግጭት ምክንያቶችና ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ዘዴ የረጅም ጊዜ እውቀት እንደላቸው በአካባቢያቸው ይታወቃሉ:: በሽምግልና ስራም ለረጅም ጊዜ ተሳትፈዋል:: በረኪታ ቃል ታሪኮችንም ያውቃሉ:: |
| 10 | [illegible] | ወ | 70 | ስለአኙዋ ባህልና ቃል ታሪኮች (Oral narratives) በመተረክ የሚታወቁ ጡረተኛ ናቸው:: |
| 11 | [illegible] | ሴ | 74 | የኚያ ባለቤት የነበሩ ሲሆን የኚያ ሹመት ስነስርአት ሲከናወንም በአካል የነበሩና ስለሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርአቱ በአካል የተመለከቱትን በሚገባ ያስታውሳሉ:: |
| 12 | [illegible] | ወ | 73 | በጡረታ ላይ ያሉ ሲሆን ስለሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርአት መረጃ በመስጠት ተባብረውኛል:: |



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

| ተ.ቁ | ስም | ጾታ | ዕድሜ | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|
| | ኡሙር ኡበላ | ወ | 62 | በግብርና ስራ ላይ የተሰማሩና ስለአኘዋና ኑዌር ብሔረሰቦች ግንኙነት የሚያውቁ ሰው ናቸው:: ስለህገረሰባዊ የአስተዳደር ስርአትም በሚገባ ያውቃሉ:: |
| | ኡሙድ ኡጂሉ | ወ | 47 | በግብርና ስራ የተሰማሩና ስለአኘዋና ኑዌር ብሔረሰቦች ግንኙነት የሚያውቁ ሰው ናቸው:: ስለህገረሰባዊ የአስተዳደር ስርአትም በሚገባ ያውቃሉ:: |
| | ኡሙድ ኡኬኝ | ወ | 58 | በግብርና ስራ የተሰማሩ ሲሆኑ ስለአኘዋ ባህልና ታሪክ በመተረክ ይታወቃሉ:: ስለህገረሰባዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችም በቂ ዕውቀት እንዳላቸው በአካባቢያቸው ይታወቃሉ:: |
| | ኡግን ኡጂሉ | ወ | 46 | ቢጋምቤላ ዙሪያ ወረዳ ፍርድ ቤት ከፍተኛ የአቃቢ ህግ ባለሙያ:: |
| | ኡግት ኡግን | ወ | 48 | የትምህርት ደረጃቸው ዲፕሎማ ሲሆን በክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም መምሪያ ኃላፊ ናቸው:: ስለአኘዋ የግጭት አፈታት ዘዴዎች በቂ ግንዛቤ አላቸው:: |
| | ኡዶላ ኡሙድ | ወ | 49 | በመለስተኛ የጉልበት ስራ የተሰማሩና በርካታ ቃል ታሪኮች የሚያውቁ ናቸው:: ስለህገረሰባዊ አስተዳደርና የግጭት አፈታት ዘዴዎችም ያውቃሉ:: |
| 19 | ኡዋር ኡባላ | ወ | 60 | ጡረታ የወጡ መምህር ሲሆኑ ስለአኘዋ ሀገረሰባዊ አስተዳደርና የግጭት አፈታት ዘዴዎች ዘርዘር ባለሁኔታ የመግለጽ ችሎታ አላቸው:: ተረት በመተረትም ይታወቃሉ:: |
| 20 | ኡጂሉ ኡዶንግ | ወ | 60 | ቀደም ሲል በፍትህ ቢሮ ይሰሩ የነበሩና አሁን በጡረታ ላይ ያሉ:: በሽምግልና ስራም የረጅም ጊዜ ልምድ አላቸው:: |

| ተ.ቁ | ስም | ጾታ | ዕድሜ | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|
| [illegible] | [illegible] | ወ | 47 | በተለይ የሚታወቀው በአኝዋ ባህላዊ ሙዚቃ ነው። ቃል ታሪኮችንም በሚገባ ያውቃል። |
| [illegible] | [illegible] | ወ | 57 | የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ። ስለአኝዋ ባህልና ቋንቋ መረጃዎችን በማሰባሰብ ላይ ይገኛሉ። ስለአኝዋ ባህልና ታሪክም በሚገባ የሚያውቁ ናቸው። ቀደም ሲል በመምህርነት ያገለገሉ ሲሆን ከጋምቤላ ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በዲፕሎማ ተመርቀዋል። |
| [illegible] | [illegible] | ወ | 72 | በጡረታ ላይ ያሉ ሲሆን ስለአኝዋ ባህልና ታሪክ ዘርዝር ባለ ሁኔታ እንደሚያውቁ ከሚነገርላቸው የአገር ሽማግሌዎች አንዱ ናቸው። |
| [illegible] | [illegible] | ወ | 62 | በክልሉ የአገር ሽማግሌዎች አማካሪ ምክር ቤት አባል ሲሆኑ ስለአኝዋ ባህልና ታሪክም በሚገባ ያውቃሉ። |
| [illegible] | [illegible] | ወ | 44 | የክልሉ አስተዳደር፣ ፍትህና ጸታ ጉዳዬች ቢሮ ኃላፊ (ከሱዌር ብሔረሰብ)። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ስለተከሰቱ ግጭቶችና ስለተፈቱበት አግባብ መረጃዎችን በመስጠት ተባብረውኛል። |
| [illegible] | [illegible] | ወ | 65 | ቀደም ሲል የወረዳ አስተዳደሪ የነበሩና በአሁኑ ጊዜ በክልሉ እርሻ ምርምር ቢሮ የሚሰሩ። አቶ ፊሊፕ ከልምድም ጭምር ስለአኝዋ ህገረሰባዊ አስተዳደር፣ የግጭት አፈታት ዘዴዎችና የአኝዋ ቃል ታሪኮችን በተመለከተ ጠለቅ ያለ ዕውቀት አላቸው። |
| [illegible] | [illegible] | ወ | 49 | በክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የባህል መምሪያ ኃላፊ ሲሆኑ በአኝዋ ባህል ላይ መረጃዎችን በማሰባሰብ ጥናት ስለሚያካሂዱ ስለአኝዋ ባህልና ታሪክ በሚገባ ያውቃሉ ከሚባሉት አንዱ ናቸው። የትምህርት ደረጃቸውም ዲፕሎማ ነው። |
| [illegible] | [illegible] | ወ | 79 | ጡረተኛና ታዋቂ የአገር ሽማግሌ ሲሆኑ ስለአኝዋ ባህልና ታሪክ እንዲሁም ቃላዊ ታሪኮች በሚገባ ያውቃሉ። |

## አሥራ አንድ ሚቶች (myths)

አንዋሮች እውነተኛ የታሪካችን አካል ናቸው ብለው የሚተርኩዋቸውን ቃል ትረካዎች (Oral narratives ) «ሳም» ብለው ይጠሩዋቸዋል:: እነዚህ ሳም የሚባሉት የሚት (Myth) ባህሪይ ያላቸው ሲሆኑ አንዳንዶቹ ስለህገረሰባዊ አስተዳደርና የግጭት አፈታት ዘዴዎች አጀማመር የሚያወሱ ናቸው:: ይህን በተመለከተ «ኡቹዶን» መሰረት አድርገው ከሚተረኩ ሚቶች የሚከተሉት ይገኙበታል::

ሚት 1

በዱሮ ጊዜ ኡኪሮ የሚባል በውሃ ውስጥ የሚኖር ሰው ነበር:: አንድ ቀን ሁለት ጎረምሶች ከወንዝ ያጠመዱትን አሳ ጭራና ጭንቅላት ይዘው እየተጎተቱ ለእኔ ይገባል በማለት ሲነታረኩ ኡኪሮ ሰምቶ ወደ ወጣቶቹ ይመጣና ለምን እንደሚጣሉ ጠየቃቸው:: አንደኛው ወጣት አሳው ከወንዝ ውስጥ ሳለ ቀድሞ በጦር የወጋው እሱ መሆኑን ፣ ሌላኛው ደግሞ የተወጋውን አሳ «ቀድሜ ከወንዝ ያወጣሁት እኔ ነኝ» በሚል ሁለቱም በእኩል ይገባኛል ጥያቄ እየተጨቃጨቁ መሆናቸውን ለኡኪሮ ገለጹለት:: ኡኪሮም የወጣቶቹን አቤቱታ ካዳመጠ በኋላ በመጀመሪያ የአሳውን ጭንቅላት ይዞ ለነበረው ልጅ አሳውን እንዲለቅ አዘዘው:: ወጣቱም እንደታዘዘው አሳውን ሲለቅ ጭራውን ይዞ ከነበረው ልጅ አሳው አሟልጦት መሬት ይወድቃል:: ኡኪሮም እንደገና አሳውን አንስቶ እንደ ቀድሞአቸው እንዲቆሙ አደረገና ከጭራው የያዘውን ልጅ በተራው የአሳውን ጭራ እንዲለቅ አዘዘ:: በዚህ ጊዜ አሳው ጭንቅላቱን ይዞ ከነበረው ልጅ እጅ ሳያመልጥ በመቅረቱ ኡኪሮ አሳው «ለአንተ ይገባሃል» ሲል ፈረደለት:: ወጣቶቹም በኡኪሮ ውሳኔ ተስማምተው ወደ መንደራቸው ከተመለሱ በኋላ ስለገጠማቸው ሁኔታ ለመንደርተኛው ሲናገሩ ችዋይ የሚባል የቀበሌያቸው አስተዳዳሪ የነበረ ባላባት ሰምቶ ኡኪሮ ተይዞ እንዲቀርብለት አዘዘ:: በማግስቱ ጠዋት የመንደሩ ጎረምሶች የታዘዙትን ለመፈጸም ወደ ወንዙ ሄደው ከመካከላቸው ሁለቱ የተጣሉ ለመምሰል ይነታረኩ ጀመር:: ኡኪሮም ንትርካቸውን ሰምቶ ቀደም ሲል እንዳደረገው ሊዳኛቸው ሲመጣ አዘናግተው በመያዝ ወደ ችዋይ ወሰዱት:: ችዋይ ኡኪሮን ካነጋገረ በኋላ የተጣሉ ሰዎችን ታስታርቅልናለህ በማለት አብሮት እንዲኖር ጠየቀው:: ኡኪሮ ግን እንቢ በማለት በአካባቢው ለነበሩት ሰዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንዲመልሱለት ጠየቃቸው::

«ሴት ልጆቻችሁን ነጥቄ ብወስድባቸው ምን ይሰማችኋል?» ህዝቡም በአንድ ድምጽ «ምንም አይሰማን» ሲሉ መለሱለት::

በመቀጠልም «ወንድ ልጆቻችሁንስ?» ሲል ጠየቀ::

ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

«ምንም አንልህ» በመጨረሻም «ሚስቶቻችሁን ነጥቁ ብወስደስ?» ብሎ ሲጠይቅ ሁሉም ጸጥ አሉ። አኪሮም «የሰው ሚስት መንጠቅ መጥፎ ተግባር ነው» ብሎ ህዝቡን ከመከረ በኋላ «ስእንግዲህ የሰው ሚስት ያማገጠ በጦር መወጋት አለበት» በማለት ይህ ተግባራዊ እንዲሆን አዘዘ።

በሌላቱ አኪሮ ከችዋይ ቤት አድሮ ነበር:: ችዋይም እንግዳውን ተቀብሎ ኮሪ የምትባል ልጇን ጋፃና ውሃ እንድትሰጠውና እንድታስተናግደው አድርጎ ነበር:: አኪሮም የቀረበለትን ጋፃ ከጨለና ውሃውን ከጠጣ በኋላ ከተዘጋጀለት ጎጆ ገብቶ ተኛ:: የአኪሮን መተኛት ችዋይ ባወቀ ጊዜ ኮሪ አብራው እንድታድር አዘዛት:: ኮሪም ከአኪሮ ጋር አደረች። በማግስቱ ጠዋት ኮሪ ከእንቅልፏ ሳትነቃ አኪሮ በአንገቱ አጥልቆት የነበረውን አቾክ የሚባል ጨሌ ከትራስጌዋ አኑሮ ወደ መጣበት ወንዝ ተመልሶ ሄደ:: ከዚያን ሌሊት ጀምሮ አኪሮ ዳግም አልተከሰተም። ኮሪ ከአኪሮ ጸንሳ ስለነበረ ጊሎ የሚባል ወንድ ልጅ ወለደች። ጊሎ ለአቅመ አዳም በደረሰ ጊዜ አባቱ ትቶት የሄደውን አቾክ በአንገቱ አጥልቆ የአኝዋ ኚያ (ንጉስ) ተብሎ ነገሰ::

ሚት 2

በሚት አንድ መሰረታዊ ይዘት ላይ ለውጥ ባይኖርም ከሽማግሌዎች የሰማሁት ነው ሲሉ አቶ አኛይ ኡዶል የሚከተለውን ነገረውኛል::

አባ ለማጥመድ ወደ ወንዝ የሄዱት አቻላና አቻንግ የሚባሉ ልጃገረዶች ናቸው:: ሁለቱ ልጃገረዶች በአሳ ይዞቸል ጥያቄ ሲጨቃጨቁ ሰምቶ የገላገላቸው ኡቼዶ የሚባል በወንዝ ውስጥ ይኖር የነበረ ሰው ነው። የመንደሩ ወጣቶች ኡቼዶን ለመያዝ ወደ ወንዝ ሲሄዱ ዱል ጆክ (የንገድ ትማች) ላይ ከወንዙ ዳር ተቀምጦ አገኙት:: ወደ ሰፈራችን እንሂድ ቢሉት እንቢ ስላላቸው በሀይል አስገድደው ጉዞ እንደጀመሩ አንዴ ወደ ጥቁር፣ አንዴ ደግሞ ወደ ነጭ ኮርማ በሬ ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ቁጥቋጦና ቆንጆ ልጃገረድ በመሆን እራሱን ይለዋውጥ ጀመር። ከመንደራቸው ደርሰው ችዋይ ፊት ሲቀርብ ደግሞ ትክክለኛ ሰው ኡቼዶ ሆኖ ተሰጠ። ችዋይም ኡቼዶን ተቀብሎ ምግብ አዘዘለት:: ኡቼዶ ግን የቀረበለትን ምግብ አልበላም በማለቱ ቀለቡ ውሃ ሊሆን ይችላል በሚል ውሃ ቀረበለት:: እሱ ንም ውሃው የተሰጠኝ ሳይሐደን ነው በማለት አልጠጣም ስላለ እንደገና በተከደነ ዕቃ ሲቀርብለት ተቀብሎ ጠጣ። ያስተናገደው የነበረችው ኮሪ የምትባል የችዋይ ልጅ ነበረች። አብረዋት የነበሩ ሰዎች ወደ ጎጆሽ ውሰጂውና አብራችሁ እደሩ ስላሉዋት አብራው አደረች። በማግስቱ ጠዋት ኡቼዶ ኡቾክ የሚባል የአንገት ጨሌ በኮሪ አንገት አጥልቆላት ወደ መጣበት ወንዝ ተመልሶ ሄደ:: ኮሪም ከኡቼዶ ጸንሳ ስለነበር ወንድ ልጅ ወለደች።

ኡቹዶ ከወንዝ ሲመጣ ስሙ አይታወቅም ነበር። ኡቹዶ ብለው ስም ያወጡለት እንዋዎች ናቸው። ኮሪ የወለደችው ልጅም ኡኚያ እየተባለ ይጠራ ነበር። ኡኚያ ማለት አባቱ የማይታወቅ ልጅ ማለት ነው። ኡኚያ አድጎ ለአቅመ አዳም በደረሰ ጊዜ ኡቾክ ዘለ ጋት አጥልቀ ፖቦ (ባለ አንድ እግር በርጩማ) ላይ በመቀመጥ ኚያ ተብሎ ነገሰ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የአኝዋ ንጉስ ተብሎ የሚነግስ ኡቾክ በአንገቱ አጥልቆ ፖሎ ላይ እንዲቀመጥ ይደረግ ጀመር።

## ሚት 3

አቶ ሀኪም ኡፓራ በነገሩኝ ሌላ ተረክ ደግሞ ሁለቱ ልጃገረዶች የተጣሉበትን ጉዳይ ተመልክቶ ኡቹዶ የሰጠውን ትክክለኛ ፍርድ ህዝቡ ሲሰማ በጣም ተደስቶና ተገርሞ ነበር። ሕዝቡ በወቅቱ ይዳኝ የነበረው በችዋይ ነበር። የችዋይ ፍርድ አድሎአዊ ስለነበር በዘመኑ ትክክለኛ ፍትህ አልነበረም። ችዋይም ኡቹዶን ማግኘት ስለፈለገ ተይዞ እንዲመጣ አዘዘ። የታዘዙት ሰዎች ኡቹዶ ቷየ ወደ ተባለበት አካባቢ ሲደርሱ ከወንዝ ዳር ዳል ጆክ ከሚባል የግንድ ጉማጅ ላይ ተቀምጦ አገኙት። ችዋይ እንደሚፈልገው ነግረውት እንሂድ ቢሉት እንቢ ስላላቸው በሀይል አስገድደው ወደ ችዋይ ወሰዱት። ከችዋይ ዘንድ እንደቀረበ አሮጌ ቆዳ ተትጥፎለት ተቀመጥ ቢባል አዲስ ቆዳ ካልተነጠፈልኝ አልቀመጥም በማለቱ አዲስ ቆዳ ተነጥፎለት ተቀመጠ። ችዋይ በኡቹዶ መምጣት ተደስቶ አብሮት እንዲኖር ጠይቆት ነበር። ኡቹዶ ግን ከሚስቶቹ ጋር በወንዝ ውስጥ እንደሚኖር ገልጾለት ከችዋይ የቀረበለትን ጥያቄ መጀመሪያ እንቢ ቢልም የአካባቢው ሰዎች በተደጋጋሚ አጥብቀው ስለጠየቁት ሀሳባቸውን ተቀብሎ በመጀመሪያ ህግ ማውጣት እንደሚፈልግ ነግሮአቸው የሚከተሉትን ህጎች አወጣ። «የሰረቀ ንብረቱ ይወረሳል ፣ የሰው ሚስት ያማገጠ በጦር ይወጋል» የሚሉና ተመሳሳይ ህጎችን አወጣ።

ሕጎቹን ካወጣ በኋላ ችዋይ ከሚስቶቹ አንዷ ጋር እንዲያድር ጠይቆት ነበር። ኡቹዶ ግን «ከሰው ሚስት ጋር ወሲባዊ ግንኙነት መፈጸም ወንጀል ነው የሚል ህግ ስላወጣሁ ልጅህን ካልሆነ ሚስትህን አልፈልግም» አለ። ችዋይም ሀሳቡን ተቀብሎ ኮሪ የምትባል ልጁን አስጠርቶ አብራው እንድታድር አደረገ። በማግስቱ ጠዋት ኡቹዶ ከወንዝ ሲመጣ አጥልቆት የነበረውን ኡቾክ የሚባል ጨሌ ለኮሪ ትቶላት ወደ መጣበት ወንዝ ተመለሰ። ኮሪ ከኡቹዶ ጸንሳ ስለነበር ጊሉ የሚባል ወንድ ልጅ ወለደች። ጊሉ ጡት መጥባት እንዳቆመ ኮሪም ኡቹዶ ወደ አሚኖርበት ወንዝ ሄዳ ተሰወረች። ጊሉም ትዳር ይዞ ልጅ ከወለደ በኋላ ወዴት እንደተሰወረ አይታወቅም። ለመጀመሪያ ጊዜ የአኝዋ ንጉስ ሆኖ የተሾመው የጊሉ ልጅ ነው።

## ሚት 4

በጥንት ዘመን ችዋይ የሚባል ባላባት ነበር። በችዋይ የአስተዳደር ዘመን ፍትህ አልነበረም። አንድ ቀን ከወንዝ ውስጥ እንደመጣ የሚነገርለት ማንነቱ የማይታወቅ

እንግዳ ሰው ወደ ችዋይ ዘንድ መጥቶ አረፈ:: ችዋይም እንግዳውን ተቀበሎ ከሴት ልጁ ጋር አብረው እንዲያድሩ አደረገ:: ሰውየው በማግስቱ ጠዋት ተነስቶ በችዋይ ልጅ አንገት ላይ ጨሌ አጥልቆላት ወደ መጣበት ወንዝ ተመለሰ:: ከዚያን እለት ጀምሮ ሰውየው ዳግመኛ አልታየም:: ችዋይ ልጁ በአንገቷ ያጠለቀችውን ጨሌ ከየት እንዳመጣች ሲጠይቃት እንግዳው ሰውዬ እንደሰጣት ነገረችው:: ችዋይም በሰውየው ሁኔታ ተገርሞ ጨሌውን ኡቾክ አለው:: በአኝዋ ቋንቋ ቾክ ማታለል ! ኡቾክ ደግሞ ማታለያ ማለት ነው:: ችዋይ ጨሌውን ኡቾክ ያለው ሰውየው በጨሌ አታሎኝ ሄደ ለማለት ፈልጎ ነው:: ከእንግዳው ሰውዬ ጋር ያደረችው የችዋይ ልጅ ጸንሳ ስለነበር ኡቼዶ የሚባል ወንድ ልጅ ወለደች:: ኡቼዶ እንደተወለደ «ኡኚያ» እየተባለ ይጠራ ነበር:: ኡኚያ ማለት አባቱ የማይታወቅ ልጅ ማለት ነው:: የ«ጆናማ» ልጅ እየተባለም ይጠራል:: ጆናማ የወንዝ አማላክ ማለት ነው:: ኡቼዶ ለአቅመ አዳም እንደደረሰ በችዋይ አማካኝነት ኡቾክ በአንገቱ ተጠልቆለት የአኝዋ ኚያ ሆኖ ነገሰ:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ኚያ ተብለው የነገሱ የኡቼዶ ዝርያ ያላቸው ብቻ ናቸው::

አቶ ዶል አኳይ

ሚት 5

በጥንት ዘመን መኖሪያውን በኪሮ ወንዝ ውስጥ ያደረገ ኡቼዶ የሚባል ማንነቱ የማይታወቅ ሰው ነበር:: በወቅቱ የአኝዋ መሪ ችዋይ ይባላል:: አክዋ የምትባል የችዋይ ልጅ ወደ ኪሩ ወንዝ እየወረደች ውሃ ስትቀዳ ከኡቼዶ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያደረጉ ስለነበር በአንገቱ ኡቾክ የሚባል ጨሌ ያጠለቀ ወንድ ልጅ ወለደች:: ስሙንም ጊሎ አለችው:: ጊሎ ለአቅመ አዳም እንደደረሰ ችዋይ ህዝቡን ሰብስቦ የአኝዋ ንጉስ አርጎ ሾመው:: የሹመት ስነስርዓቱ ሲከናወን ጊሎ ምሉ የሚባል ባለ አንድ እግር በርጩማ ላይ እንዲቀመጥ ከተደረገ በኋላ ኡቾክ በአንገቱ ተጠለቀለት:: ችዋይ ጊሎን ንጉስ አርጎ የሾመው ስልጣኑን አስረክቦት ወደ እግዚአብሔር መሄድ ስለፈለገ ነው:: በዱሮ ጊዜ እግዚአብሔር ከሰው ጋር አብሮ ይኖር ነበር:: እግዚአብሔር ከሰው ተለይቶ ሲሄድ በምድር ላይ ያለውን ስልጣን ያስረከበው ለችዋይ ነበር:: ችዋይ በበኩሉ ከሰዎች ተመርጦ የተሰጠውን ስልጣን ለጊሎ አስረክቦ ወደ እግዚአብሔር ሄደ:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የነገሱ የአኝዋ ኚያዎች የጊሎ ዝርያ ያላቸው ናቸው::

አቶ አዱላ አመድ

## አባሪ ሁለት —ትንተና የተደረገባቸው ተረቶች

### ተረት 1

ዝንጀሮና ዓይጥ አብረው በወዳጅነት እርሻ እያረሱ ሲኖሩ አንድ ቀን አይጥ “የረሃብ ጊዜ ሲመጣ እንዳለፈው ዘመን እንዳይቸግረን ዛሬ በደህናው ቀን እህል በጎተራ አስገብተን እናስቀምጥ»ስትል ለዝንጀሮ ሃሳብ አቀረበች:: ዝንጀሮም በሀሳቧ የተስማማ መሆኑን እንዳወቀች “ታዲያ ጐተራው ከማን ጋር ይቀመጥ ” በማለት ጠየቀችው:: በዚህ ጊዜ ዝንጀሮ “ ከእኔ ጋር ይቀመጥ ” ለማለት ከበደውና በጣም ተጨነቀ :: ከዚህም “ ጐተራው ከአንቺ ጋር ቢቀመጥ ምን ችግር ይኖራል ? በእኔ በኩል ካንቺ ጋር ቢቀመጥ ደስ ይለኛል ” አላት:: «እሷም ጥሩ! ሊቀመጥ ይችላል» ካለች በኋላ እንደገና «የጎተራውን ቁልፍ ማን ይያዝ?» በማለት ሌላ ጥያቄ አቀረበችለት:: ዝንጀሮም “ ቁልፉንም አንቺ ልትይዥው ትችያለሽ እኔና አንቺ እንተማመናለን :: ስለዚህ ቁልፉ ካንቺ ተቀመጠ ከኔ ምን ለውጥ አለው?” አላት:: በዚህ ጊዜ አይጥ ኮስተር አለች :: ወዲያውም “ አይሆንም ቁልፍ ካንች እጅ መቀመጥ ይኖርበታል ::ምክንያቱም ጎተራው እኔ ጋር እንዲሆን ከተስማማን ቁልፍ ከእኔ እጅ እንዲሆን ደግሞ መስማማት የለብንም :: ስለዚህ ቁልፍ ካንተ እጅ መቀመጥይ ኖርበታል!” አለችው:: ዝንጀሮም “እሺ! እኔ እይዘዋለሁ ካለ በኋላ በስምምነታቸው መሰረት ጎተራውን ከአይጥ ጋር አስቀመጡት:: ለአንድ ዓመት ቀለብ የሚሆናቸውን ያህል በቆሎ በጎተራው ሞልተው ቆለፉና ቁልፉን ዝንጀሮ ይዞ ሄደ :: አይጥና ዝንጀሮ ለክፉ ቀን እንዲሆናቸው እህል በጎተራ አስቀምጠው ሲኖሩ ዓመታት አለፉ::በኋላ በኋላ ግን በአገሩ ረሀብ መጣ :: በየቤቱም የሚላስ የሚቀመስ እህል ጠፋ:: በዚህ ጊዜ አቶ ዝንጀሮ ቁልፉን ይዞ ወደ ወዳጁ አይጢት ቤት ሄደ:: ከአይጢት ጋርም ሰላምታ ከተለዋወጠ በኋላ “ እንደምታይው ሀገሩ ረሀብ ወርዷል:: የሚላስ የሚቀመስ ነገርም ጠፍቷል:: አንችም እግዚአብሄር ይባርክሽ:: ምክንያቱም ከብዙ ዓመታት በፊት የተቀደሰ ሃሳብ አፍልቀሽ ቤት በሚያክል ጎተራ እንዲህ ላለ ክፉ ቀን መውጫ የሚሆን በቆሎ ለማስቀመጥ ቻልን:: ረሀብ ከፋ ቀየ:: ግን ከመቸኮል ትንሽ ልቆይ ብዬ ድርሻዬን ልውሰድ አላልኩሽም:: አሁን አንችንም እንዳይቸግርሽ እኔም ልጆቼ እያለቀሱ እንዳልቸገር በሚል ነው የመጣሁ ” አለና ቁልፉን በእጁ ይዞ በማሳየት «ልጆቼ በረሃብ ሳይሞቱብኝ ያስቀመጥነውን እህል እንከፋፈል አላት»:: አይጢትም በጥሞና ስታዳምጥ ቆየችና “ የዝንጀሮው ረሀብ ረሀብ ነው? ወይም ምንም ረሀብ ሊባል አይችልም:: የሚበላ ነገር እኮ አልጠፋም:: ቀው አቶ ዝንጀሮ እህሉን ቆጥበን ብናቆየው የሚቀጥለው ዓመት ምን ሊሆን እንደሚችል ስለማናውቅ ቀን ልንወጣበት እንችላለን” አለችው :: ዝንጀሮም

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በአነጋገሯ በጣም ተጨነቀ። የገጠመውን ችግርም እየደጋገመ ነገራት። አይጥ ግን መቸኮል እያስፈለገም በማለቷ ዝንጀሮ ተመልሶ ወደ ቤቱ ሄደ። ከቤቱ የሚበላ ነገር አልነበረውም። እንደደረሰም ልጆቹ እርቧቸው ስለነበር ምግብ አምጣ እያሉ ተሰብስበው አስቀሰቡት። ስለዚህ እንደ ገና በልጆቹ ሁኔታ በጣም ተጨነቀ። ቢያታልላቸውም ማልቀሳቸውንና ምግብ አምጣ እያሉ መጨቅጨቃቸውን ሊተው አልቻሉም። አቶ ዝንጀሮ በጣም ግራ ተጋብቶ ጥቂት ቀን ከቆየ በኋላ "አሁንስ የፈለገው ይሁን እንጂ ድርሻዬን ተካፍዬ አምጥቼ ልጆቼ በረሀብ ሳያልቁ ማብላት አለብኝ" ብሎ ወደ አይጥጢት ቤት ለመሄድ ወሰነና ተመልሶ ሄደ። ከዚያም " ወዳጄ አይጢት በቆሎውን ብንካፈል ይሻላል። ልጆቼ ዓይኔ እያየ በረሃብ ሊያልቁብኝ ነው። እና ዛሬ መካፈል ይኖርብናል" በማለት አጥብቆ ለመናት። አይጢት ግን "ተው አቶ ዝንጀሮ የዘንድሮ ረሀብ ረሀብ አይባልም" ለከርሞ ይቀመጥ ፋንታህን የሚወስድብህ የለም ቁልፉም በእጅህ ነው የሚገኘ። እሽ ብትልና ምክሬን ብትቀበለኝ አሁን ምን አለበት? አቶ ዝንጀሮ እስቲ አንድ ነገር ልንገርህ ። 'ልጆቼ እያለቀሱ ፣ በረሀብ ሊሞቱ ነው' ትላለህ። ልጅ እኮ እየበላ የሚያለቅስ ፍጥረት ነው። እኔ እንደሚመስለኝ ከርሞ የባሰ የረሃብ ዘመን ሊሆን ይችላል። የሚታወቅ ነገር የለም። እና ያን ጊዜ ምን ትሆናለህ?እ! ልጆችህን ምን ታበላለህ? ስለዚህ ለመጭው ዘመን አርቀህ ማሰብ አለብህ እንጂ መቸኮል አይኖርብህም" አለቸው። በዚህ ግዜ አቶ ዝንጀሮ በጣም ተጨነቀና "ለከርሞ ማስቀመጥ የሚቻለው ዛሬ የሚበላ ሲገኝ ነው ። ልጆቼ በቁም እያለቁ ነው እያልኩ እየነገርኩሽ ለምን አይገባሽም? ዛሬ ከሞትኩ ነገ እንዴት እኖራለሁ? ስለዚህ ድርሻዬን ወስጄ ዛሬ መብላት አለብኝ" አለና አምርሮ ለአይጢት ነገራት። እሷ ግን ጭንቀቱንና ችግሩን ተረድታ እሽ ልትለው አልቻለችም። ስለዚህ አቶ ዝንጀሮ በጣም እያዘነና እየተበሳጨ አሁንም ወደ ቤቱ መመለስ ግድ ሆነበት። ሆኖም ከቤቱ ሲደርስ እንደተለመደው ልጆቹ በረሃብ እየተንጫጩ አገኛቸው። ልጆቹ ከቤት በወጣ ቁጥር እንደ ቀድሞው የሚበላ ነገር ይዞ የሚመለስ ይመስላቸው ነበር። ስለዚህ እሱን ባዩ ጊዜ ጨርሶ ረሃብ ይገርፋቸውና አባባ! አባባ! ምግብ! ምግብ! ስጠን እያሉ ሆዳቸውን በጥፍራቸው እየጫሩ ማልቀሳቸውን ይቀጥላሉ።ዝንጀሮም በዚህ ጊዜ እንጉሉ ዞር በጣም እየተጨነቀ ሳለ ልጆቹ እያለቀሱ ይጨቀጭቁታል ። በዚህ ሁኔታ ቀኑን ሊያሳልፈው አልቻለም ። ስለዚህ እንደ ገና ወደ አይጢት ቤት ገስግሶ እንደደረሰ "ዛሬ በፍጹም ድርሻዬን ይዤ መሄድ አለብኝ በማለት አይጢትን በቁጣ ጠየቃት። እሷም "እምቢ አይሆንም የጋራ ጎተራችን መከፈት የለበትም" በማለት በጣም ተቆጣች። ዝንጀሮ ግን "በፍፁም

ድርሻዬን ካልያዝኩ ዛሬ ተመልሼ አልሄድም" አለና እንቢ አላት። በዚህ ጊዜ አይጢት ደግሟ ፈላና "ምን ትጨቀጭቀኛለህ! ቁልፍ የሚገኝ በእጅህ ሄድና ክፈተዋ" አለችው ። ዝንጀሮም ጎተራውን ከፈተና አንገቱን አስግጉ ሊመለከት በጎተራው ውስጥ አንድ ፍሬ በቆሎ እንኳን ለምልክት የለም ።በዚህ ጊዜ አቶ ዝንጀሮ በድንጋጤ ተውጦ አ!አ!አ! በማለት ጮኸና አይጢትን"በቆሎውን የት አደረስሽው?"አላት። አይጢትም ከት ብላ በመሳቅ "ቁልፍ ያለው ካንተ እጅ! እንዴት የት አደረስሽው ብለህ እኔን ትጠይቀኛለህ" አለችና በቁጣ "አሬ ይልቅ አንተ የት አደረስከው? መጠየቅ ያለበት እኔ ነኝ ወይስ አንተ ነህ? እኪኪኪኪ" አለችና እሷም ወደ ጎተራው ሄዳ ተመለከተች ። "አይጢት እንዴት እንደዚህ ትናገሪያለሽ? እኔ ካለ ዛሬ ይህን ጎተራ ከፍቼ አይቸው አውቃለሁ?" በማለት አቶ ዝንጀሮ እንደ ገና ኡኡታውን አቀለጠው። አይጢትም "ቁልፉን በእጅህ ይዘህ በልተህ ስታበቃ በላችው እያልክ ስሜን ልታጠፋ ነዋ" በማለት ደነፋችበት ። ከዚህ በኋላ ለክፉ ቀን ይሆናል ብለን በጋራ ያስቀመጥነውን አንድ ጎተራ ሙሉ በቆሎ ዝንጀሮ ከዶኝ በላው በማለት ለእንስሳት ጆዶንን (ለእንስሳት ሽማግሌዎች) እያለቀሰች አመለከተችና ዝንጀሮን በክህደት ከሰሰችው። የእንስሳት ጆዶንንም አይጢት ያቀረበችውን ክስ ፍሬ ነገር አዳምጦ ምርመራውን ቀጠለ። ፍርድ ለመስጠት ግን በጣም ተቸገረ ። ጆደንንው ፍርድ ለመስጠት የተቸገረበት ምክንያት ምንም እንኳን ቁልፍ በአቶ ዝንጀሮ እጅ ቢሆንም አይጥም ውስጥ ለውስጥ ጉድጓድ ጭራ ከጎተራው ውስጥ በመግባት በቆሎውን ልትበላ አትችልም ማለት አይቻለም በማለት ነበር። በመጨረሻም ጆዶንጉው ጥፋተኛውን ለመለየት መቸገሩን ለዝንጀሮና ለአይጥ ገለጠላቸው። በዚህ ጊዜ አይጥ በፍጥነት "ጆደንን በዚህ ምክንያት ጥፋተኛውን ለመለየት ለጊዜው ከተቸገረ ሁለታችንም ከጎተራው እንግባና እሳት ይንደድብን።ከሁለታችን በህይወት የተረፈ ንጹህ ነው ተብሉ ስሙ ይጠበቅለት" በሚል ሀሳብ አቀረበች። ዝንጀሮም "ጥሩ ሀሳብ ነው እስማማበታለሁ"አለ። ከዚህ በኋላ ጆደንንው ተመካክሮ አይጢትንና ዝንጀሮን ከጎተራው ውስጥ አስገባና የጎተራውን የሳር ክዳን በእሳት አያይዘው ። ሆኖም እሳቱ እንደተያያዘ ኃይለኛ ዝናብ በረዶ ቀላቅሉ መውረድ ጀመረ ። አይጢትም ወዲያው እሳቱ እንደተያያዘ በጎተራው ስር ቆፍራ በቆሎውን በበላችበት ጉድጓድ ሾልካ ገባች ። አይጥ ወደ ጉድጓድ እንደገባች ዝናቡ እሳቱን ባንድ ጊዜ አጠፋው። ዝንጀሮም በዝናብሀይል እሳት ሳያገኘው ቀረ። አይጢትን ግን በጉድጓዷ የገባ ጎርፍ አጥለቅልቆ ገደላት።

## ተረት 2

ከእለታት አንድ ቀን አንበሳ ከርከሮን ሊበላ ሲያሳድደው እየረጠ ሄዶ ጃርት ከምትኖርበት ጉድጓድ ይገባና ጃርትን "እባክሽ አድኚኝ፣ አንበሳ ሊበላኝ እያሳደደኝ ነው" ይላታል ። ጃርትም ሁኔታውን ለማጣራት ከጉድጓድ ብቅ ስትል አንበሳን በንዴት ቆሞ ስታየው መርዛማ እሾሆቿን ረጭታበት ትገድለውና ወደ ከርከሮ ተመልሳ "አይዞህ ተረጋጋ ጠላትህን ገድየዋለሁ። አንተ ግን ለኔ ውለታ ልትከፍለኝ ይገባል" አለችው ። ከርከሮ ግን "እኔ ምስኪን ደሀ ስለሆንኩ ውለታሽን መክፈል አልቻልም"ሲል መለሰላት። ጃርትም በከርከሮ ሁኔታ ተናዳ ከጉድጓዷ ታባርረዋለች።

በከርከሮ ውለታ ቢስነት የተናደደችው ጃርት ልትበቀለው ፈልጋ ፈጥና ወደ ጅብ በመሄድ ላይ ሳለች ከመንገድ አግኝታው "እያ ጅቦ ለምን ከርከሮን ገለህ አትበላም? ከርከሮ እኮ ደካማና አቅመ ቢስ ነው" በማለት እንዴት ከአንበሳ መንጋጋ እንዳተረፈችው ገለጸችለት። ጅብም እርቦት የሚበላ ይፈልግ ስለነበር "ታዲያ አሁን የት አገኘዋለሁ" ሲል ጃርትን ጠየቃት።"ወደማታ ውሃ ሊጠጣ ወንዝ ይመጣል። አንተ ከወንዙ ዳር አድፍጠህ ጠብቀው" ስትለው ወደ ማታ አካባቢ ወደ ወንዝ ሄዶ በማድፈጥ ከርከሮን ዘሎ ያንቀዋል። ከርከሮም ከጅብ መንጋጋ ለማምለጥ እየተፈራገጠ " ምነው ወንድሜ ጅብ ምን አጠፋሁ " እያለ እንዳይገለው እጥብቆ ተማጸነ። "አንተ ከሀዲ ነህ፣ ጃርት ከሞት አትርፋህ ውለታዋን አልከፍልም በማለትህ ልትቀጣ ይገባል" አለው ። ከርከሮም ጅብ እንዳይገለው በጣም ፈርቶ ስለነበር የተጠየቀውን እንደሚከፍል ቃል ገብቶለት «እባክህ የዛሬን ይቅርታ አድርገልኝ» እያለ በድጋሚ አጥብቆ ለመነው ። "ዉለታዋን የምትከፍል ከሆነ ይህንኑ ለጃርት ማሳወቅ አለብህ" ብሎ ተያያዘው ወደ ጃርት ሄዱ ። ጃርት፣ ጅብና፣ ከርከሮ ስለተፈጠረው ሁኔታ ሲወያዩ መግባባት ባለመቻላቸው ጉዳዩ በዱር እንስሳት ሸምጋይነት እንዲታይ ተስማሙ። የዱር እንስሳት ዳኞችም ጉዳዩን በጥንቃቄ ከመረመሩ በኋላ "ጃርት ከርከሮን ከሞት ስላተረፈችው ውለታዋን ልትከፍል ይገባል"ሲል ፈረደ። ጅብን ደግሞ "ከርከሮ ጥፋተኛ ስለሆነ ይዘህ ወደ እኛ እንዲመጣ ማድረግህ ትክክል ቢሆንም ጉዳት ልታደርስበት ግን አይገባም"

በማለት ካስማሙዋቸው በኋላ ጅብ እርቦት ስለነበር ጃርት የገደላቸውን አንበሳ እንዲበላ ተወስነለት ይባላል ።

አቶ አኩዌር ኡጁሉ

ተረት 3

ከዕለታት አንድ ቀን አንዲት ዶሮ ተኝታ ከነበረች ውሻ ቂጥ ላይ የነበረች መዥገር ለመብላት ስትመነቁሪት ውሻዋ ደንብራ ስትሮጥ መንገድ ላይ ሳር ትግጥ የነበረች ጥጃ በዘኩሉዋ ድንገት በውሻው ሩጫ ደንብራ ስትሮጥ አንድ ተኝቶ የነበረ ህፃን ልጅ እረግጣ በመግደሏ የህፃኑ አባት ካሳ እንዲከፈለው በአገር ሽማግሌዎች በኩል ይጠይቃል። የአገር ሽማግሌዎችም ጉዳዩን ከመረመሩ በኋላ ዶሮዋ ውሻውን ባትመነቁር ኖሮ ውሻዋ ደንብራ አትሮጥም ነበር ። ጥጃዋ ደንብራ ባትሮጥ ኖሮ ደግሞ ህፃኑ አይሞትም ነበር በማለት የዶሮው ባለቤት ለሞተው ህፃን ወላጆች ካሳ እንዲከፍል ተወስነበት ይባላል ።

አቶ አኛይ ኡዶሉ

ተረት 4

ከዕለታት አንድ ቀን ሁለት ሰዎች አደን ላይ ሳሉ በጦር የወጉት ዝሆን አምልጦአቸው ከሸሸ በኋላ ራቅ ወደ አለ ቦታ ሄዶ ይሞታል ። የሞተውን ዝሆን ሌሎች አዳኞች አገኙተውት ስጋውን ሲከፋፈሉ ቀድመው በጦር የወጉት አዳኞች ይደርሱና ዝሆኑ ለእኛ ይገባል በሚል ጭቅጭቅ ይፈጠራል። ጭቅጭቁ እየከረረ በመሄዱ ጉዳያችን በአገር ሽማግሌዎች መታየት አለበት በሚል ተስማምተው ወደ አገር ሽማግሌዎች ይሄዳሉ።የአገር ሽማግሌቹም ጉዳዩን ከመረመሩ በኋላ "በእኛ የአደን ደንብ መሰረት የታደነው አውሬ የሚሰጠው ቀድሞ በጦር ለወጋ ሳይሆን መጀመሪያ አውሬውን ወድቆ ወይም ሞቶ ላገኘ ነው መስጠት ያለበት ስለዚህ ቀድመን በጦር የወጋን እኛ ነን የምትሉ ወገኖች ዝሆኑን ተከታትላችሁ መያዝ ነበረባችሁ" በማለት ዝሆኑ ቀድመው ላገኙት አዳኞች ሊሰጥ ይገባል ሲሉ ፈረዱላቸው ይባላል ።

አቶ አጉዋ ኝጉዎ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

## ተረት 5

በጥንት ጊዜ ኦማል የሚባል አንድ ሰው ነበር። ኦማል አስራ ሁለት ልጆችና አምስት ሚስቶች ነበሩት ። ብዙ ፍየሎችና በጐችንም ያረባ ነበር ። ኦማል አንድ መንጋ ፍየልና በግ ያለው መሆኑን ጅብ በማወቁ ለቤተሰቡ ፣ ለልጆቹና ለሚስቱ የሚበቃውን ያህል በየቀኑ ስስትና አራት ፍየሎችንና በጐችን እየወሰደ ሲበላ ከኖረ በኋላ ሁሉንም በጊዜ ብዛት ጨረሳቸው። በዚህ እየተናደደ ሳለ ልጆቹን ተራ በተራ ይበላበት ጀመር። የቀረፋትን ልጆቹን ጅቡ እንዳይበላበት ከቤት እንዳይወጡ፣ ወደ እርሻ፣ እንጨት ሰበራ እንዳይሄዱ፣ ውሃ ለመቅዳት ወንዝ እንዳይወርዱ ቢያደርግም በየት በኩል ገብቶ አንቆ ይዟቸው እንደሚሄድ ማወቅ ባለመቻሉ በጣም ግራ ተጋባ። እንዲህ እያደረገ አቶ ጅብ አሥራ ሁለት ልጆቹን ከጨረሰበት በኋላ አንዷቱን ሚስቱን ደግሞ በሌሊት ተሸክሞበት ሄደ። ቀጥሉም ሁለተኛዋን በላበት። ሶስተኛዋን ሚስቱን ደግሞ አራት በልታ ልትተኛ ኦማል ወደሚገኝበት ቤት ማታ ስትሄድ "እሙኝ፣እሙኝ" እለና ጮሆ እያስለፈለፈ ተሸክሞ ወሰዳት። አራተኛይቱንና የመጨረሻዋን ሚስት ደግሞ ቀን ውሃ ቀድታ ወደ ቤቷ ስትመለስ ከጪሻ ውስጥ ተደብቆ በድንገት ዘንታትሮ ጣላትና ተሸክሞ እያስለፈለፈ ወሰዳት። ኦማል በዚህ ጊዜ "እንግዲህ የቀረሁት እኔ ብቻ ነኝ ፣ እኔንም ሳይበላኝ ይሄ ጅብ እርፎ አይቀመጥም ። የሚያገኘኝም ከዚህ ከቤቴ አካባቢ ነው። ስለዚህ ቤቴን ለቅቄ ጫካ መኖር አለብኝ » እለና ጦሩን ይዞ ወደ ጫካ ለመግባት ወሰነ። ኦማል በወሰነው መሠረት ሲሄድ፣ሲሄድ ውሎ ጥቅጥቅ ካለ ጫካ እንደደረሰ ደከመውና ጋደም አለ። በዚህ ጊዜ አቶ ጅብ እያሸተተ ከች በማለት ኦማልን ተኝቶ አገኘው። በዚህ ጊዜ "እንቅልፍ ይዞት ይሆን?» እለና በልቡ ተኝቶ የተኛውን ኦማል አስተዋለው። ኦማል አይንቀሳቀስም። እስትንፋስም ያለው አይመስልም። ጦሩን ግን በእጁ እንደያዘ ነው። በሁኔታው አቶ ጅብ ግራ ተጋባና ዙሪያውን እምቡላሌ ይዞር ጀመር። ምን አልባት እንቅልፍ ይዞት ከሆነ ኦማል ይንቃል በሚል ጪሻውን እያንኳኳና እያደባ ትኩር ብሎ አየው ። አሁንም ኦማል አልተንቀሳቀሰም። አቶ ጅብ እንደ ገና ድንጋዩን በእግሩ ገልበጥበጥ እያደረገ አንኳኳው። አሁንም ኦማል አልተንቀሳቀሰም። እንደገናም በፊት ለፊት በኩል ሄደና በልቡ ተኝቶ ቀና እያለ ተመለከተው ። አሁንም ምንም ንቅንቅ አላለም ። በዚህ ጊዜ አቶ ጅብ " ይህ ሰው አይሰማም፣ አይለማም፣ ከቶ እንስ ሞቷል ልበል?" እለና እንደ ገና ዙሪያውን እያማተረና እየዞረ ማንኰሽኰሹን ቀጠለ ። ከዚያም ወደ ኦማል ትንሽ ቀረብ በማለት በልቡ ተኝቶ ሲያጢቃ ወዲያው ፈጥኖ ብድግ አለ። "እንቅልፍ አይደለም። በቃ! በቃ ሞቷል። በእጁ ከርር አድርጉ ጦሩን መያዙ የመሞቱ ሌላው ምልክት ነው! እለና ይበልጥ ለማረጋገጥ

ኪ-ኪ-ኪ-ኪ እለና በፍርሃት ፊት ብሉ ኦማልን አስተዋለው:: ከዚያም “እኔ ጅቦ ! የሞተ ጠፍቶኝ ነው» እለና ኦማልን ቀረብ ብሎ እያሸተተ አተኩሮ ተመለከተው :: ኦማል ግን አሁንም አልተንቀሳቀሰም::ያው እንደተኛ ነው:: በዚህ ጊዜ አቶ ጅብ «በቃ! ሞቷል» አለና በፊት እግሩ ነካ አድርጎ እንደገና በድንጋጤ ፊት ብሎ ዞረና አየዉ :: አሁንም ኦማል እንደተኛ ነው:: ወዲያው አቶ ጅብ ተመልሶ ሄደና ኦማልን በፊት እግሩ ገልበጥ አደረገው:: ኦማል ጡሩን እንደያዘ በአንድ ጎኑ ተገልብጦ አየው:: “እንዴት ይከብዳል? ሰብቶ የለም እንዴ? ተሸክሜው ልሄድና ከቤቴ ወስጄ ከልጆቼ ጋር ልብላው” አለና ኦማልን ሰቅስቆ በትክሻው ተሸክሞት ወደ ቤቱ መሄድ ጀመረ:: ተሸክሞት በመሄድ ላይ እንዳለ ኦማል ሽንቱን ሸናበት :: በዚህ ጊዜ አቶ ጅብ “ስቡ አግድም ፈሰሰ ፤ አይ!” አለና የተንጠባጠበውን ሽንት ላስ ላስ ላስ አድርጎ ሲጓዝ ወፍ ከዛፍ ቁጥሎ ወጥታ

«ኩኩ - ቁቁ፣ ኩኩ - ቁቁ

ኦማል አለ በህይዉቱ::

ኦማል ሞተ ብለህ

አያ ጅቦ ትሞኛለህ” አለችው::

እንዲህ ብላ ስትናገር አቶ ጅብ ተናደደና “የሞተና ያልሞተ እንኳን የማታውቅ ደደብ፣ ቴል ፤ በዚህ ሰው እየቀሰጠ እየተንጠባጠበ “ ትሞኛለህ ትላለች” አለና መንገዱን ቀጠለ:: አሁንም እንደገና ወፊቱ እየበረረች መጣችና ከዛፍ ላይ ቁጭ ብላ

“ኩኩ -ቁቁ፣

ኩኩ - ቁቁ፣

ዛሬ ጅቦ እንጃለቱ” በማለት ደግማ ተናገረች::

ኦማል አለ በሕይወቱ፣

አቶ ጅብም በወፏ አነጋገር ይበልጥ ተናደደና «አንች ሞጥሟጣ በማን ነው የምታሾፊው? ደደብ! የሞተና ያልሞተ እንኳን የማታውቂ» በማለት ኦማልን ይዞ ወደ ፊት ገሠገሠ :: አቶ ጅቦ ከቤቱ ደርሶ ኦማልን ወለል ላይ ሲዘረጋው ልጆቹ ሁሉ በደስታ ተቐጡ :: እሙኝ በማለትም ተናጩ :: እስቲበሉ ድረስም በጣም ቸኮሉ:: ሚስቱም ልጆቿ በደስታ ሲናጩ በመስማት ከጓዳ ወጥታ መጣችና ተመለከተች:: ኦማል በዚህ ጊዜ የጅብ ቤተሰቦች በሙሉ መሰባሰባቸውን ተረዳ:: ከዚያም ፈጥኖ ከወደቀበት በመነሳት ተራ በተራ በጦር ጀቦቹን ገድሎ ብድሩን በመመለስ ወደ ቤቱ መጣ ይባላል::

ምንጭ:- በይለየኝ ጣሰው ፤ የአኝዋ ተረቶች

ተረት 6

ከእለታት አንድ ቀን ቀጭኔና ጥንቸል ከአንድ ዙሪያውን ከታጠረ የገበሬ እርሻ የበሰለ ፍራፍሬ አይተው ሊበሉ ገቡ። ፍራፍሬውን እየበሉ ሳለ ጥንቸል ድንገት የእርሻው ባለቤት ደርሶ አደጋ ያደርስብናል በሚል ስለተጠራጠረች ለቀጭኔ ሳትነግራት ለራሷ ማምለጫ እንዲሆናት ወደ አጥሩ አንድ ጥግ ሄዳ መሽሎኪያዋን አዘጋጅችና ወደ ቀጭኔ ተመልሳ የበሰለ የበሰለውን ፍራፍሬ ይበሉ ጀመር። ጥንቸል በልታ እንደጠገበች «የበሰለ ጣፋጭ ፍራፍሬ ከበላሁ በኋላ የመዝፈን አመል አለብኝ። ስለዚህ ልዘፍን ነው» ስትል ለቀጭኔ ትነግራታለች። ቀጭኔ ግን የጥንቸልን ሀሳብ በመቃወም በጣም ትናደድና «ቢያንስ እኔ በልቼ እስክጠግብ ድምጽ ማሰማት የለብሽም» አለቻት። ጥንቸል በበኩሏ የግድ መዝፈን እንዳለባት በድጋሚ ነግራት ድምጿዋን ከፍ አድርጋ ከዘፈነች በኋላ ባዘጋጀችው መሽሎኪያ ቀዳዳ ወጥታ በሩጫ ከአካባቢው ትጠፋለች። የጥንቸልን ድምጽ ሰምቶ የእርሻው ባለቤት ሲመጣ ቀጭኔ መውጫ አጥታ ያገኛትና ክፉኛ ገርፎ ያባርራታል ። በሁኔታው ቀጭኔ ቂም ይዛ ስለነበር አንድ ቀን ከወንዝ ዳር ጥንቸልን ታገኛትና ወንዙን አብረን አቋርጠን እንሻገር ብላት በማቋረጥ ላይ ሳሉ ከወንዝ ዳፍቃ ገደለቻት ይባላል።

አቶ አኛይ ኡደል

ተረት 7

ከእለታት አንድ ቀን ዝሆን ውሃ ሊጠጣ ከአንድ ኩሬ እንደደረሰ እንቁራሪትን ያገኛትና በንቀት አይን እየተመለከታት ከአጠገቧ ይቆማል። እንቁራሪትም በዝሆን ሁኔታ በጣም ትናደድና “እባክህ ግዙፍነትህን ተመክተህ እንዲህ አትኩራ” ትለዋለች። ዝሆንም በእንቁራሪት የንቀት አነጋገር ተገርሞ እየሳቀባት እንደገና በንቀት ቁልቁል ይመለከታት ጀመር። በዚህ ጊዜ እንቁራሪት ይበልጥ ትናደድና“ ግዙፍነትህን ተማምነህ ከሆን ይህ የኩሬ ውሃ እስኪያልቅ ሁለታችንም በመጠጣት እንወራረድ። ውሃው ሳያልቅ ቀድሞ የደከመ ተሸናፊ ይሆናል በማለት ነው” ትለዋለች። ዝሆንም “ያለ አቅምሽ አትንጠራራ ከፈለግሽ መወዳደር እንችላለን” ይላትና ውድድሩ ይጀመራል። ውድድሩ እንደተጀመረ እንቁራሪት ውሃውን እየሳበች የምትጣጣ በማስመሰል መልሳ ትተፋው ነበር። ዝሆን ግን ውድድሩ ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ አንዴም ቀና ሳይል ውሃውን ሲጠጣ፣ ሲጠጣ ሆዱ ይነፋና ፈንድቶ ይሞታል። በዚህ ሁኔታ ብልጧ እንቁራሪት ዝሆንን በዘዴ ተበቀለችው ይባላል።

አቶ አኩዌር ጉይ

ተረት 8

በጥንት ዘመን አንድ በጣም ሆዳምና ህብረተሰቡን ያስቸገረ ሰው ነበር፡፡ ይህ ሰው ከእለታት አንድ ቀን በአትራቢያው ካለ መንደር ሄዶ ከማያውቀው ሰው ቤት ለአዳር ያርፋል፡፡ የቤቱ ባለቤትም እንግዳውን ተቀብሎ በማስተናገድ እራት በልተው ይተኛሉ፡፡ እንግዳው ሰውዬ ግን ለሊት ላይ ተነስቶ ከቤት ያለውን ምግብ ሁሉ ጠራርጎ ከበላ በኋላ አልጠግብ ስለአለ የአሳ ቋንጣ እያወረደ መጥበስ ይጀምራል ፡፡ በዚህ ጊዜ አባውራው ከእንቅልፉ ይነቃና"ምን እየስራህ ነው ጃል!" ይለዋል፡፡ እንግዳው ስውዬም «እርቦኝ የሚበላ እየፈለኩ ነው» ይለዋል፡፡ አባውራውም በእንግዳው ስውዬ ድርጊት በመገረም "እራትህን እስክትጠግብ ከእኛ ጋር በልተህ የለም እንዴ? ያለ እኛ ፈቃድ ተነስተህ የምትንጎዳጎደው ለምንድን ነው?" ሲለው « እናንተን ከመቀስቀስ ብዬ ነው» ይለዋል፡፡ አባውራው በንዴት ተነስቶ ቤቱን ሲቃኝ አንድም የተረፈ ምግብ የለም፡፡ ተዘልዝሎ የተሰቀለውን ቋንጣም ሆዳሙ ሰውዬ ጨርሶታል ፡፡ የሰውዬው ሁኔታ በጣም ስላናደደው ከቤቱ ያባርረዋል፡፡ በነጋታውም ስለሰውዬው ሁኔታ ለመንደርተኛው በማሳወቅ እንዳያስጠጉት ይነግራቸዋል፡፡ ወሬውን የሰሙ ሰዎች ሁሉ ሰውዬውን በማግለል እናስጠጋህም ስላሉት በአትራቢያው ካለ ሌላ መንደር ይሄድና እንደለመደው ከአንድ ከማያውቀው ሰው ዘንድ ያርፋል ፡፡ በእለቱ የቤቱ ባላቤቶች እንግዳውን ሰው ተቀብለው ያስተናግዱና አብረው ምግብ ከበሉ በኋላ ከቤት ትተውት ወደ ወንዝ ይሄዳሉ፡፡ ሆዳሙ ሰውዬም እንደለመደው ባለቤቶቹ በሌሉበት የአሳ ቋንጣቸውን በልቶ ከጨረሰ በኋላ አልጠግብ ስላለ አንድ ፍየል አግኝቶ አርዶ ሲበላ ባለቤቶቹ ደርሰው "ለምን ፍየላችንን አርደህ ትበላለህ" ይሉታል፡፡ እንግዳው ሰውዬም "እርቦኝ ነው" ሲላቸው "አሁን እስክትጠግብ አብልተንህ እንዴት ይርብሃልህ" በማለት ተናደው ሰውዬውን ያባርሩታል፡፡ ለአካባቢው ሰዎችም ስለሰውዬው ባህሪይ ነግረው እኝዋዎች ሁሉ እንዲያገሉትና እንዳያስጠጉት ተደረገ ይባላል ፡፡

አቶ አኛይ ኡዶል

ተረት 9

በድሮ ጊዜ አንድ ቀናተኛ ባል የነበራት ሴት ነበረች፡፡ በባሏ ጭቅጭቅና ቅናት የተማረረች ሚስት ሌላ ውሽማ ትይዝና ቀን ቀን እየመጣህ ጎብኘኝ ትለዋለች፡፡ውሽማ ግን ባልየውን ፈርቶ በ"ቀን አልመጣም"ሲላት"ማታ ማታ እንድትመጣ" ትለዋለች፡፡ አሁንም ውሽማ "ባልሽ ቀናተኛ ስለሆነ ይገለኛል አልመጣም"ይላታል፡፡ ሲትየዋም

ውሽማዋን አግባብታ ካሳመነች በኋላ አንድ ቀን ማታ ከጓሮ ሆኖ እንዲጠብቃት ቀጠረችው። በቀጠሮው መሰረት ውሽማ ከጓሮ ተደብቆ ሁኔታውን ይከታተልጀመር።ዘዴኛዋ ሚስት ለሊት ላይ ሆዴን አመመኝ እያለች ወደጓሮ በመውጣት ከውሽማዋ ጋር ወሲባዊ ግንኙነት ስታደርግ አደረች። ባል ጠዋት ከመኝታውተነስቶ"እንዴት ነሽ ! ተሻለሽ" ብሎ ሲጠይቃት ሚስት በበኩሏ እየቀለደችበት «አንተበጣም ሞኝ ሰው ነህ፣ እኔ ለሊት እየተነሳሁ እውጣ የነበረው አሞኝ ሳይሆን ውሽማዬ ከጓሮ ይጠብቀኝ ስለነበር ከእሱ ጋር ለመገናኘት ነው»አለችው። ይህንን ያደረገችውም ለቀናተኛ ባሏ ትምህርት ለመስጠት ፈልጋ እንደሆነ በመግለጽ በቅናትና በጭቅጭቅ ሴት ልጅን መቆጣጠር እንደማይቻል ትነግረዋለች ። ስለዚህ ባል ጭቅጭቅና መቅናት አቆሞ በእሷ ላይ እምነት እንዲኖረው አበክራ ነገረችው። ባልም ስህተቱን አምኖ በመቀበል ሚስቱን መጨቅጨቅ ትቶ በሰላም ይኖሩ ጀመር ይባላል።

አቶ አኛይ ኡዶል